የተሠበረው ጋሪ እና መዘዙ
ገጽ 11

ሕልምህን ካላከበርከው፤ ትገፈተራለህ!
ገጽ 14

«ልጆቻችሁ ልጆቻችን ናቸው »
ገጽ 16




አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 341 ነሐሴ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ‘‘ድላችን ልምምድ ከምናደርግባቸው በደን የተሸፈኑ አካባቢዎች ጋር የተሳሰረ ነው’’

**- አትሌት ታምራት ቶላ**

አዲስ አበባ፡- ለድል የበቃነው ልምምድ በምናደርግባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ዛፎች የሚፈጥሩትን ነፋሻማ አየር እየተመገብን ነው ሲል በፓሪስ ኦሎፒክ በማራቶን የድል ባለቤት የሆነው አትሌት ታምራት ቶላ ገለጸ።

አትሌት ታምራት ቶላ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)በአንድ ጀምበር 600 ሚሊዮን ችግኞችን እንትከልን ጥሪ ተከትሎ በጉለሌ ዕጽዋት ማዕከል ችግኝ ሲተክል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ እኔ ብዙ ጊዜ ልምምድ የማደርገው በእንጦጦ አካባቢ ነው። እኔም ሆነ አብዛኛዎቹ አትሌቶች ሀገራችንን ለድል ያበቃነው ልምምድ

“ድላችን ልምምድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## የኢትዮጵያ ቱሪዝም - ከአዲሱ ገበያ ተኮር የምንዛሪ ሥርዓት አንጻር

**አዲሱ ገረመው**

**ዜና ትንታኔ**

የኢኮኖሚ ማሻሻያው በተለይም ገበያ ተኮር የምንዛሪ ሥርዓት ትግበራው የተለያዩ ዘርፎች ላይ በጎ ተፅዕኖ እንደሚያሳርፍ

የኢትዮጵያ ቱሪዝም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የመድኃኒታማና መዓዛማ እፅዋቶች ምርምር በወንዶ ገነት


**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

**ዜና ሐተታ**

ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በ268 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኘው የወንዶ ገነት የግብርና ምርምር ማዕከል በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ስር ከሚገኙ የምርም ማዕከላት መካከል አንዱ ነው፡፡

በመድኃኒታማና መዓዛማ እጽዋቶች፣ በሰብል፣ በባዮ ቴክኖሎጂ፣ በግብርና ኢኮኖሚክስ፣ በመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜትና ዘር በምግብ ሳይንስና ሥነ ምግብ፣ በዕጽዋት ጥበቃ፣ በእንስሳት፣ በግብርና ኤክስቴንሽንና በአፈርና ውሃ ምርምር ላይ ትኩረት አድርጎም ይሠራል፡፡

የመድኃኒታማና መዓዛማሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# ኢኮኖሚ ነክ ዘገባን በ‘ፋይናንሺያል ጋዜጠኝነት’

ታደሠ ብናልፈው

**ዜና ሐተታ**

በፋይናሺያል ጋዜጠኝነት የሠለጠነ የሰው ኃይል ባለመኖሩም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በሚገባ ተዘግበው ለሕዝብ ዓይንና ጆሮ ደርሰዋል ለማለት አያስደፍርም።

በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እየተዘገቡ ያሉት ሙያዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን ተለምዷዊ በመሆነ መንገድ ነው። በተለምዷዊ ዘገባ ለማህበረሰቡ ተደራሽ በመሆኑም ኢኮኖሚው ሙያዊ ዘገባን ተርቧል፤ ተጠምቷል።

ሚዲያውና ባለሙያው ስለ ካፒታል ገበያ ምንነትና ጥቅም በሚዘግበው ዘገባ ሕዝቡ ምን ያህል ተረድቷል? ስለ ዋጋ ግሽበትና ከግሽበት ስለሚወጣበት ነገር ምን ያህል ያውቃል? ኢትዮጵያ በኢኮኖሚው እድገት ከአፍሪካ አምስተኛ ደረጃ ላይ ተቀመጠች በሚለው ዘገባ ውስጥ ያስመዘገበችው ሀብትና ደረጃውን ስለያዘችበት መስፈርት በቀላል ቋንቋ ተተንትኖ ማህብረሰቡንና ባለድርሻ አካላት ገብቷቸዋል ወይ? የምጣኔ ሀብት ምሁራንም ሆኖ መንግሥት ስለሚያወራው የዲጂፒ እድገት ማህበረሰቡ ምን ያህል ግንዛቤው አለው?

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንት ወንደወሰን ሙሉጌታ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ያለውን የኢኮኖሚያዊ እድገት፤ ኢኮኖሚዋን ለማሳደግ ስለምታሸሻላቸው ፖሊሲዎች፤ ስለ ካፒታል ገበያ መረጃን በትክክለኛው መንገድ ሰብስቦ፣ አጣርቶ፤ በእውቀት ተንትኖ ለሚመለከታቸው የቢዝነስ ሰዎችና ለማህበረሰቡ ተደራሽ የሚያደርግ የፋይናሻል ጋዜጠኛ ያስፈልጋታል።


ወንደወሰን ሙሉጌታ (ዶ/ር)


አረጋ ይርዳው (ዶ/ር)

የኢኮኖሚ እድገት ሲመዘገብ፣ የኢኮኖሚ ነክ ማሻሻያዎች ሲደረግ ስለ ተመዘገበው እድገትና ስለ ፖሊሲው ማሻሻያው ጥቅም በእውቀት ተንትኖ የሚዘግብ የፋይናሻል ዘጋቢ ባለመኖሩ ሁሉም በግሉና በራሱ መተርጎም ይጀምራል፤ ይህም የተሰሳተ ግምትና መረጃ እንዲኖር ያደርጋል፤ የተሳሳተ መረጃ ሕዝብ፤ ተቋማትና ሀገር ይጎዳል ሲሉ አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ ኢኮኖሚው ዘርፍ ላይ እያደረገች ስላለው ትልቅ ለውጥ፤ ስለምትከተለው የካፒታል ገበያና አስተማማኝ ልውውጥ ስለ እያንዳንዱ ነገር መረጃን በማስደገፍና ዋቢ በማድረግ በአግባቡና በትክክል፣ ተንትኖ ለሚመለከታቸውና ለሕዝብ የሚያደርሱ የፋይናሺያል ጋዜጠኞች መፍጠር አስፈላጊ ነው ሲሉ ነግረውናል።

ሀገሪቱ ስለምትከተለው የገበያ ሥርዓት፤ ስለ አሻሻለቻቸው ፖሊሲዎች፤ እያመጣችው ስላለው ኢኮኖሚያዊ ለውጥ፣ ስለ ምጣኔ ሀብት እውቀት ባላቸው የፋይናሺያል ጋዜጠኞች በትክክልና በግልጽ ቋንቋን ተዘግቦ ለሕዝብና ለቢዝነስ ሰዎች አይንና ጆሮ እንዲደርስ ከተደረገ ዜጎች በኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ በር ይከፍታል ሲሉ ምልከታቸውን አስቀምጠዋል።

ኢትዮጵያ የምታስመዘገበውን የምጣኔ ሀብት

ኢኮኖሚ ነክ ዘገባን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ወይዘሮ ነብል መሃዲ


መምህርት ብዙወርቅ ንጋቱ


ወጣት እታገኝ በቀለ

# “በሀገራዊ መግባባት የሴቶችንና ሀገራዊ ጥቅሞችን ለማረጋገጥ ምክክሩ ወሳኝ ነው ”

*- የሀገራዊ ምክክር ሴት ተሳታፊዎች*

ገመቹ ከድር

ድሬዳዋ፡- እየተካሄደ ያለው ሀገራዊ ምክክር ሀገራዊ መግባባት በማስፈን የሴቶችና ሀገራዊ ጥቅሞችን ለማረጋገጥ ወሳኝ ምዕራፍ መሆኑን በሀረሪና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሀገራዊ ምክክር የተሳተፉ ሴቶች ገለጹ። ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በሀረሪና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አጀንዳ ልየታ ምክክር መርሐ ግብሩን አካሂዷል።

የሀረሪ ክልል ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ወይዘሮ ነብል መሃዲ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክር ሀገራዊ መግባባት በማስፈን የሴቶችና ሀገራዊ ጥቅሞችን ለማረጋገጥ ወሳኝ መሸጋገሪያ ምዕራፍ ነው ። ከምክክሩ የሚገኙ ው ጤቶችም ለዘላቂ ሀገራዊ መግባባትና ሁለንታዊ የሴቶች ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ይሆናሉ ብለዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ምክክር እንደ ሀገር ያለን ዕሴት ሆኖ ሳለ ምክክርን ወደጎን በመተው ሀገር ችግር ው ስጥ እንድትገባ ሆናለች። ሆኖም ግን ወደ ኋላ በመመለስ እና የምክክርን ጠቃሚነት በመረዳት ምክክር ተጀምሯል።

እንደ ሀገር እየተካሄደ ባለው ሀገራዊ ምክክር ሀገራዊ መግባባት ላይ ደርሰን የተሻለች ሀገር መገንባት የጠበቅብናል ያሉት ተሳታፊዋ፤ ይህንን ማድረግ ካልቻልን ቀዳሚ ተጎጂው የማህበረሰብ ክፍል ሴቶችና ህጻናት እንደሆኑ ገልጸዋል።

ሴቶች የትውልድ መሠረት መሆናቸውን በመግለጽም፤ ሴቶች ከተጎዱ ትውልድ ይጎዳል ትውልድ ከተጎዳ ሀገር አይኖርም ሲሉ አብራርተዋል።

ስለዚህ በሃሳብ ልዩነቶች ወደ ግጭት ከሚወስዱ መንገዶች ለመመለስ ቁጭ ብሎ በመመካከር ሀገራዊ መግባባትን በማስፈን ሀገርና ሴቶችን ለማዳን በምክክሩ ሂደት የሁሉም ተሳታፊዎች ማህበራዊ ኃላፊነት ነው ብለዋል።

ሴቶች ሁሉንም የማስታረቅ ተፋጥሮአዊ ጸጋቸውን በመጠቀም ወደ መግባባት የሚያሻግሩ ሃሳቦችን በማመንጨት ሀገራቸውንና ራሳቸውን ከማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ለማው ጣት በምክክሩ ላይ በንቃት ሊሳተፉ እንደሚገባ ጠቅሰዋል።

በሀገራዊ ምክክር ላይ ያልተሳተፉ አካላት ጉዳዩ ትውልድ የማዳን ጉዳይ መሆኑን ተረድተው ሊሳተፉ እንደሚገባ ገልጸው ፤ ኮሚሽኑ ምክክር ሂደቱን አካታችና አሳታፊ ለማድረግ የሐረሪ ክልል ህብረተሰብ እንዲረዳ በተለያዩ ቋንቋዎች ተዳራሽ ማድረጉ ለስኬቱ ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።

መምህርት ብዙወርቅ ንጋቱ የሀኪም ወረዳ መምህራንን ወክለው በመርሐ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር ለምክክር መቀመጣችን በራሱ በማያግባቡን ነገሮች ላይ ለመግባባት 50 በመቶ ርቀት ለመፍትሄ መቅረባችንን የሚያሣይ ነው ብለዋል።

ለልጆቻችን፣ ለእናቶቻችን፣ ለወንድሞቻችን በአጠቃላይም ለሀገራችን ስንል በቅንነትና በታማኝነት በምክክሩ ላይ በመሳተፍ ሀገርና ሕዝብን የሚያሻግሩ ሃሳቦችን ማመንጨት ከሁሉም መርሐ ግብሩ ተሳታፊዎች ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

ይህ የማይሆን ከሆነ በሃሳብ ልዩነቶች ወደ ግጭት በሚያመሩ ድርጊቶች ቀዳሚ ተጎጂዎች ሴቶችና ህጻናት መሆናቸውን በመጥቀስ፤ ሴቶች በመርሐ ግብሩ ሲሳተፉ ሃሳባቸውን ይዘው ከመቀመጥ በንቃት በመሳተፍ ወደ ሀገራዊ መግባባት የሚያሻግሩ የመፍትሔ ሃሳቦች በማመንጨት መሸጋገሪያ ድልድይ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል።

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሴቶችን የወከሉ ተሳታፊ ወይዘሮ ሂሩት ከበደ በበኩላቸው ፤ በምክክር ሀገራዊ መግባባት ከሰፈነ ያልተፈቱ የሴቶች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎችን ለማሻሻል ሀገራዊ የማስፈጸም አቅም እንዲኖራት ያደርጋል ብለዋል።

ሀገራዊ የማስፈጸም አቅም በተገነባ ቁጥር ሴቶች በሁሉም መስኮች መብታቸውን ለማስከበር ሰፊ ዕድል እንዲያገኙ ስለሚያደርግ ሴቶች በምክክሩ በንቃት በመሳተፍ ሀገራዊና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ምክክሩ የሀገርና የሴቶችን ችግሮች ለመለየትና የሀገርና የሴቶች ቁርኝት የሚገለጥበት መድረክ ነው ያለችው ደግሞ ከ01 ወረዳ ወጣት እታገኝ በቀለ ናት።

ሴቶች ይህንን ዕድል ተጠቅመው የራሳቸውንና ለሀገር መፍትሄ ሆኖ ሊያሻግር የሚችሉ ሃሳቦችን ለማፍለቅ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል ብላለች።

## በዞኑ፣ በኩታ ገጠም እየለማ የሚገኘው የመኸር ቦለቄና ስንዴ ውጤታማ ነው

አስቴር ኤልያስ

ሻሸመኔ፡- በምዕራብ አርሲ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች በኩታ ገጠም እየለማ የሚገኘው የመኸር ቦለቄና ስንዴ ውጤታማ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ አስታወቁ።

ፕሬዚዳንቱ፣ በምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ወረዳ ጨፋ ጉታ ቀበሌ፣ ዶዶላ ወረዳ ጨሬ ቀጨማ ቀበሌ እና ገደብ ሃሳሳ ወረዳ ደባራ ቡቡራ ቀበሌ ተዘዋውረው በኩታ ገጠም እየለማ የሚገኘውን የመኸር ቦለቄ እና የስንዴ ምርት እንዲሁም የከብትና የዶሮ እርባታን ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ፤ በዞኑ የጎበኙት የልማት ሥራ ሂደት ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛል። በምዕራብ አርሲ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች በኩታ ገጠም እየለማ የሚገኘው የመኸር ቦለቄና ስንዴ ውጤታማ ነው ሲሉ ጠቅሰዋል።

“የእኛ ባለሀብቶች አርሶ አደሮቻችን ናቸው” ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ሕዝቡ ከዚህ በተሻለ እንዲሠራ አበረታተዋል።

አቅማችን እናንተ ናችሁ ሲሉ አርሶ አደሮችን ያሞካሹት አቶ ሽመልስ፤ ለተሠራው ሥራም ዞኑን አበረታትተው አመስግነዋል።

የምዕራብ አርሲ ዞን ግብርና ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ ኢብሳ ገመዳ በበኩላቸው እንዳስታወቁት፤ የዞን ግብርና ከያዛቸው አራት ግቦች መካከል እየሠራበት የሚገኘው አንዱ ስንዴ ላይ ሲሆን፣ ወጪ ምርትን መሠረት በማድረግ ነው። ስንዴ ቀደም ሲል በሔክታር እስከ 36 ኩንታል ይገኝበታል፤ አሁን ይህንን ቁጥር ወደ 40 ለማሳደግ እየተሠራ ነው።

ከዚህ ቀደም ስንዴ ምርትን በተመለከተ የአመለካከት ችግሮች እንደነበሩ ያነሱት ምክትል ጽህፈት ቤት ኃላፊው፣ በዘርፉ አምራች ኃይል፣ መሬት፣ ውሃና ተስማሚ የአየር ንብረት እያለ ስንዴ ከውጭ በርዳታ ሲገባ መቆየቱን ተናግረዋል።

ችግሩን ለመቅረፍ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ማምረት ይቻላል በሚል በአቀዱት ተነሳሽነት መሠረት በዞኑ በዘንድሮው ዓመት ከ180 ሺህ ሔክታር በላይ በስንዴ እየተሸፈነ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል። በመኸር ወቅት እና በበጋ መስኖ ስንዴ እየለማ እንደሚገኝም አብራርተዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ከዚህ ቀደም የዞኑ አርሶ አደሮች የዓመት ዝናብ ላይ ተንጠልጥለው ያመርቱ ነበር። ይህን በመቀየር በመስኖም ጭምር ማልማት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ በሰፊው ወደ ሥራ ሊገባ ችሏል።

አርሶ አደሮች በዘንድሮ ዓመት ብቻ ከ112 ሺህ ሔክታር መሬት በላይ ስንዴን በመስኖ አምርተዋል፤ ምርታቸውንም ወደ ውጭ ሀገር መላክ ጀምረዋል ብለዋል። እንደ ዞን ከለማው ስንዴ 114 ሺህ ኩንታል ለውጭ ገበያ ማቅረብ መቻሉን ጠቅሰዋል።


በዘንድሮ መኸር ደግሞ ወደ ሰባት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ይገኛል ብለን በመጠባበቅ ላይ ነን ያሉት አቶ ኢብሳ፣ እያመረትን ያለነውም በኩታ ገጠም ነው ብለዋል።

በዚህ ዘርፍ ከአርሶ አደሩ ጋር ውሎ በማደር እየተሠራ እንደሚገኝም ተናግረዋል። ቦለቄም በዞኑ በስፋት እየለማ እንደሚገኝ ተነግሯል።

# በክልሉ ባለፉት ሁለት ወራት ከ240 ሺህ በላይ ዜጎች በወባ በሽታ ተይዘዋል

## - ከፍተኛ የወባ ስጋት ያለባቸው 34 ወረዳዎች ተለይተዋል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሁለት ወራት ምርመራ ከተደረገላቸው 370 ሺህ ዜጎች ውስጥ ከ240 ሺህ በላይ ዜጎች በወባ በሽታ መያዛቸውን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡ ከፍተኛ የወባ ስጋት ያለባቸው 34 ወረዳዎች መለየታቸውም ተመላክቷል፡፡

በቢሮው የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቅኝትና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ተስፋጺዮን ተረፈ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት የሰኔና ሐምሌ ወራት ላይ ምርመራ ከተደረገላቸው 370 ሺህ ዜጎች ውስጥ 64 በመቶ ወይም ከ240 ሺህ በላይ የሚሆኑት ዜጎች በወባ በሽታ በመያዛቸው በቂ ህክምና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የክልሉ መልክዓ ምድር ለወባ በሽታ ተጋላጭ የሚያደርግ በመሆኑ እንዲሁም ወቅቱ ክረምት መሆኑ ለበሽታው መስፋፋት ምክንያት መሆኑን አንስተዋል፡፡

እንደ አቶ ተስፋጺዮን ገለጻ፤ ቢሮው ከአጋር ድርጅቶችና ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን ቅድመ መከላከል ላይ በሠራው ሥራ ከሁለት ወራት በፊት ከነበረው የወባ ጫና አሁን ላይ 11 በመቶ መቀነስ ተችሏል፡፡

የታመሙትን በመለየት በቂ ህክምና እንዲያገኙ መደረጉን ጠቅሰው፤ በተለይ የሞት መጠንን ለመቀነስ በሁሉም ጤና ጣቢያዎች ላይ ምርመራ በማድረግ አፋጣኝ ህክምና እየተሰጠ ይገኛል ብለዋል፡፡

በክልሉ በሚገኙ ስድስት ዞኖች ውስጥ ከፍተኛ የወባ ስጋት ያለባቸው 34 ወረዳዎች ተለይተው ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

ህመማቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ታማሚዎችን የጤና ባለሙያዎች ቤት ለቤት ቅኝት በማድረግ ህክምና እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡

የወባ ትንኝ ቁጥጥር ሥራዎችን ማጠናከር፣ የወባ በሽታ ምርመራና ሕክምና አገልግሎት መስጠት፣ የወባ በሽታ ቅኝትና ምላሽ ማጠናከር፤ የወባ በሽታ በህብረተሰቡ ላይ ስጋት ወደማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ እየተተገበሩ ያሉ ዋና ዋና ስልቶች መሆናቸውን አቶ ተስፋጺዮን አመላክተዋል።

በ2015 በጀት ዓመት ከፍተኛ የወባ ጫና ባለባቸው 50 ወረዳዎች ላይ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ አጎበር ለተጠቃሚው ማህበረሰብ መሰራጨቱን አውስተው፤ ይህም ሰዎችን ከወባ ትንኝ ንክሻ ለመከላከል እንደሚያግዝ አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም በተመረጡ ስምንት ወረዳዎች ላይ የፀረ-ወባ ኬሚካል ርጭት መከናወኑን ጠቅሰው የኬሚካል ግብዓት እጥረት በመኖሩ በሚፈለገው ልክ ለማድረስ እንዳልተቻለ ተናግረዋል።

ማህበረሰቡ ወባን በመከላከል ረገድ ያለውን ግንዛቤ ለመጨመር የሚያስችሉ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሠራታቸውን አስረድተዋል።

ህብረተሰቡ ያቆሩ ውሃዎችን በማፋሰስ፤ የግልና የማህበረሰብ መፀዳጃ ቤቶች ንጽህና በመጠበቅ እና የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎችን በማዳፈን የድርሻውን አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚገባም አቶ ተስፋጺዮን ጠቁመዋል።



ወይዘር አኳታ ቻም

# ከክልሉ ማዕድን ሀብት የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ ሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ይደረጋል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል ከማዕድን ሀብት የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ ሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን የክልሉ የማዕድን ሀብት ቢሮ አስታወቀ።

የጋምቤላ ክልል የማዕድን ሀብት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ አኳታ ቻም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ከማዕድን ሀብት የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ በዘርፉ እንቅፋት የሆኑ ሕገወጦች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ይደረጋል።

በክልሉ በዋነኝነት አራት ወረዳዎች ላይ ሰፊ የወርቅ ሀብት አለ ያሉት ወይዘሮ አኳታ፤ ሆኖም ከዘርፉ መገኘት የሚገባው ጥቅም እየተገኘ አለመሆኑን ገልጸዋል። ለዚህም የኮንትሮባንድ ንግድን ዋነኛ ምክንያት ነው ብለዋል።

ይህ እንደ ሀገርም እንደክልልም ተግዳሮት የሆነው የኮንትሮባንድ ሥራም የተመረተውን የወርቅም ሆነ ሌሎች ማዕድናት በትክክል ለብሄራዊ ባንክ ከማቅረብ ይልቅ ጥቁር ገበያ በማቅረብ ከዘርፉ ተገቢውን ጥቅም እንዳይገኝ ሆኗል ሲሉ ተናግረዋል።

ይህንን ሕገወጥነት በመቅረፍ የተመረተውን ምርት በትክክል ለባንክ ለማቅረብ እንዲቻልም ከክልሉ መንግሥት ጋር በጋራ በመሆን ከክልል እስከ ቀበሌ ባለው ዘርፍ ግብረሃይል አደራጅቷል። የተቋቋመው ግብረሃይል ሕገወጦች ላይ በየጊዜው ክትትል የማድረግ እንዲሁም ፍቃድን እስከመሰረዝ የሚያደርስ ርምጃ የሚወስድ መሆኑን ገልጸዋል።

ክልሉ በ2016 በጀት ዓመት 300 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሄራክ ባንክ ገቢ ያደረገ ሲሆን ከዚህም 50 ሚሊዮን ብር በላይ ለክልሉ ገቢ ተደርጓል። የተገኘው ውጤት በክልሉ ካለው ሰፊ ሀብት አንጻር ከዚህ በላይ መሥራት እና ተጠቃሚ መሆን የሚቻል መሆኑን አመላካች እንደሆነ ኃላፊዋ ተናግረዋል።

በዘርፉ የተሠማሩ 280 ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው አካላት ያሉ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ሥራ ላይ አይደሉም ብለዋል።

በመሆኑን በማዕድን ዘርፍ የክልሉን ቀጣይ ተጠቃሚነት ለማሳደግ፤ ሁሉንም ፍቃድ ያላቸው ሕጋዊ አካላት ወደ ሥራ ለማስገባት እንዲሁም ኢንቨስትመንት አማራጮችን ለማስፋት በዘርፉ ከተደራጁ ባለሀብቶች ጋር የሚሠራ መሆኑን ወይዘሮ አኳታ ጠቅሰዋል።

እንዲሁም ምርቱ በኮንትሮባንድ ንግድ እንዳይባክን የመቆጣጠር፣ በፊት የነበረውን ባህላዊ የወርቅ አወጣጥና አመራረት ዘዴ ወደ ዘመናዊ መንገድ የመቀየር፤ በሕግ እና በንግዱ ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን በማስተካከልና ከመንግሥት ጋር በመቀናጀት የሚሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

# “የኮሚሽኑ አቋም ሁሉም ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሄ ይሆናሉ የሚል ነው”

*- አምባዬ ኦጋቶ (ዶ/ር)*
*የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር*

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የኮሚሽኑ አቋም ሁሉም ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሄ ይሆናሉ የሚል ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባዬ ኦጋቶ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ኮሚሽነር አምባዬ ኦጋቶ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሁሉም ኢትዮጵያውያን በሀገሩ ላሉ ችግሮች መፍትሄ መሆን ይችላል የሚል አቋም ይዞ የሚሠራ ነው፡፡

ኮሚሽኑ ልሂቃንን፣ ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ሲቪክ ማህበራትን፣ መንግሥትን፣ ብዙኃን መገናኛዎችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ አርሶና አርብቶ አደሩን፣ ዲያስፖራውን እና ለኢትዮጵያ የሚበጅ ሃሳብ አለኝ የሚሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሁሉ በዕኩል በማካተትና በማሳተፍ የኢትዮጵያን ችግሮች በኢትዮጵያውያን ለመፍታት እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ከአለችበት ችግር መውጣት የምትችለው ሁሉም ኢትዮጵያውያን የመፍትሄ አካል ሲሆኑ በመሆኑ፤ ኢትዮጵያን ለማንጻት፣ ለማሻገርና የነገዋን ኢትዮጵያ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ተሳታፊ ሊሆኑ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፣ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ያላቸውን እውነት፣ ጥበብ፣ እውቀትና ክህሎት በመሰብሰብ ጠንካራ ሀገርና ማህበረሰብ መገንባት ይቻላል፡፡ በመሆኑም እኔ የኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ ላይ ይመለከተኛል፤ ባለቤትም ነኝ ብለው የሚያምኑ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በምክክሩ እንዲሳተፉ እየተሠራ ነው፡፡



ፎቶ - ገበቡ ገብሬ

የምክክሩ አካታችነት በኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከታችኋል ባለቤት ናችሁ ለማለት እንጂ ከኮታ ጋር የተያያዘ አለመሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በአዋጁ አካታች ናችሁ የሚል የሕግ መነሻ ስላለ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ሁሉ በሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ሳይገለሉ ይሳተፋሉ ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ይህንን የሕግ መነሻ በመጠቀም በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ታጣቂዎች በምክክሩ እንዲሳተፉ ጥሪ እያቀረብን ነው ብለዋል፡፡

ታጣቂዎች ሃሳባቸውን ለምክክር እንዲያቀርቡ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራን ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፣ በኢትዮጵያ ያሉት የሃሳብ ልዩነቶች ጠረጴዛ ላይ ሲመጡ የአንዱ ሃሳብ ለሌላው ስጋትና ጠላት እንዳልሆነ ይገነዘባሉ፡፡ ኢትዮጵያ ብዝሃነት ያላት ሰፊ ሀገር ስለሆነች በሀገራዊ ምክክር ሂደቱ አንዱ የህብረተሰብ ክፍል የሌላውን ጥበብ፣ ዕውቀት፣ ክህሎትና ሃሳብ የማዳመጥ ዕድል ማግኘቱ እና የሌላውን ችግር እያወቀ መሄዱ ጠንካራ ሀገር መገንባት ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን ግጭትና ጦርነት ይብቃን፤ ለሰላም ግንባታ የበኩላችንን ማዋጣት አለብን በማለት በሀገራዊ ምክክሩ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ አመላክተዋል፡፡

ኮሚሽኑ አሁን የደረሰበት ደረጃ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የምክክር ምዕራፍ ላይ ሲሆን፤ 11 ከሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ከየወረዳው ተመርጠው የመጡ ተወካዮች ክልል ውስጥ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚመክሩበት ምዕራፍ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የምክክር ምዕራፍ ከወረዳና ከክልል የተመረጡ ተወካዮች ሀገራችንና ማህበረሰባችንን ሰላም የነሱ አጀንዳዎች እነዚህ ናቸው ብለው በአንድነት የሚስማሙበት፣ በምክክር ሀገርን ማሻገር እንደሚቻል የጋራ ዓላማ የሚሰንቁበት እና ለዋናው ሀገራዊ ምክክር የሚሳተፉ ተወካዮችን የሚመርጡበት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶችን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የምክክር ምዕራፍን ማጠናቀቅ፣ በአማራና ትግራይ ክልሎች የቀሩ ሥራዎችን ማጠናቀቅ፣ ለዋናው ሀገራዊ ምክክር የተመረጡ ተሳታፊዎች በተመረጡት አጀንዳዎች ላይ እንዲመክሩና እንዲደማመጡ ማድረግ የኮሚሽኑ ዋና ዋና ተግባራት መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

# ኢኮኖሚ ነክ ዘገባን...

ከ2ኛ ገጽ የዞረ

እድገትና የምትከተለውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በፋይናንሺያል ጋዜጠኝነትን የሠለጠኑ ባለሙያዎችን ማፍራት አስፈላጊ ነው፤ ይህም ማህበረሰቡ የፋይናንሺያል መረጃዎችን ከተቋማት ብቻ ሳይሆን በባለሙያ ተተንትኖ ከሚቀርብ ዘገባ በቀላሉ እንዲያገኝ ያድርገዋል፤ በኢንቨስትመንት ለመሳተፍም ትክክለኛ ውሳኔ እንዲወስን ያግዛል ብለዋል።

ሚዲያና ጋዜጠኛ ለአንድ ነገር ለመጣልም ሆነ ለማንሳት ትልቅ ሚና አላቸው፤ ማህበረሰቡ እየተመዘገበ ያለውን የኢኮኖሚ እድገት እንዲያስቀጥል ስለካፒታል ገበያ፣ ስለምጣኔ ሀብት እድገት ትክክለኛና ግልጽ የሆነ የኢኮኖሚ መረጃ ማግኘት አለበት ሲሉ ጠቆም አድርገዋል።

በኢትዮጵያ የፋይናንሺያል ጋዜጠኝነት ባለመኖሩ የኢኮኖሚ ዘገባ በሳይንሳዊ መንገድ ለማህበረሰቡ ተደራሽ እየተደረገ ነው ለማለት አያስችልም። የኢኮኖሚን ዘገባን በትክክል ተደራሽ ለማድረግ የፋናንሺያል ጋዜጠኝነትን ሙያን ለጋዜጠኞች በሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸውልናል።

ለጋዜጠኞች ፋይናንሺያል ጋዜጠኝነት ሥልጠና በመስጠት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ፣ ግልጽና ተአማኒነት ባለው መንገድ እንዲዘገብ ማድረግ ተገቢ ነው፤ ሀገሪቱ ስለሻሻለቻቻው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች አተገባበር፣ አፈፃጸምና ጥቅም በትክክልና በግልጽ ቋንቋ ለመዘገብ ያስችላል ሲሉ ጠቅሰዋል።

የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አረጋ ይርዳው (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ የፋይናንስ አዘጋገብ ለማህበረሰቡ ግልፅ ሆኖ በቀላሉ የሚገባ ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም። በኢኮኖሚ ዙሪያ በሚዲያ ተዘግበው ለማህበረሰቡ አይንና ጆሮ የሚቀርቡ ዘገባዎች የአዲስ አበባ ሕዝብን ምልከታ ያደረጉ እንጂ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያካተቱ ናቸው ለማለት አያስችልም።

ኢትዮጵያ ስለምትከተለው የካፒታል ገበያ፤ ስለኢኮኖሚ ማሻሻዎች፣ ስለዋጋ ግሽበት በሚዘገበው ዘገባ ዜጎች ሙሉ የሆነ መረጃ ሆነ እውቀት የላቸውም፤ ፋይናንሺያል ጋዜጠኞችን ለማፍራት መሠራት አለበት ብለዋል።

ማህበረሰቡ ስለካፒታል ገበያ ምን ያህል እውቀት አለው? ስለሚታየው የዋጋ ግሽበትስ ምን ያህል ያውቃል? ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ጂዲፒ እድገት ሲወራ ጂዲፒ እድገት ማለት ምን ማለት ነው ስለሚለው ስንቱ ያውቀዋል? ስለዚህ ፋይናንሺያል ዘገባን በግልጽ አብራርቶና ተንትኖ ለዜጎች አይንና ጆሮ የሚያደርስ የፋይናንሺያል ጋዜጠኛ ለሀገሪቱ አስፈላጊ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ሀገሪቱ ስፖርትን ተንትኖ፤ ፖለቲካንና ባህልን በትኖ የሕዝብን ጆሮና አይን የሚመግብ ጋዜጠኛ እንዳፈራች ሁሉ ኢንቨስትመንቷን የሚያሳልጥ የፋይናንሺያል ጋዜጠኛም ገንብታ ወደ ገበያው ማሰማራት ይገባታል ሲሉ ገልጸውልናል።

የፋይናንሺያል ጋዜጠኛ ኢኮኖሚውን በቀላል ቋንቋ ተንትኖ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ስለሚያደርግ የኢንቨስትመን ዘርፉ እንዲያድግ ከማድረግ ባለፈ ዜጎች ስለሀገራቸው ኢኮኖሚ እድገት ሙሉ የሆነ መረጃ እንዲኖራቸው ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢኮኖሚ ነክ ዘገባዎች ከቁጥራዊ መረጃ ባለፈ በቃላት ተተንትነው ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ ከተሠራ፤ ዜጎች የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት የደረሰበትን የእድገት በቀላሉ ይገነዘባሉ፤ በኢንቨስትመንት ዙሪያ ትልቅ ውሳኔያቸውን አሳርፈው እንዲልፉ ያደርጋል ሲሉ ጠቅሰውልናል።

የፋይናንሺያል ዘገባ በትክክል ተተንትኖ ካልቀረብ ከፍተኛ ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጫና ያስከትላል፤ መረጃዎች የተጠናከሩና ታማኒነት ያላቸው ከሆኑ ደግሞ ኢንቨስተሮች የካፒታል ገበያን ተንተርሰው ወደ ኢንቨስትመንት በስፋት እንዲገቡና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ሲሉ ምልከታቸውን አሳርፈዋል።

ጊዜው የፋይናንሺያል ጋዜጠኝነትን ዘገባ የሚጠይቅ ነው፤ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እድገት፤ እየተከተለች ያለውን የካፒታል ገበያ፤ የተሻሻሉ ፖሊሲዎቿን የትርጓሜ አውዳቸውን፣ ጥቅማቸውን በትክክል ትንትኖ በሚዲያ ለማህበረሰቡና ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ተደራሽ ለማድረግ የፋይናንሺያል ጋዜጠኞችን ማፍራት አስፈላጊ ነው፤ ለማፍራትም መሥራት አለበት ሲሉ ጠቆም አድርገዋል።

# የኢትዮጵያ ቱሪዝም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚጠበቅ ነው። አወንታዊ ተፅዕኖ ያርፍባቸዋል ተብለው ከሚጠቀሱ ዘርፎች ውስጥ አንዱ የቱሪዝም ዘርፉ ነው።

በኢኮኖሚ ዘርፉ በተለይም ገበያ ተኮር የምንዛሪ ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ በኢትዮጵያ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ምን ዓይነት አወንታዊ ለውጥ ይኖረዋል?

የፕላንና ልማት ኮሚሽን “በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ” በክፍላተ ኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ የተወሰዱ ማሻሻያዎችን አስመልክቶ የቱሪዝም ዘርፉን ሁኔታ የሚዳስሱ መረጃዎችን አጋርቷል።

የኮሚሽኑ መረጃ እንደሚያመላክተው፤ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በቱሪዝም ዘርፍ ከተያዙት ዓላማዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሻሻል እና ለሥራ አጥነት ቅነሳ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ናቸው።

የዘርፉን ተዋናዮች እና የመንግሥትን ገቢ ማሳደግ እንዲሁም ለሌሎች ዘርፎች ገበያ እንዲፈጥር ማድረግም የኢኮኖሚ ማሻሻያ በቱሪዝም ዘርፍ ከያዛቸው ዋና ዋና ዓላማዎቹ ይጠቀሳሉ።

የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያን መተግበር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ያሏት እምቅ የተፈጥሮ፣ ታሪካዊ እና ባህላዊ ሀብቶችን በማበልጸግና በመንከባከብ ከእነዚህ ሀብቶች በቱሪዝም ዘርፍ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም በአግባቡ እንድታገኝ በርካታ ተግባራትን ማከናወን እንደተቻለም ያነሳል።

ከእነዚህም ውስጥ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴሩን ዝቅተኛ ተቋማዊ የመፈጸም አቅም ለማገዝ ታስቦ የቱሪዝም ኢትዮጵያ ድርጅት በአዲስ መልክ ተቋቁሟል። በሁለቱ መሥሪያ ቤቶች ጥረትም በዘርፉ ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ልታገኝ የሚገባትን ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳ ዘንድ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ለማከናወን ከተያዙት ተግባራት ውስጥ “ኢትዮጵያ ራይዚንግ” የሚለው የበይነ መረብ የቱሪዝም ማስተዋወቅያ መድረክ በመፍጠር እና የተቀናጀ የማስተዋወቅ ዘመቻዎችን በማከናወን የኢትዮጵያን እሴቶችና መልካም ገጽታ የመገንባት እና የቱሪዝም መዳረሻዎችን የማስተዋወቅ ስራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውንም ሪፖርቱ ያብራራል።

በተጨማሪም በዋናነት ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ከኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቱሪዝም ማስተዋወቅ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ ለማከናወን የሚረዳ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት በርካታ ሥራዎች ሲሠሩ እንደቆዩም ያትታል።

የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ከሚያግዙ ተግባራት መካከል ደግሞ በቅርቡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሻሻለው የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ይጠቀሳል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ፍቃዱ ድጋፌ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱን ወደ ገበያ ተኮር አካሄድ ተሻግሮ በባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ምንዛሪ ተመን የሚወሰንበትን መንገድ ለኢትዮጵያን ቱሪዝም ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ይገልጻሉ።

እንደ አቶ ፍቃዱ ማብራሪያ፤ ከዚህ ቀደም በቱሪዝም ዘርፍ የውጭ ምንዛሬን በተመለከተ አሠራሩ ለቀቅ ያለ ነበር። ከዚህ ቀደም ሰዎች ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር ሲጓጓዙ የውጭ ምንዛሪ ይዘው ይሄዱበት የነበረው መንገድ አንዳንዶቹ አሠራሮች ተቀርፈዋል። በመሆኑም ማሻሻያዎቹ በተለይም ለቱሪዝሙ ዘርፍ አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል።

አቶ ፍቃዱ፤ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሲስተካከል ቱሪስቶች የውጭ ምንዛሪ ይዘው ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ በኢትዮጵያ ብር የሚያገኙት የገንዘብ መጠን ከፍ ያለ መሆኑን በመጥቀስ፤ ይህም ቱሪስቶች ገንዘባቸውን በጥቁር ገበያ ወይም በትይዩ ምንዛሪ የመለዋወጥ ፍላጎታቸውን እንደሚቀንሰው አንስተዋል። ከዚህ አኳያ ይህ ማሻሻያ ኢትዮጵያን ለቱሪስት ምቹ ያደርጋታል ይላሉ።

እንደ አቶ ፍቃዱ ገለጻ፤ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ቱሪስቶች የውጭ ምንዛሪ ተመን ማሻሻያ በኢትዮጵያ ብር ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ከማግኘትም ባሻገር፤ ቱሪስቶች አሁን ላይ ገንዘባቸውን በኦፊሴላዊ ቻናሎች በቀላሉ መቀየር ስለሚችሉ የጥቁር ገበያ ልውውጥን ወይም ትይዩ ዋጋን የመፈለግ ፍላጎት ይቀንሳል። ይህም ኢትዮጵያ ለቱሪስቶች ምቹ እንደትሆን ያስችላታል።

ይሁን እንጂ ማሻሻያውን ተከትሎ የሆቴል ዋጋ እና የትራንስፖርት ወጪ ሊጨምር እንደሚችል አቶ ፍቃዱ ይጠቅሳሉ። ሆኖም ከፍ ያለ የልውውጥ ዋጋ ጥቅሙ ከእነዚህ ወጪዎች የበለጠ እንደሚሆን አስረድተዋል።

ማሻሻያው ቱሪስቶች በኢትዮጵያ ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ አሊያም በጉብኝታቸው ወቅት የበለጠ ወጪ እንዲያወጡ ያበረታታል ተብሎ ይጠበቃልም ነው ያሉት። ይህም ሆኖ የዋጋ ንረት እነዚህን ጥቅማጥቅሞች እንዳይጎዳው የዋጋ ግሽበትን መቆጣጠር አስፈላጊ መሆኑን አመልክተዋል።

የውጭ ምንዛሪ መሻሻል የኢትዮጵያን የቱሪስት መዳረሻነት እንደሚያሳድግና በዘርፉ ላይ በጎ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር አቶ ፍቃዱ ጠቁመዋል።

ማሻሻያው የውጭ ኢንቨስትመንትን ወደ ሀገሪቱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ መሳብ የሚችል መሆኑን ጠቅሰው፤ ባለሀብቶች ከሚያመጡት የውጭ ምንዛሪ ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲይዙ ስለሚፈቀድላቸው ይህ የቱሪዝም አገልግሎት ዕድገትን እንደሚያሳድግ ያብራራሉ። ለሀገሪቱ አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትም ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ተናግረዋል።

ማሻሻያው የሀገር ውስጥ ፍላጎትን እና የቱሪዝም ዘርፉን ኢንቨስትመንት በማነቃቃት የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ የቱሪዝም መስህብ እና የኢኮኖሚ መረጋጋትን እንደሚያጎለብት ይጠበቃል ሲሉ ገልጸዋል።

ማሻሻያዎቹ ለሕጋዊ ምንዛሪ ልውውጥ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በሆቴሎች፣ በጉዞ ኤጀንሲዎች እና በአስጎብኚ ድርጅቶች ላይ በጎ ተጽእኖ እንደሚኖራቸውም አቶ ፍቃዱ አጽንኦት ሰጥተዋል። ይህ በበኩሉ እነዚህ ቢዝነሶች አገልግሎታቸውን እንዲያስፋፉ በማድረግ የቱሪዝም ዘርፉን የበለጠ ንቁ እና በኢኮኖሚ አዋጭ ያደርገዋል ብለዋል።

በሚቀጥሉት ዓመታት የቱሪዝም ዘርፉ ከእነዚህ ማሻሻያዎች የሚመጡትን በርካታ አዎንታዊ ውጤቶችን ሊያስመዘግብ እንደሚችል አቶ ፍቃዱ አመላክተዋል።

# የመድኃኒታማና መዓዛማ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማዕከሉ በመድኃኒታማና መዓዛማ እጽዋቶች ላይ ትኩረት ሠጥቶ እያደረገ ያለው ምርምር እጽዋቱን ከባህል ህክምና ባለፈ ለዘርፉ ብዙ ጠቀሜታ እንዲውሉ በማስቻል ረገድ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ማዕከሉ አስታውቋል፡፡

በምርምር ማዕከሉ፣ የመድሃኒታማና መዓዛማ እፅዋቶች ተመራማሪና የመድሃኒታማና መዓዛማ እጽዋቶች ምርምር ፕሮግራም ብሔራዊ አስተባባሪ ደስታ ፍቃዱ እንደሚናገሩት፣ ሀገራችን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ባላቸው የተለያዩ እጽዋቶች የበለጸገች ብትሆንም እጽዋቱ በይበልጥ የሚታወቁት ከባህል ህክምና እና ከምግብ ቅመምነት ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ባደጉ ሀገራት እጽዋቶቹ ለኮስሞቲክስ፣ ለመድሃኒት እንዲሁም ለምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ያነሱት ተመራማሪው፣ በሀገራችን በእነዚህ እጽዋት ላይ የሚደረገው ምርምር ብዙም ትኩረት የተሰጠው አለመሆኑን ይናገራሉ፡፡ የወንዶ ገነት የምርምር ማዕከል በመድሃኒታማና መዓዛማ እጽዋት ላይ ምርምር በማካሄድ ብቸኛ ማዕከል መሆኑንም አንስተዋል፡፡

ማዕከሉ በምርምሩ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ የታወቁና ጠቀሜታ ያላቸውን የእጽዋት ዝርያዎች ከውጭ በማስገባት የማላመድ ሥራ ሲሠራ፣ ሀገር በቀል የሆኑና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ የተሻሻሉ የእጽዋት ዝርያዎችን በመለየትና ምርምሮችን በማካሄድ በዝርያነት የማስመዝገብና ዝርያዎቹን ተንከባክቦ የማቆየት ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ባለፈው በጀት አመት 36 የሚሆኑ ዝርያዎችን ማስለቀቅ ችሏል፡፡

ተመራማሪው እንዳሉት አርሶ አደሮችንና የግብርና ባለሙያዎች በማሠልጠን የተለቀቁ ዝርያዎችን የማስተዋወቅ፣ የአመራረትና የእንክብካቤ ሂደትን የማሠልጠንና ህብረተሰቡ እጽዋቱን አውቆ እንዲጠቀም የማድረግ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ አፍሪኸርባልን የመሳሰሉ የኮስሞቲክስ ምርቶች ሀገር ውስጥ መመረት መጀመራቸውን አንስተው ሮዝመሪና ሌሎችም የእጽዋት ዝርያዎች በኮስሞቲክስ ኢንዱስትሪዎች ለቅባት፣ 10:10

ሻምፖና መሰል ምርቶች በግብዓትነት ጥቅም ላይ እየዋሉ መምጣታቸውንም አንስተዋል፡፡

እጽዋቶቹ በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ መምጣታቸው አርሶ አደሩን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል ያሉት ተመራማሪው፣ በሀገራችን በተለይ በስልጤና ጉራጌ አካባቢዎች እንዲሁም ሲዳማ፣ ኦሮሚያና አማራ ክልሎች እጽዋቶቹ እየተስፋፉ መምጣታቸውን ተናግረዋል፡፡ በአጠቃላይ እጽዋቶቹ 10ሺህ ሄክታር በሚሆን መሬት ላይ እየተመረቱ እንደሚገኙም አስታውቀዋል፡፡

በእጽዋት ልማት ከሌሎች ምርቶች የአመራረት ሂደት አንጻር አስቸጋሪ አለመሆኑን ያነሱት ተመራማሪው ብዙ እንክብካቤን ሳይፈልጉ በአነስተኛ መሬት በብዛት መመረትና አንዴ ተተክለው ለረጅም ዓመታት ምርት መስጠት የሚችሉ መሆናቸውን አንስተዋል፡፡

አያይዘውም፣ መድሃኒታማና መዓዛማ እጽዋቶች ዘርፈ ብዙ ጠቃሜታ እንዳላቸው ያነሱት ተመራማሪው፣ በጤና፣ በምግብ፣ በኮስሞቲክስና በባዮ ዳይቨርሲቲ ላይ የሚሠሩ አካላት ምርምሩ ትኩረት እንዲሰጡና እንደ ሀገር ከዘርፉ መገኘት ያለበት ጥቅም እንዲገኝ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ጠይቀዋል፡፡

# “ድላችን ልምምድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በምናደርግባቸው ተራራዎች አካባቢዎች የሚገኙ ዛፎች የሚፈጥሩትን ነፋሻማ አየር እየተመገብን ነው።

ልምምድ በማደርግበት እንጦጦ አካባቢ ተገኝቼ ችግኝ በመትከሌ ደስተኛ ነኝ ያለው አትሌት ታምራት፤ አትሌትና ደን የተሳሰሩ ናቸው ሲል ገልጿል።

በደን የተሸፈነ አካባቢ ልምምድ ባናደርግ ኖሮ ለውጤት አንበቃም ነበር ያለው አትሌቱ፤ ምክንያቱም ለድል የሚያበቃንን ልምምድ ስናደርግ የምንመገበው ነፋሻማ አየርን ነው ብሏል።

የአረንጓዴ ዐሻራን ማኖር ማለት አካባቢን መጠበቅና ሰዎች ነፋሻማ አየር እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑን ገልጾ፤ በተለይ ለአትሌቶች በደን የተሸፈኑ አካባቢዎች ላይ ልምምድ ማድረግ ለድል የሚያበቃ መሆኑን እኔ ምሳሌ ነኝ ብሏል።

ከልጅነቴ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ችግኝ መትከል እወዳለሁ ያለው አትሌቱ፣ የአረንጓዴ ዐሻራ የአየር ንብረትን ለውጥ ተከትሎ ከፍተኛ ሙቀት እንዳይከስት የሚያደርግና ነፋሻማ አየር ለማግኘት የሚያስችል መሆኑን የእንጦጦ አካባቢ ምሳሌ መሆኑን ተናግሯል።

ኢትዮጵያን ለዜጎቿ የተሻለች፣ ምቹና ነፋሻማ ሀገር ለማድረግ ሁልጊዜም ችግኝ መትከል ይኖርብናል ያለው አትሌት ታምራት፤ ሁሉም ሰው ልጁን ተንከባክቦ እንደሚያሳድግው ሁሉ የሚተክለውን ችግኝንም ተንከባክቦ ማሳደግ ይጠበቅበታል ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል።

በሩጫው የድል ባለቤት በመሆን ኢትዮጵያን እንዳስጠራናት ሁሉ በአረንጓዴ ዐሻራውም የበለጠ ሠርተን ሀገራችንን ማስጠራት ይኖርብናል። ለዚህም ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ችግኝ መትከልንና ተንከባክቦ ማሳደግን ባህል ማድረግ ይኖርብናል ነው ያለው አትሌቱ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ትናንት በማህበራዊ ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ አዋቂዎች፣ ከ20 በላይ፣ ታዳጊዎች ከ10 በላይ ችግኝ በመትከል ለሀገር ያለንን ፍቅር፣ ለትውልድ ያለንን ስጦታ በተገቢው ስፍራ እንግለጥ ሲሉ ጥሪ ማቅረባቸው የሚታወስ ነው።

የእሳቸውን መልዕክት ተከትሎም አትሌቶች፣ አርቲስቶች፣ ጋዜጠኞችና ተጽዕኖ ፈጣሪ የማህበራዊ ሚዲያ ባለሙያዎች ትናንት በእንጦጦ እጽዋት ማዕከል ተገኝተው ችግኝ ተክለዋል።

ከተከሏቸው ሀገር በቀል ችግኞች መካከል ዝግባ፣ ወይራ፣ ሾላና ብርብራ ይገኙበታል።

2011 ዓ.ም የክረምት ወራት ላይ 20 ሚሊዮን ሕዝብ በተሳተፈበት ዘመቻ በአንድ ቀን 350 ሚሊዮን ችግኞች መተከላቸው ይታወሳል። ይህም በየዓመቱ እያደገ ሄዶ ዓምና በአንድ ጀምበር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር 500 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ዕቅድ ተይዞ 566 ሚሊዮን 971 ሺህ 600 ችግኝ መተከሉን ይታወሳል።

ዘንድሮም በመጪው ነሀሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም በአንድ ጀምበር 600 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ዕቅድ የተያዘ ሲሆን ለዕቅዱ ስኬትም ሁሉም ዜጋ ከጫፍ እስከ ጫፍ አረንጓዴ ዐሻራውን በማኖር ይሳተፋል ተብሎ ይጠበቃል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

## ድሃ ለአንድ ቀን ጨክኖ ጎመን እንዳይበላ ዕድሜ ልኩን ....

**ይታወስ ታሪኩ ከካዛንቺስ**

ቆፍጠን ጅግን ካላልክ የዚህችን ዓለም ትግልና ቀንበር መቋቋምና መመከት አትችልም፤ በዛሬዋ ዓለም እውነታን አስመስለው እንደሚተውኑ አርቲስቶች በምናብ እየተወኑ መጓዝና ድል አደርጋለሁ ብሎ ማሰብ ቂልነት ብቻ ሳይሆን ጅልነትም ጭምር ነው ብዬ አስባለሁ።

ቆፍጣናነትና ጀግንነት በስሜት ሳይሆን በስሌት ሲመሩ ውጤታቸው ያምራል ይሰምራልም። ጀግና ማለት ደግሞ ጨለማን የሚጋፈጥ፤ ሕይወትን የሚያስውብ፣ ያልተፃፉ መልዕክቶችን የሚያነብ፣ ሳትናገር የሚረዳህ፣ ውለታን ሳይሻ ነገን አስቦ መልካም የሚውል ነው። የእነዚህ ሰዎች መፈጠርና መኖር ሀገርንና ሕይወትን ውብ ያደርጋል።

ሺ ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን ብንቃኝ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዘመናት በፊት የዓለማችን የሁለንተናዊ ዕድገት ደረጃ ቁንጮ ተብሎ ከሚታወቁት አምስት ሀገራት ውስጥ አንዷ ነበረች። ይሁንና የእኛዋ አቢሲኒያ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የውስጥ ችግሮቿን በሚገባ መያዝና መፍታት ስላልቻለች በዚሁ ምክንያት የተገነባው ትልቅነቷና ዕድገት ቀስ በቀስ አሽቆልቁሎ ከልዕለ ኃያልነት ወደ ተረጂነት እየወረደች መጥታለች።

ገናናዋ ኢትዮጵያና ኩሩ ሕዝቦቿ ከረጂነት ወደ ተረጂነት ተሸጋግረው በማይመጥናት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ3ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ እየተገነባ የመጣውን የ900 ዓመታት የማያቋርጥ ገናናነት ከ6ኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በእርስ በእርስ ጦርነት ፈተና ውስጥ በመግባቱ ሥርዓተ መንግሥቱና "ትልቅም ነበር ትልቅም እንሆናለን" የሚለው ትልቅ ራዕይ ምኞት ብቻ ሆኖ ቆይቷል።

ልዩነቶችን አቻችለንና ሀገራዊ አንድነታችንን አጠናክረን መቀጠል ሲገባን ከዚህ በተቃራኒው እየተባባሰ የመጣው የርስ በርስ ጦርነትና ግጭት የሀገሪቷን ፈተና 1262 ዓ.ም. ጀምሮ የጎንደር ዘመነ መንግሥት በ1632 ዓ.ም እስከሚመሠረት ድረስ ኢትዮጵያ ወደለየለት ዝቅጠት የምትሄድበት ዘመን አመላካች ሆኗል።

ለዚህ በአብነት የሚጠቀሰው በአክሱምና ላስታ ለዘመናት የአንድ መንግሥት አዛዥነትን ገንብቶ የማስተዳደር ልምድ የዘለቀ ቢሆንም፤ ወቅቱ አንድ ማዕከላዊ መንግሥት የሚቀመጥበት ማዕከል የሌለበት፣ የሥርዓተ መንግሥት አመራር መስጫና ልዩ ቦታ ያልተገነባበት፣ በስም ብቻ በአካባቢያዊ መጠሪያ "የደጋ ክርስቲያን መንግሥት" በሚል ንግሥና በቤተሰባዊ ውረድ ተዋረድ የሚተላለፍበት ነበር።

ሀገር የምትመራበት መርሕ እያጣች ስትመጣ፣ የንግድ መስመሮቿ በሰሜን በኩል በቱርክ፣ በምሥራቅ በኩል በአዳል መንግሥት ተቀማ፤ በዚህም በወቅቱ እራሱን እንደ ማዕከላዊ መንግሥት የሚመለከተው "የደጋ ክርስቲያን መንግሥት" ወደ ጦርነት ገብቷል ።

አንዳንድ በአሉታዊ ትርክት የተካኑና አክራሪ የታሪክ ጸሐፊዎች ጦርነቱ በሃይማኖቶች መካከል የተደረገ ጦርነት ለማስመሰል ቢሞክሩም ሐቁ ግን የምሥራቁን ወደብ ተቆጣጥሮ የንግድ መስመሩን የማስተዳደር ፍልሚያ፤ የኢኮኖሚ የበላይነትን የመቆጣጠር ጉዳይ እንደነበር ብዙዎች ይስማማሉ ።

ይህንን ተከትሎ በሀገሪቱ ይስተዋል የነበረውን ሥልጣንን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችን በማስቆም፤ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የመመሥረት ጥረት በዓፄ ቴዎድሮስና ዮሐንስ ቢጀመርም፤ የተጠበቀውን ያህል ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል። ይህ ጥረት በዓፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ፍሬ አፍርቶ ሀገርን በአንድነት ማቆም ተችሏል። ይህም ሆኖ ግን ሥርዓቱ የቆመበት ፖለቲካ ኢኮኖሚ አጠቃላይ የሆነውን የሕዝቡን ፍላጎት የሚመልስ አልሆነም።

የአፄ ኃይለ ሥላሴ የአገዛዝ ሥርዓትም በዘመናዊነት ስም በጭቆና የተቃኘ ንጉሣዊ/ሉዓላዊ ሥርዓት መሆኑ፤ ሀገሪቱ ለገዛ ዜጎቿ የእስር ቤት ያህል የሆነችበት፤ ዜጎችም የገዛ ሀገራቸው ባለቤት ከመሆን ይልቅ እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚቆጠሩበትን ሁኔታ ፈጥሯል። እነዚህንና መሰል እውነታዎች ለዘመናት በልዕለ ኃያልነት ትታወቅ የነበረችውን ሀገር በግጭት አዙሪት ዋጋ እንድትከፍል አድርጓታል። በሕዝቦች የመብት ጥያቄ ስም የተደረጉ "የነፃነት" ንቅናቄዎችም ችግሩን እያባባሱት መለያዋ ስደት፣ ችግር፣ ረሃብ ሆኗል።

በትንንሽ የመንደር አለቆች ያገነገነው፣ በአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ላይ የቆመው የአፄዎቹ ሥርዓት በውስን የመሬት ባለቤትነት፣ መላውን ሕዝብ ጭሰኛ አድርጎ የሄደበት መንገድ፤ ሕዝቡ የሚፈልገውን ነፃነት፣ እኩልነት እና ፍትሕ ለማግኘት አላስቻለውም። የሕዝቦችን ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ አላስቻለም። ይህም ኃይልን ያካተተ ያልተደራጀ ትግል እዚህም እዚያም እንዲፈጠር አድርጓል።

በራያና ቆቦ፣ በጐጃም፣ በባሌና በጌዴኦ ሥርዓቱን ለመጣል የተደረጉ ጥረቶች የዚሁ ማሳያ ናቸው። ሙከራ ትግሉ በወቅቱ ከነበረበት የአደረጃጀትና የአመራር ክፍተት እንዲሁም፤ ሥርዓቱ ከነበረው ዘመናዊ ወታደራዊ አደረጃጀትና ጦር መሣሪያ የበላይነት አኳያ ውጤታማ መሆን ሳይችል ቀርቷል።

ሥርዓቱ በየቦታው በተነሱ የመብት ጥያቄዎች አጣብቂኞች ውስጥ ገብቶ በነበረበት በዚህ ወቅት በተፈጠረ የረሃብ፣ የኑሮ ውድነት፣ ሙስናና አጠቃላይ የሕዝብ ቅሬታ የ1966ቱ አብዮት እንዲፈነዳ ግድ ሆነ። ተቀጣጥሎ የነበረው የሕዝቦች ትግልም የተደራጀ ኃይል ባለመኖሩ በወታደራዊ መንግሥት ተጠልፎ የለውጡ መሻት ጉዞ ወደ ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር ተቀይሯል። ጭቆናን የሚታገሉ ኃይሎች ትግላቸውን ወደ ትጥቅ ትግል በመቀየራቸውም የዜጎች ደም መፍሰስ ተባብሶ ቀጥሏል።

በሀገሪቱ በተፈጠረውን የፖለቲካ አለመረጋጋት እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ የወሰደው ወታደራዊ መንግሥት ወደሥልጣን መጥቷል እሱም ቢሆን በሥልጣን ላይ በነበረባቸው 17 ዓመታት፤ ሀገር ከውስጥም፤ ከውጪም ያጋጠማትን ፈተናዎች መሻገር ባለመቻሉ፤ ሀገር እና ሕዝብን ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎችን ካስከፈለ እና ከብዙ የደም መፋሰስ በኋላ በጠበንጃ ትግል በተለመደው የአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ከሥልጣን ተወግዷል።

በ1983 ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ/ም ወደ ሥልጣን የመጣው ኢሕአዴግ መራሹ መንግሥት ለ27 ዓመታት በልዩነት ትርክት /በዘር፣ በቋንቋ እና በሃይማኖት/ ሀገሪቱን ገዝቶ፤ በ2010 መስዋዕትነት በጠየቀ የሕዝብ ትግል ከሥልጣን ተሰናብቷል። በሥልጣን ዘመኑ የፈጠራቸው የልዩነት ትርክቶችም አሁን ላይ ፈተና በመሆን ሀገሪቱ ከተለመደው የግጭት አዙሪት እንዳትወጣ አድርጎናል ።

ይሄን ሀገራዊ የታሪክ ትርክት በወፍ በረር ለማንሳት እና የጽሑፌ መንደርደሪያ ያደረግኩበት አንድም የመጣንባቸው ያለመደማመጥ /የግጭት/ መንገዶች የቱን ያህል ዘመን እየተሻገሩ ዛሬ ድረስ እንደ ጥላ እየተከተሉን፤ ብዙ ያልተገባ ዋጋ እያስከፈሉን፣ "ከትናንት ገናና ታሪካችን አውርደው ዛሬ ላይ እንዳቆሙን፤ ከሁሉም በላይ ከትናንት አለመማራችን ችግሩ ዛሬም ፈተና እንደሆነብን ለማሳየት ነው።

እነዚህን ረጅም የፈተና ጊዜያትን /የግጭት ዘመናትን ሳስብ ለምን "ከሱሪ ሱሪህን" እልህ ወጥተን በሠለጠነ መንገድ ቁጭ ብለን በችግሮች ዙሪያ ተወያይተን፤ ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ ማፈላለግ አቃተን፤ ለምን የየዘመኑ ትውልድ ከትናንት ጥቁር ታሪካችን መማር አቃተው፤ በርግጥ ከቀደመው የገናናነት ታሪካችን አኳያ ችግሮቻችን ከኛ በላይ ናቸው የሚሉት ጥያቄዎች በውስጤ ይመላለሳሉ።

ዛሬ ምፅዋት የምንለምናቸውና አንዳንዶቹም የዓለም ፖሊስ የሆኑ ሀገራትን ስናይ አሁን ለደረሱበት ደረጃ ውስጣዊ ጉዳዮቻቸውን በራቸውን ዘግተው በራሳቸው ማንንም ጣልቃ ሳያስገቡ እርስ በርሳቸው ተነጋግረው መፍታት በመቻላቸውና መድረሻቸውን ሳይጀምሩ በሀሳብ የጨረሱ ያወቁ በመሆናቸው ነው።

ዛሬ ሁላችንም የምንመኛትና የምንናፍቃት አሜሪካ በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ሕዝቦቿ በቆሻሻ፣ በነፍሳት እና በአስቸጋሪ ጠረኖች ውስጥ ይኖሩ እንደነበር የተለያዩ ጽሑፎች ያስረዳሉ። የእርሻ ቦታዎቻቸውም ጭምር በእንስሳት እዳሪ (ቆሻሻ) የተጥለቀለቀና በየቦታው ፍግ የተበተነ የገበሬዎቹ ቦት ጫማ እና ሱሪ ንፅሕና የጎደለው ነበር።

ምንም እንኳን አሁን በዘመናዊና በሳይንሳዊ መንገድ እየከወኑ ለዓለም የተረፉ ቢሆንም፤ የሥራ

"
ዛሬ ምፅዋት
የምንለምናቸውና
አንዳንዶቹም የዓለም ፖሊስ
የሆኑ ሀገራትን ስናይ አሁን
ለደረሱበት ደረጃ ውስጣዊ
ጉዳዮቻቸውን በራቸውን
ዘግተው በራሳቸው ማንንም
ጣልቃ ሳያስገቡ እርስ
በርሳቸው ተነጋግረው መፍታት
በመቻላቸውና መድረሻቸውን
ሳይጀምሩ በሀሳብ የጨረሱ
ያወቁ በመሆናቸው ነው

ልብሳቸው ብዙውን ጊዜ ቆሻሻ እና ደረቀ ላብ የበዛበት ከመሆኑ የተነሳ የጠነከረ፤ የወንዶቹ ሸሚዝ ደግሞ በትምባሆ ጭማቂ "በቢጫ ኅብር ወይም ሪቫሌቶች" የተበከለ ነበር፤ ነገር ግን ነገን አስበውና የሚደርሱበትን ከጅምሩ ጨብጠው በጥፍራቸው ቆመው ለማደግና ለመለወጥ ታግለዋል።

ዛሬም እኛ በታሪክ አጋጣሚ የዛሬው ትውልድ ላይ የምንገኝ ፈጣሪ የሚሰጠንን አዳዲስ ቀንና መልካም ዕድሎችን በመጠቀም ከግጭት አዙሪት የምንወጣበትን መንገድ ማፈላለግ፤ ለዚህ የሚሆን ድፍረት እና ዝግጁነት ያስፈልገናል። ለትውልድና ለአገር የሚበጅ ነገር መከወን ለነገ ድርጊቶቻችን የሕይወት ዘመን ሽልማቶቻችን መሆኑን በመረዳት "ደግ አባት ዕርስት ያቆማል ክፉ አባት ዕዳ ያቆያል" እንደሚባለው በቅን መንፈስ መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል።

የሕይወት ዘመን ዓላማ እና ግባችን ከራስ ጥቅም በላይ ትውልድን እና ሀገርን ተሳቢ ያደረገ፤ ከቋንቋ እና ከማስመሰል ባለፈ ሆኖ መገኘት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል። በርግጥ መኖር ማለት አለመሞት ከሆነ እስትንፋስ ያለው ሁሉ እየኖረ ነው። እውነታው ግን ከዚህ ያለፈ ነው፤ መኖር ማለት ራስን መሆን፣ ለዓላማ መቆም ሕሊናን አለመዘንጋት ፍርድ አለማጓደል ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌላው ራስን መስዋዕት ማድረግ ብሎም አርዓያ የሚሆን ነገር ጥሎ ማለፍ ነው።

ዋጋውን በሰው ዕይታ ውስጥ ሳይሆን በሕሊናው ውስጥ መፈለግ ያቃተው እና ዓሣውን ከውሃ ውስጥ አውጥቶ ከመስመጥ አዳንኩት ከሚል ጉንጭ አልፋ ሙግት ከሚገጥም ጋር ጊዜ ማባከን አስፈላጊም አይደለም። ለራሳችን ታማኝ ሆነን ማምለጫ አጀቦችን ሳንደረድር ምክንያታዊ የሆነ ዘለቄታዊ መፍትሔ ለማግኘት የምናደርው ጥረት አስደሳች ስሜትን እንድንጎናጸፍ የሚያደርገን ከመሆኑም በላይ፤ ኢትዮጵያ በምትባል ትውልድ የሚቀጥልባት ሀገር ውስጥ ተወዳሽ አልያም እንደ ሥራችን ተወቃሽ የሚያደርገን ነው።

መንፈሳዊ ዕድገት የሚገኘው ከራስ የበላይ ማንነት ጋር የሚኖር መስተጋብር ሲጎለብትና ይኸው የራስ የበላይ ማንነት እያንዳንዷን የሕይወታችንን ሂደት እንዲመራ ስንፈቅድ ነው። በማንበብ፣ በመማር፣ በመመራመር፣ ታላቅ ፍጥረት መሆናችንን በመገንዘብና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ምክንያታዊ ስንሆን ዛሬ ከነበርንበት መስፈንጠር እንችላለን።

በእርግጥ ወደ ብልፅግና የምናደርገው ጉዞ መራራ ነው፤ ነገር ግን ጨክነው ከወሰዱት ወይም ከጠጡት እንደኮሶ መድኃኒት ያሽራል፣ ይፈውሳልም። ሺህ ዓመት ጎመን እየበሉ ከመኖር የተወሰነ ሰዓት ጨክን ብሎ ጎመንን በልተው ሺህ ዓመታትን በብልፅግና እና በተድላ መኖር ተመራጭም የግድም ሊሆን ይገባል፡፡

ድሮ ድሮ ልጅ እያለሁ አክስቴ "ድሃ ለአንድ ቀን ጨክኖ ጎመን እንዳይበላ ዕድሜ ልኩን እየተሰቃየ ይኖራል" ትለኝ ነበር። አሁን ላይ ቆም ብዬ ሳስበው ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ያለው መልዕክት ትልቅ ነው። ስለሆነም አሁን ላይ ይበቃል፣ እስከ መቼስ ኋላ ቀር፣ ተመፅዋች እና ድሆች እየተባልን እንኖራለን በማለት የምንቆጭ ብቻ ሳይሆን የችግሩ መቋጫችንም መሆን ይኖርብናል።

የሸረሪት ድር አድርቶባት ለነዋሪዎቿ የማትመች እንደነበረችው ከተማችን አዲስ አበባ ጨክነን ግልጥልጥ በማድረግ እንደስሟ ውብ እንደተደረገው ሁሉ መራራም ቢሆን እንቆቆውን አልመን በመጨለጥ ከትናንት በሽታችን እንፈወስ። ከትናንት የግጭት ታሪኮቻችን ተምረን ለዘላቂ ሰላማችን እና ከዚህ ለሚመነጨው ብልፅግናችን ዘብ እንቁም ።

እንደ ሀገር አንድነታችንን እና ወንድማማችነታችንን ማጽናት ለኛ የምርጫ ጉዳይ አይደለም፤ የነገ ተስፋችን እና ብሩህ እጣ ፈንታችን ከዚህ የሚመነጭ ነው ።ለዚህ ደግሞ በችግሮቻችን ፤በአለመግባባቶቻችን ዙሪያ ከአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት እና ትርክቱ ከፈጠረው እና ሊፈጥረው ከሚችል ጥፋት ወጥተን ወደ አዲስ የመደማመጥ መንገድ መምጣት አለብን ።

በተለወጠ ማንነት ፤በሰከነ መንፈስ ከልዩነት ይልቅ በሚያግባቡን ጉዳዮች ላይ በማተኮር ፤ የጋራ ትርክቶቻችን ላይ ቆመን ፤ የተለወጠች ሀገር ለመፍጠር መትጋት ይኖርብናል ።ይህም የምንመኛውን ሀገራዊ ብልጽግና ተጨባጭ ለማድረግ አልፋ እና ኦሜጋ ነው። ይህንን በአግባቡ በቅንነት መረዳት እና ተግባራዊ ማድረግም ከሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ የሚጠበቅ ነው። አይቀሬውን የለውጥ /የመለወጥ ተግዳሮት በጽናት መሻገር የምንችለው በዚህ እና በዚህ ብቻ ነው ፡፡

ሰላም!!!

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## "የከተማዋ የቀላል ባቡር መስመር ኮንቬንሽናል ሀገር አቋራጭ የጠጠር መንገድ የተተገበረበት ነው"

- ኢንጂነር አስረስ ኪዳኔ፣
አርክቴክት እና ሲቪል መሐንዲስ፤



ወንድወሰን ሽመልስ

ውልደታቸው፣ የጥበበኞቹ ሰፈር አዲስ አበባ ሾሮ ሜዳ አካባቢ ነው፤ የልጅነት ጊዜያቸውንም በሕጻናት አምባ አሳልፈዋል። የሾሮ ሜዳም ሆነ የሕጻናት አምባ ቆይታቸው ግን ከስምንት ዓመታት የዘለለ አልሆነም። ምክንያቱም በስምንት ዓመታቸው ከኢትዮጵያ የመውጣት አጋጣሚ ተፈጠረላቸው። እኝህ ሰው፣ ኢንጂነር አስረስ ኪዳኔ ካሣ ይባላሉ፡፡

ኢንጂነር አስረስ ኪዳኔ፣ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ፤ በዜግነት ስፓኒሽ(ስፔናዊ) ናቸው። በትምህርት ዝግጅታቸውም፣ በኩባ ፊዚካል ፕላኒንግ፣ በስፔን አርክቴክቸር፣ በዩኬ(እንግሊዝ) ሲቪል ምሕንድስና ከፔይስሊ (west of Scotland) ዩኒቨርሲቲ በባችለር ዲግሪ፣ ከዛው ከእንግሊዝ ስትራትክላይድ ዩኒቨርሲቲ በሲቪል ምሕንድስና ማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል።

በሥራ ልምዳቸውም ቢሆን፣ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ልምዳቸውን ጨምሮ በባቡር መሐንዲስነት ከ20 ዓመታት በላይ ሠርተዋል። በዚህም ኢትዮጵያን ጨምሮ በተለያዩ ሀገራት አገልግለዋል። ለአብነትም፣ በኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን በባለ 1 ሜትር ስፋት ባለው የድሮው ባቡር (በተለይም በመተሐራ-አዋሽ እና ድሬዳዋ አካባቢዎች ላይ) ሠርተዋል፤ በኋላም በመንግሥት ጥያቄ ቀርቦላቸው የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ባለ አንድ ሜትር ከግማሽ የአውሮፓ ደረጃውን የጠበቀ የባቡር መስመር ዲዛይን እና ሪቪው ላይ ተሳትፈው ሠርተዋል።

በተለይ የአዋሽ-ወልድያ የባቡር መስመርን ዲዛይን በማድረግ፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ-ጅቡቲ መስመር ዲዛይን ሪቪው ላይ ዕውቀት በማስተላለፍ አስተዋፅዖ አድርገዋል። ኢንጂነር አስረስ፣ በአሁኑ ጊዜ በስፔን ሀገር የስፔን የመንግሥት ባቡር ኮርፖሬሽን (ADIF) በመሠረተ ልማት ውስጥ ዳይሬክተር በመሆን የምዕራብ ስፔን የባቡር ሐዲድ ኔትዎርክ አስተዳደርን በኃላፊነት እየመሩ ይገኛሉ፡፡

የዛሬው የዘመን እንግዳ ሆነው ልምድና እውቀታቸውን እንዲያጋሩ ያቀረብናቸው ኢንጂነር አስረስ፣ በኢትዮጵያ የባቡር ቴክኖሎጂ ዙሪያ በተለይ በሂደቱ ተሳታፊ ስለነበሩበት የአዲስ አበባ የቀላል ባቡር ፕሮጀክት ትግበራ እና የትግበራ ሂደት ችግሮቹ ላይ ትኩረት በማድረግ ሀሳብና አስተያየታቸውን ያጋሩን ሲሆን፤ በተለይ ፕሮጀክቱን ዛሬ ላይ ካለበት ችግር ለማላቀቅ መወሰድ ስለሚገባቸው ርምጃዎችም ሙያዊ ምልከታቸውን አጋርተውናል። እኛም የባለሙያውን ሀሳብና ሙያዊ ማብራሪያ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሀገራት በከተሞች ያለን የትራንስፖርት አገልግሎት በተለያየ መልኩ ለዜጎቻቸው ተደራሽ ሲያደርጉ ይስተዋላል። ከእነዚህ መካከል አንዱ የከተማ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ነው። ስመሆኑ የከተማ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት ከሌሎች ትራንስፖርቶች ምን የተለየ ባሕሪ አለው? ተመራጭነቱስ?**

**ኢንጂነር አስረስ፡-** እንደየሀገራት ተጨባጭ ሁኔታ በከተሞች የተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮችን ለከተማው ነዋሪ ያቀርባሉ። እንዳልከውም የከተማ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አንዱ ነው። ይሄ ከሌሎች የትራንስፖርት አገልግሎቶች የሚለዩት የራሱ ባሕሪያት ያሉት ከመሆኑ አኳያ በተለይ ባደጉት ሀገራት በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ፤ በማደግ ላይ ያሉትም ሆነ የማደግ ተስፋን የሰነቁ ሀገራትም ወደዚሁ ቴክኖሎጂ እየገቡ ያለበትን እውነት እንገነዘባለን፡፡

ለምሳሌ፣ የከተሞች ቀላል ባቡር ትራንስፖርት በራሳቸው ትራኮች ላይ ተወስነው ከመንገድ ትራፊክ ነፃ ሆነው የሚሠሩት ናቸው። ይሄ ደግሞ ፈጣን እና የተቀላጠፈ አገልግሎትን እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል። ከዚህ በተጓዳኝ ፈጣን እና ቀልጣፋ ምልምልስ ባደረጉ ቁጥር፣ በከተሞች የሚኖረውን የትራፊክ መጨናነቅ የማቅለል ዕድል ይሰጣሉ። በከተማ መንገዶች ላይ ያሉትን ተሽከርካሪዎች ቁጥር በመቀነስ፣ የትራፊክ መጨናነቅ እንዲቀንስ እና በከተሞች የትራፊክ ፍሰቱ እንዲረጋጋ ያደርጋሉ።

ከዚህ ባሻገር፣ እነዚህ ባቡሮች ታዳሽ ኃይልን የሚጠቀሙ ከመሆኑ አንጻር፣ በራሳቸው ለአየር ብክለት የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ካለመኖሩም በላይ፤ በተሽከርካሪዎችን ምልልስ ምክንያት በከተሞች በአብዛኛው በነዳጅ የሚሠሩ ሞተሮች የሚለቁትን የበካይ ጋዝ መጠን ለመቀነስ ያስችላሉ። የሚጠቀሙት የኤሌክትሪክ ኃይልም ከነዳጅ አንጻር በዋጋ ያነሰ እንደመሆኑ፣ ለከተማ ነዋሪዎች በአንጻራዊነት የረከሰ የትራንስፖርት አማራጭን ያስገኛሉ፤ ምቹና ደኅንነቱ የተጠበቀ፣ ቀልጣፋ እና አስተማማኝ አገልግሎትንም ለነዋሪዎች ለመስጠት ማስቻላቸው ነው እንደ አንድ የትራንስፖርት አማራጭ ሆነው እየቀረቡ ያለው፡፡

ምክንያቱም፣ የከተማ አካባቢዎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደኅንነት የሚወሰነው በጥሩ ሁኔታ በሚሠራ የትራንስፖርት ሥርዓት ላይ ነው። ይህም ሰዎች እቃዎችን እና አገልግሎቶችን በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። በተለይም በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት እና በአዳጊ ኢኮኖሚ ውስጥ ያሉ አብዛኞዎቹ የከተማ አካባቢዎች በመጠን እና በሰዎች ቁጥር እየሰፉ በመሆናቸው የመጓጓዣ እና የመንቀሳቀስ ፍላጎት ይጨምራል።

በአብዛኛዎቹ ባለታዳጊ ኢኮኖሚዎች ከተሞች በተቀላጠፈና ምቹ ትራንስፖርት እጥረት ምክንያት የትራፊክ መጨናነቅ፣ አደጋዎች እና የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀቶች ተጋላጭነት ስጋት አለባቸው። በመሆኑም በማደግ ላይ ባሉ ኢኮኖሚዎች ውስጥ ከትራንስፖርት ሥርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት እያደገ የመጣውን የከተማ ሕዝብ ለማንቀሳቀስ ዘላቂነት ያለው የብዙኃን ትራንስፖርት ሥርዓት(mass transit system) ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት በከተሞች ተመራጭ እየሆነ መጥቷል፡፡

**አዲስ ዘመን፡-የከተሞች ቀላል ባቡር ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ዝርጋታ ታሳቢ የሚያደርጋቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው? በምን አግባብስ ሲከናወን/ ሲተገበር ይገባዋል?**

**ኢንጂነር አስረስ፡-**የከተማ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ተግባራዊ ሲደረግ፤ ሥራው ከመሠረተ ልማት ዝርጋታ እና አስፈላጊ ነገሮችን ከማሟላት የሚጀምር ነው። ከዚህ አኳያ፣ የከተማ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ሥራ ሲከናወን ታሳቢ ከሚያደርጋቸው ጉዳዮች አንዱ የከተማው እድገት እና ፕላን ነው። ምክንያቱም፣ አንድ ፕሮጀክት ሲተገበር የሚተገበርበትን ከተማ የእድገት ሁኔታ እንዲሁም የከተማዋን ፕላን ማገናዘብ ይኖርበታል፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ፣ የከተማዋ የሕዝብ ቁጥር እድገት ሁኔታ፣ የአካባቢ ተስማሚነት/ተፅዕኖው፣ የፋይናንስ አቅም፣ የቴክኖሎጂ እና የሰው ኃይል (በዘርፉ ያለን የሠለጠነ የሰው ኃይል) እና መሰል ጉዳዮችን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባዋል። ይሄን ማድረጉ የሚተገበረው ፕሮጀክት ዘላቂ፣ አስተማማኝ፣ ደኅንነቱ የተጠበቀ፣ ከአካባቢ ተፅዕኖ/ብክለት የፀዳ፣ የቀጣይ የከተማዋንም ሆነ የሕዝብ ቁጥር እድገት ጥያቄ መመለስ የሚችል፣ የከተማን ውበት እና የሕዝቡንም ማኅበራዊ ብሎም ኢኮኖሚያዊ ጉድኝት በማያውክ መልኩ እንዲፈጸም ያስችለዋል፡፡

በዚህ መልኩ የሚከወን የከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ብዙ ጥቅሞች አሉት። ለአብነት፣ ባቡሮች በከፍተኛ ፍጥነት ብዙ ሰዎችን ማንቀሳቀስ ይችላሉ። በቦታ መነጠል (የተለየ መሆን) ምክንያት አስተማማኝ አገልግሎት ይሰጣሉ። የኃይል ምንጩም ታዳሽ በመሆኑ፣ የአደጋ ተጋላጭነቱም አነስተኛ ከመሆኑ አኳያ እያደገ የመጣውን የከተማ ሕዝብ በብቃት ለማጓጓዝ ያስችላል፡፡

ለዚህም ነው በታዳጊ እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት በዓመት ፍላጎቱ እየጨመረ የሚታየውም፣ እድገቱም በአማካይ በሶስት ነጥብ አምስት በመቶ ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚታየው። መረጃዎች እንደሚያሳዩትም እ.ኤ.አ. በ2018፣ 907 ነጥብ አንድ ኪሎ ሜትር የመሬት ውስጥ(የሜትሮ) መስመሮች በታዳጊ እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች የተሠሩ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥም 94 ነጥብ አምስት በመቶ አዳዲስ የሜትሮ መስመሮች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የከተማ ቀላል ባቡር ትራንስ ፖርት መሠረተ ልማት ዝርጋታ ታሳቢ ሊያደርጋቸው ከሚገቡ ጉዳዮችም ሆነ ከአተገባበሩ አኳያ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር መስመርና መሠረተ ልማት ዝርጋታን እርሶ እንዴት ይገመግሙታል?**

**ኢንጂነር አስረስ፡-** የአዲስ አበባ የቀላል ባቡር ፕሮጀክት እንደ ሀገር አዲስ ቴክኖሎጂን ያስተዋወቀ፤ ለዘርፉ የሰው ኃይል አቅም ግንባታ የእውቀት ሽግግር የተገኘበት፤ እና ሌሎችም ዕድሎችን ይዞ የመጣ ነው። ለምሳሌ፣ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር የተገነባው ዘመናዊ በሆኑ የምሕንድስና ዘዴዎች እና በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሥራ ላይ በዋሉ ቴክኖሎጂዎች ነው። በሁለቱም የባቡር መስመሮች ላይ ጥምር ስታንዳርድ ስፋት ያላቸውን የባቡር ሐዲዶች (Double Track) ያቀርባል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ መልካም ዕድሎች የተገኙበት የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር መስመርና መሠረተ ልማት ዝርጋታ፤ አንድ የከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት መሠረተ ልማት ሲከናወን ሊከተላቸው ከሚገቡ መሠረታዊ ጉዳዮች አኳያ ብዙ ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡

በዚህ ረገድ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆኜ በአሜሪካ ዶላር ከኢትዮጵያ ግብር ከፋዮች ተወስዶ እየተከፈለኝ ሂደቱ እንደተሳተፈ አንድ ባለሙያ እራሴን ጥፋተኛ አድርጌ በመጀመር ነው ስለ ፕሮጀክቱ ችግሮች ማውራት የምፈልገው። ይሄን የምለው ግን ችግሩ ሲፈጠር ዝም ብዬ ተመልክቻለሁ በሚል አይደለም። ምንም እንኳን ሀሳብና ሙያዊ አስተያየቴ ተቀባይነት ባያገኝም የምችለውን ያህል በሰነድ አስደግፌ ዛሬ ላይ የሚታዩ ችግሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ለማስረዳት በእጅጉ ታግያለሁ፡፡

ሆኖም እንደ አንድ ባለሙያ በወቅቱ የነበሩትን የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ኃላፊዎች እና ባለሥልጣኖች፤ እንዲሁም የመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎችን (የወቅቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ጨምሮ) አሁን እንደተሠራው እንዳይሠራ ማሳመን አልቻልኩም። በዚህ መልኩ ማሳመን ላለመቻሌ ደግሞ፣ ምናልባት ጉዳዩን ለማስረዳት የሞከርኩበት መንገድ ውስንነት ስለነበረበት ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህ ባለፈ ግን በወቅቱ አወቅሁ አወቅሁ ባዮች፣ እንዲሁም የወራት የሙያ ሥልጠና ወስደው ራሳቸውን እንደ ብቁ የዘርፉ ባለሙያ አድርገው የሚመለከቱ ተፅዕኖ ፈጣሪነትን የተላበሱ የሙያም፣ የሥራም ኃላፊዎች በመብዛታቸው ነው ሀሳቤ ተቀባይነት እንዳያገኝ መሆኑ። ይሄ በመሆኑ ምክንያት ዛሬ ላይ በግልጽ እንደሚታየው ፕሮጀክቱ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ያሉበት ሆኖ ተተግብሯል። በፕሮጀክቱ ዙሪያ የሚታዩ (የዲዛይን ችግር፣ ከከተማዋ ፕላን፣ ገጽታ እና ውበት፣ በጥቅሉም ከከተማዋ የእድገት ፍላጎት ጋር ላለመጣጣሙ) ችግሮች ለመፈጠራቸው ቀዳሚ ተጠያቂዎችም እነዚሁ አካላት ናቸው፡፡

ምክንያቱም፣ እንደ እኔ ሀሳብ በዋናነት ኢምቤድድ ኮንክሪት የሚባለው ወይም ከአስፋልቱ እኩል በተሠራ እና ሐዲዱ በመሬት የተቀበረ እንዲሆን ነው ምክረ ሀሳብ ያቀረብኩት። ፕሮጀክቱ ውጤታማ እና ጥሩ የሚሆነው እንደዛ ቢሆን ነበር። ነገር ግን በወቅቱ የሚሰማ ባለመኖሩ ከዲዛይንም፣ ከከተማ ገጽታም፣ ከደኅንነትና ሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች አኳያ የሚነሱ ችግሮች ሊከሰቱ ችለዋል። እነዚህ ሊከሰቱ እንደሚችሉም እአአ በ2017 ላይ ለምድር

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “የከተማዋ የቀላል ባቡር መስመር ኮንቬንሽናል. . .

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

ባቡር ኮርፖሬሽን ባቀረብኩት ሪፖርት ጭምር በግልጽ አመላክቼ ነበር። ነገር ግን አልተተገበረም፡፡

ለምሳሌ፣ የባቡሩ ሐዲድ 70 በመቶ ወይም 25 ኪሎ ሜትር የሚሆነው ጠጠር፤ 25 በመቶ የሚሆነው ደግሞ በኮንክሪት ነው የተሠራው። ነገር ግን በየትኛውም ከተማ የሚገነባ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት ሐዲዶች በኮንክሪት ነው የሚሠሩት። ይሄ በሕንድና ቻይናም ሆነ በሌሎች ያደጉና ቴክኖሎጂውን ተጠቃሚ በሆኑ ሀገራት የሚታይ ነው። ይሄ ሲሆን ሐዲዱ በመሬት ውስጥ ያለ እንደመሆኑ በላዩ ላይ መኪና መሄድ ይችላል። ለተጨማሪ የውበት ሥራዎችም ይመቻል፡፡

በአዲስ አበባ ባለው ሁኔታ ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው 75 በመቶው በጠጠር የተከናወነ፤ ይልቁንም ኮንቬንሽናል የሀገር አቋራጭ የጠጠር መንገድን ነው ለከተማው የተተገበረው። ይሄ ደግሞ ከፍ ያለ የአደጋ ተጋላጭነትን የሚፈጥር ነው። ምክንያቱም ጠጠር የበዛበት መስመር አንድም የጥራት ችግር ያለበት እንደመሆኑ ለተደጋጋሚ ጥገና የሚዳርግ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከደኅንነት አኳያ የባቡሮቹ እንቅስቃሴ እና ፍጥነት ይገድባል፤ የአደጋ ተጋላጭነትንም ያስከትላል፤ የባቡር መሠረተ ልማቶች በቀላሉ እንዲጎዱ እና እንዲሰረቁም ያደርጋል። በተደጋጋሚ የባቡር መስመሮች ኬብሎች ስርቆት ሲካሄድ የሚታየውም ከዚሁ ለአደጋ ተጋላጭነቱ ጋር በተያያዘ ነው።

ከዚህ ባሻገር ድልድዮች የበዙበት እንደመሆኑ አንድም ለከተማዋ ገጽታ፤ ሁለተኛም ለጥገናና መሰል ተግባራት ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ነው። ለዛም ነው ዛሬ ላይ የከተማዋን ገጽታ ከማበላሸት አንጻር የሚነሱ ችግሮች የታዩት። ለምሳሌ፣ መስቀል አደባባይ ጋ ያለው ድልድይ የአከባቢውንም፣ የከተማዋንም ገጽታ በእጅጉ የጎዳ ነው። በሌሎች አካባቢዎች ያሉ ያለአግባብ የተደረደሩ ድልድዮችም የዚሁ የከተማ ገጽታ አጠልሺዎችም፤ ያልተገባ የጥገና ወጪ አስከታዮችም ናቸው፡፡

እነዚህ እና ሌሎች የሚጠቀሱ የፕሮጀክቱ ትግበራ የወለዳቸው ችግሮች ምክንያት ዛሬ ላይ ከከተማዋ ውበት፣ ከነዋሪዎቿ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አኳያ፣ እንዲሁም ከሌሎች ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አንጻር፤ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎቱ እንኳን የታሰበለትን ግማሽ ያህል እንኳን አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ሆኗል፡፡

ምንም እንኳን በትግበራ ሂደቱ እንደ አማካሪ ባለሙያ እነዚህ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ከማሰብ አንጻር ሙያዊ ሀሳቤን ሳጋራ የሚሰማኝ ያላገኘሁ እና ስናገራቸው የነበሩ ችግሮች የተፈጠሩ ቢሆንም፣ ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ከዚህ ውጪ ባለው ጉዳይ ግን የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት መስመርና መሠረተ ልማት መዘርጋቱን በጣም የምደግፈው ነው። ምክንያቱም ቢያንስ ቴክኖሎጂውን አስተዋውቋል፤ አዳዲስ እይታዎችን አምጥቷል፤ ከሰው ኃይል ልማቱም አኳያ የእውቀት ሽግግርን አስገኝቷል ማለት ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከመሠረተ ልማት ዝርጋታው ጋር አብሮ የሚነሳው የዲዛይን እና የባቡሮቹ ጉዳይ ነው፤ በዚህ ላይስ የእርስዎ ምልከታ ምንድን ነው?**

**ኢንጂነር አስረስ፡-** እርግጥ ነው የመሠረተ ልማት ግንባታው ውጤታማነት ከዲዛይኑ ይጀምራል። እኔ እንደ አማካሪ የባቡር መስመሩ ግንባታ ሂደትን ከተወሰኑ ድልድይ ከሚያስፈልጋቸው ወንዞች እና የዋሻ ውስጥ መስመሮች ውጪ በኮንክሪት እንዲሆን ነበር ያቀረብኩት። ከዚህ በተቃራኒው ግን 75 በመቶውን ጠጠር አድርገው፣ ለቁጥር የሚታክቱ ረዣዥም ምሰሶዎች የተደረደሩባቸው ድልድዮችን ተጠቅመው ነው የሠሩት። ይሄ ደግሞ ቀደም ሲል እንዳነሳሁት የራሱ ዘርፈ ብዙ ችግሮች አሉት፡፡

በኮንክሪት የሚሠራው መስመር ሲጀመር በጠጠር ከሚሠራው አኳያ ሲታይ ውድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከሚያስገኘው ጥቅም አንጻር ሲታይ እጅጉን አዋጪነት ያለው ነው። ይሄንን በሌሎች ሀገራትም ማየት ይቻላል። ከደኅንነትም፣ ከውበትም፣ ከዲዛይን ሳቢነትም፣ ለብልሽት ካለመጋለጡ እና ብልሽት ቢያጋጥመው እንኳን በቀላሉ መጠገን የሚችል ነው። ለዚህም ነው በሀገራት ዘንድ ከጠጠሩ ይልቅ የኮንክሪቱ ቴክኖሎጂ ነው ተመራጭ የሚሆነው፡፡

በዋናነት የባቡር መስመሩ ግንባታ የሚከናወነው በመሬት ላይ (at grade)፣ ከመሬት በታች (below grade) እና ከመሬት በላይ (above grade) ሲሆን፤ የአዲስ አበባው ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ትግበራ ደግሞ በመስመሩ ላይ ትንንሽ ድልድይ ከሚፈልጉ ማቋረጫዎች በስተቀር ይህ ነው የሚባል ወንዝ ወይም ሸለቆ የለም። የሚገነባው የመሬት ውስጥ ዋሻም በጠቅላላው አንድ ኪሎ ሜትር አይሞላም።

**ከከተማዋ ውበት፣ ከነዋሪዎቿ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አኳያ፣ እንዲሁም ከሌሎች ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አንጻር፤ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎቱ እንኳን የታሰበለትን ግማሽ ያህል እንኳን አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ሆኗል**

በመሆኑም ሐዲዶቹን በመሬት ውስጥ ቀብሮ በኮንክሪት ነበር መከናወን የነበረባቸው፡፡

በተመሳሳይ፣ ለባቡሩ ጐታቾችና ሌሎች አካላት ፍተሻና ጥገና አገልግሎት የሚሰጡ ሁለት ትልልቅ ጋራዦች እንዲኖሩት ታስቦ ነው ዲዛይኑ የተዘጋጀው። ከኃይል ፍላጎት አኳያም ቀደም ሲል የባቡሮቹ የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀም በ1ሺህ 500 ዲ.ሲ እንዲሆን ነበር የታቀደው። በኋላ ግን በመስመር ዝርጋታው ወቅት በተፈጠረ ችግር ምክንያት ወደ ሦስት ሺህ ዲ.ሲ (በእጥፍ) ከፍ እንዲል አድርጎታል። ይሄ ደግሞ መስመሩ ውጣ ውረድ ያለበት በመሆኑ የመጣ ሲሆን፤ ከፍ ያለ የኤሌክትሪክ ፍጆታም እንዲጠይቅ አድርጎታል።

ከኃይል ፍጆታው ባለፈ፣ ባቡሮቹ በተቀመጠላቸው የፍጥነት ወሰን እንዳይጓዙ እና በታሰበላቸው ሰዓት በየፌርማታዎች ደርሰው ተሳፋሪዎችን እንዳያጓጉዙ እንቅፋት ሆኗል። ለምሳሌ፣ በዲዛይኑ መሠረት ባቡሮቹ በሰዓት እስከ 80 ኪሎ ሜትር እንዲጓዙ ነው የታሰበው። ነገር ግን አሁን ባለው ትግበራ ብዙ ውጣ ወረድን ማለፍ ስለሚጠበቅባቸው እና ከመንገዱ ጥራት አኳያም ባለ ችግር ምክንያት እጅጉን ከዚህ ባነሰ ፍጥነት ለመጋዝ አስገድዷቸዋል፡፡

የባቡሮቹን ጉዳይ የሚመለከተውም ከዚህ የተለየ አይደለም። ምክንያቱም የባቡር ፉርጎዎች እንዲገዙ ሲታሰብ የከተማዋን የትራንስፖርት ፍላጎት ማዕከል ባደረገ መልኩ ነው። ለምሳሌ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የሚጠቀሙባቸው ዋና ዋናዎቹ የሕዝብ ትራንስፖርት መገልገያዎች አንበሳ የከተማ አውቶቡስ፣ መካከለኛ አውቶቡስ (ሀይገር ባሶች)፣ ሚዲባስ ታክሲዎችና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ የግል አውቶቡሶችና ሎንቺናዎች ናቸው። በወቅቱ ፕሮጀክቱ ሲታሰብ እነዚህ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ የሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች የባቡር ፕሮጀክቱ በታሰበበት መስመር በቀን ምን ያህል ሰው እንደሚያጓጉዝ ለመለየት ተሞክሯል፡፡

ከዚህ አኳያ በ2001 ዓ.ም ቀላል ባቡሩ በሚያልፍባቸው መስመሮች ላይ በእነዚህ የብዙኃን ትራንስፖርቶች አማካኝነት ይጓጓዛሉ ተብሎ የተለዩ የተጓጓዦች ብዛት (በቀን) ይፋ ተደርጓል። በዚህም መሠረት፣ ሚዲባስ ታክሲ - 516 ሺህ 560፣ መካከለኛ የከተማ አውቶቡስ - 326 ሺህ 118፣ የአንበሳ የከተማ አውቶቡስ - 97ሺ 306፣ እንዲሁም ሌሎች ድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶች - 331 ሺህ 344፣ በድምሩ አንድ ሚሊዮን 271 ሺህ 328 ሰዎችን ያጓጉዛሉ፡፡

የቀላል ባቡሩ ተግባራዊ ሲሆን ደግሞ በዚህ መስመር ይጓጓዛል ተብሎ የሚታሰበውን መንገደኛ በማጓጓዝ ሂደት ተጨማሪ አቅም ሆኖ፤ የመንገደኞችን እንግልት ቢቻል ያስቀራል፣ ባይቻል ግን ይቀንሳል፤ የትራፊክ ፍሰቱንም በእጅጉ ያሳልጣል የሚል ነው። ለዚህ ደግሞ 286 ተሳፋሪዎች በአንድ ጊዜ የመጫን አቅም ያላቸው የባቡር መኪኖችን በመጠቀም፤ በሰዓት በአንድ አቅጣጫ ብቻ 20 ሺህ ሰዎችን የማጓጓዝ አቅም ያላቸው 70 ባቡሮችን(ፉርጎዎች) አገልግሎት ላይ ለማዋል ነው የታቀደው። ለዚህ ደግሞ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያካሄደው ጥናት ትልቅ ግብዓት(ሪፈረንስ) ሆኖናል። ሆኖም ይሄም በሚታወቅ መልኩ ባስቀመጥነው ዲዛይን መሠረት ተፈጻሚ አልሆነም፡፡

ነገር ግን በአንድ በኩል ከዲዛይኑ ጋር በተያያዘ በተፈጠረ ችግር፤ ሁለተኛም ከባቡሮቹ ጋር ባለ የአስተዳደርም ሆነ የተገቢነት ጉዳይ ጋር የታዩ ችግሮችን ተቀብሎ ለማረም ዝግጁነት በመጥፋቱ ምክንያት የታሰበው ሳይሆን ቀርቶ፤ ሌላ ተጨማሪ የእንግልትም፣ የትራፊክ ፍሰት መስተጓጎል ምክንያት ሊሆን ችሏል። ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ከ18 ያልበለጡ ፉርጎዎች በአዝጋሚ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጡ እና ለመንገደኞችም የእንግልትና የቅሬታ ምንጭ ሆነው የሚገኙት። ይሄ እንዲሆን ከአስተዳደር፣ ከሰው ኃይል ሥልጠና እና ሌሎች ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ችግሮች ሊነሱ ይችላሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በእርስዎ የሚገለጹት እነዚህ ችግሮች በወቅቱ በሌሎች ባለሙያዎች አይታወቁም ነበር? በወቅቱ የእርስዎ ሀሳብ ተቀባይነት ቢያገኝ እና ቢተገበር ዛሬ ላይ የሚታየው ችግር አይፈጠርም ብለው ያምናሉ?**

**ኢንጂነር አስረስ፡-** እኔ እስከማስታውሰው፣ በወቅቱ የተለየ አቋም ይዤ ስከራከር የነበርኩት እኔ ብቻ ነበርኩ። ምክንያቱም በወቅቱ ሁሉም የኃላፊዎችን ፍላጎት፣ የፖለቲካውን ስሜት እያዳመጠ የሚራመድ ነበር። እናም እንዳልኩህ የእኔም ሀሳብ ተቀባይነት አላገኘም። በዚህ የሀሳብ ሙግቴ የተነሳም በተፈጠረብኝ ጫና ድርጅቱን ለቅቄ እስከመሄድ ደርሻለሁ። ምክንያቱም በወቅቱ ያሰቡትን እንድትቀበል እንጂ ያንተን ሙያዊ ሀሳብ ለመቀበል የተዘጋጀ አልነበረም። ለዛም ነው ጫናው ሲበዛብኝ ለቅቄ ለመሄድ የወሰንኩት።

ሆኖም ተቀባይነት ቢያገኝና እና ቢተገበር ኖሮ ዛሬ ላይ በዘርፉ የሚታየው ችግር አይፈጠርም ብዬ ልሟገት አልፈልግም። ልከራከርም ብል እውነትን መካድ ነው የሚሆነው። ምክንያቱም የትኛውም ሥራ ዜሮ ችግር (ከእንከን የፀዳ) አይሆንም፤ ሁሌ ችግር ይኖራል። ነገር ግን ችግሩን በጣም መቀነስና ማቅለል ይቻል ነበር። ሀሳብ የማድመጥ እና የሀሳቡን ፍሬ ተመልክቶ መተግበር ቢቻል ኖሮ ችግሩን በጣም መቀነስ ስለሚቻል በዚህ ልክ አፍጥጦ የማኅበራዊም፣ ኢኮኖሚያዊም ችግርነቱ ገንግኖም አይወጣም ነበር። ይሄ በመሆኑም ዛሬ ላይ እንደ አንድ ሀገሩን እንደሚወድ ሰው ቁጭት ይሰማኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ ይሄንን ችግር ለማቃለል፤ የባቡር መስመሩና ተያይዘው ያሉ ጉዳዮች (በከተማዋ ውበትና ዲዛይንም ሆነ በከተማዋ ነዋሪዎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚፈጥሩትን ከፍ ያለ እንከን) በምን መልኩ ማረም ይቻላል? የማረም ሂደቱስ ቀላል ይሆናል ብለው ያምናሉ?**

**ኢንጂነር አስረስ፡-** አዎ የሚቻልባቸው ዕድሎችም፣ አሠራሮችም አሉ። የማረም ሂደቱም ለማረም እንደምንከተለው መንገድ ቀላልም ከባድም ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ይሄንን ችግር የማቃለል ሂደት፣ የባቡር መስመሩና ተያይዘው ያሉ ችግሮች በከተማዋ ውበትና ዲዛይንም ሆነ በከተማዋ ነዋሪዎች ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚፈጥሩትን ከፍ ያለ ችግር በልኩ ከመገንዘብ ይጀምራል። ቀጥሎም ችግሩ እንዴት ይፈታል የሚለውን በጥናትም፣ በባለሙያ ምክርና ሀሳብም ማዳበር ይገባል። ከዚህ በተጓዳኝ የቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስና ተያያዥ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችል ስልት መንደፍ ይገባል፡፡

ለምሳሌ፣ እኔ እንደ አንድ በዘርፉ የትምህርት ዝግጅትም፣ ሰፊ የሥራ እና የፕሮጀክቶች አስተዳደር ልምድ እንዳለው ግለሰብ አሁን ላይ የሚታዩ ችግሮችን ማረም የሚቻልባቸው ሁለት መንገዶች ይታዩኛል። እነዚህ መንገዶች ግን ከፋይናንስም፣ ከዘላቂነትም አንጻር አዋጪነቱን መመልከቱ የተገባ ነው።

በዚህ ረገድም እአአ በ17/08/2011 ዓ.ም ላይ ለምድር ባቡር ያቀረብኩት ምክር እንደ አንድ አማራጭ ሊወሰድ ይችላል። ይሄ ደግሞ ዛሬ ላይ ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነውን በጠጠር የተሠራ እና ድልድይ የበዛበትን መንገድ በኮንክሪት መቀየር ነው። ቀደም ብዬ እንዳነሳሁትም በኮንክሪት የሚሠራው የቀላል ባቡር ሃዲድ በጠጠር ከሚሠራው ጋር ሲነፃፀር በትንሹ ዋጋው የሚጨምር ቢሆንም፣ ከሚያስገኘው ጥቅም እና ከዘላቂነቱ/ቆይታው አንፃር በበርካታም ሀገሮች ተመራጭ ነው። የኮንክሪት ሐዲድ ከብናኝና ከድምፅ ብክለት ነፃ ነው፤ ለዕይታ ማራኪ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ለብልሽት አለመጋለጡና ብልሽት ቢያጋጥም እንኳን በቀላሉ የሚጠገን በመሆኑም ከወጪ አኳያ አዋጭ ነው።

ሌላኛው አማራጭ ደሞ፣ አሁን የተሠራውን አፍርሶ ከመሬት በታች የሚሄድ ሜትሮ መሥራት ነው። ይሄ ደግሞ ወጪው ከባድ ነው። የከተማዋ የመሬት ሁኔታ እና ሌሎችም ምክንያቶች ለቦርቧሪ ማሽኑ ፈታኝ ስለሚሆኑም የዋሻ ፍልፈላ ሂደቱን እንዲዘገይ ሊያደርጉትም ይችላሉ። በእነዚህ ምክንያቶችም የግንባታ ወጪው በኪሎ ሜትር ከ40 እስከ 50 ሚሊዮን ዶላር ይሆናል። ከዚህ አኳያ የኔ ምርጫ እንዳለ አፍርሶ የኮንክሪት መስመሩን (Embedded Rail System / Advanced Urban Slab Track System) መሥራቱ የተሻለ መሆኑን ለመጠቆም እወድዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ከእርስዎ የሙያ አቅምም ሆነ የሥራ ልምድና ተሞክሮ አኳያ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ ምን መሠራት ይኖርበታል ይላሉ? ለሚመለከታቸውስ ምን ይመክራሉ?**

**ኢንጂነር አስረስ፡-** የታዩ ችግሮችን ለማረም ገንዘብ ካለ ቀላል ነው። የግንባታና ቴክኖሎጂ ጉዳዮችን በተመለከተም ልምዱ ስለተገኘ ብዙም የሚቸግር አይሆንም። ዋናው ጉዳይ የፕሮጀክት አዋጭነትና የፋይናንስ ምንጩን በአግባቡ መለየቱ፤ መንግሥት አቋም መያዙ ላይ ነው። ይህ እንዲሆን ደግሞ የመጀመሪያው ምክሬ ሥራዎችን ለመሥራት ሲታሰብ በተለይ እንዲህ አይነት ዘላቂ የሆኑ ፕሮጀክቶች ሲተገበሩ፣ ጥናት ማድረግ እና በዘርፉ ልምድና እውቀት ካላቸው ባለሙያዎች ጋር መመካከር ተገቢ መሆኑን ነው። በምክክር ሂደት የሚመጡ ማናቸውም ሀሳቦች የየራሳቸው ምልከታ ስላላቸውም በአግባቡ ታይተው ሊወሰዱ ያስፈልጋል፡፡

አሁን ላይ በአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በማረም ሂደትም ይሄን መሰል አካሄድ መከተል ከተቻለ ቀላል ነው። ምክንያቱም የተሠራውን የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ችግር ስላለበት ብቻ ዝም ብሎ (spontaneously) ማፍረሱ አዋጭ አይሆንም። ምንም እንኳን የተሠራው የከተማዋን ውበት ያበላሸ፤ በአተገባበሩም ቀላል ባቡር ሳይሆን ኮንቬንሽናል (conventional) የሀገር አቋራጭ የጠጠር መንገድ ቢሆንም፤ እንዴት እናሻሽለው ወይም እንለውጠው ብሎ ባለሙያዎችን ማማከር እና የከተማዋን ገጽና ስም በሚመጥን መልኩ መከወን ይገባል፡፡

ከዚህ ውጪ ግን ዘርፉን በዘላቂነት ማሳደግ እና የቴክኖሎጂ አቅም አንድ ማዕከል አድርጎ መሥራት ይገባል። ምክንያቱም፣ ኢኮኖሚያቸው በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ውስጥ የከተማ ቀላል ባቡርን ኢምፖርት በማድረግም ይሁን በጨረታዎች ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለአጭር ጊዜ የሚተገበር ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኢኮኖሚያቸውም ፍላጎታቸውም በፈጣን መንገድ ላይ ያሉ ሀገራት በጠንካራ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ የታገዘ ሥራን መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይሄ ግን ቴክኖሎጂውን አቅራቢ ከሆኑ ሀገራት ከፍ ያለ ጫና ሊስከትል የሚችል ቢሆንም፤ የመንግሥት ቁርጠኝነት ታክሎበት ቀደም ሲል ሲከናወኑ እንደነበሩ ቴክኖሎጂዎችን አስገብቶ ከመገጣጠም፣ ከመቅዳትና ከማላመድ ጋር የተገናኙ አካሄዶችን በመጠቀም ሊታለፍ የሚችል ነው። ለምሳሌ፣ የቀላል ባቡሩን ዲዛይን ሲዘጋጅ የቻይናን እቃ መጠቀም በሚያስችል መልኩ ነው። በመሆኑም የቀላል ባቡሩን ችግሮች በማረም ሂደት የቻይናውን ዲዛይን መከለስ ከተቻለ የሀገር ውስጥ ቴክኖሎጂንም መጠቀም የሚቻልበትን ዕድል ይሰጣል፡፡

ይሄን ማድረግ ከተቻለም በሀገር ውስጥ የባቡር ቴክኖሎጂን የማዳበር አማራጭ ወደ አገልግሎት ጥራት እና ምናልባትም ከፍተኛ የመጓጓዣ ወጪዎች ማዳን ደረጃ ሊተረጎም ይችላል። ለዚህ ደግሞ ቻይና እና ሕንድ ዐቢይ ማሳያዎች ናቸው። ሁለቱም ሀገራት ለከተማ ባቡር ልማት ትልቅ ገበያ አላቸው፤ የባቡር ቴክኖሎጂን ሀገር በቀል ለማድረግ የኢንዱስትሪ ፖሊሲን አውጥተዋል።

ቻይና ከውጪ ከማስገባት ወደ ሀገር በቀል የሆነ (በራስ አቅም የተሠራ) የከተማ ባቡር ቴክኖሎጂ የተሸጋገረችበትን ስኬት በተሳካ ሁኔታ ስታስተዳድር፤ ሕንድ በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥ ምርትን ለመጨመር እና ለከተማ ባቡር ልማት በጣም ተለዋዋጭ ከሆኑት ገበያዎች ውስጥ አንዱን በሕንድ የተሠራ (Made in India) ስትራቴጂ በመከተል ላይ ትገኛለች። የእነዚህ ሁለቱ ሀገራት ልምድ ኢትዮጵያም የትራንስፖርት ችግሮቿን ለመቅረፍ በኢንዱስትሪ ፖሊሲ የተመራ የከተማ ባቡር ትግበራን ሀገር በቀል ለማድረግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ከዚህ አኳያ የመንግሥት ኃላፊዎችም ሆኑ ዘርፉን የሚመሩ አካላትም እንዲህ አይነት አማራጮችን ማሰብ ይኖርባቸዋል፡፡


**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ስለተባበሩኝ ለጊዜዎም ለሀሳብዎም አመሰግናለሁ!**

**ኢንጂነር አስረስ፡-** እኔም ሀሳቤን እንዳካፍል ዕድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ!

# ማህደረ ጤና

# የሳምባ ካንሰርን ለመከላከል ቅድመ ምርመራና ክትትል

**አስናቀ ፀጋዬ**




**በኢትዮጵያ ከ80 በመቶ የሚልቁ የሳምባ ካንሰር ተጠቂዎች በጣም ዘግይተው ወደ ሕክምና ተቋማት እንደሚመጡ ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህም የሳምባ ካንሰር ምልክቶች ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑንና የቅድመ ምርመራና ክትትል ትግበራ እንደሀገር ያልዳበረ መሆኑን ይጠቁማል**

የሳምባ ካንሰር በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፋት ከሚታወቁ የካንሰር አይነቶች አንዱ ነው። በካንሰር ምክንያት ከሚከሰት የሞት ምጣኔ ውስጥም በቀዳሚነት ይቀመጣል። የሳምባ ካንሰር ሕክምና ውጤታማነት ካንሰሩ በታወቀበት ግዜ ካለው የስርጭት ደረጃ ጋር በቅርበት የተቆራኘ መሆኑንም ነው የዘርፉ ሕክምና ባለሙያዎች ያረጋገጡት። ይህም ማለት ሕመሙ በእንጭጭነቱ ወይም ወደተቀረው የሰውነት ክፍል ከመዛመቱ በፊት መለየት ከተቻለ የታካሚውን ሕክምና ውጤት በእጅጉ ማሻሻል እንደሚቻልም ነው ባለሙያዎች የሚጠቁሙት።

በኢትዮጵያ ከ80 በመቶ የሚልቁ የሳምባ ካንሰር ተጠቂዎች በጣም ዘግይተው ወደ ሕክምና ተቋማት እንደሚመጡ ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህም የሳምባ ካንሰር ምልክቶች ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑንና የቅድመ ምርመራና ክትትል ትግበራ እንደሀገር ያልዳበረ መሆኑን ይጠቁማል። በኢትዮጵያ የሳምባ ካንሰር ምጣኔ እየጨመረ መምጣቱን አመላካች ጥናቶች መኖሩን ታሳቢ በማድረግ የሳምባ ካንሰር ቅድመ ምርመራና የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ያመለክታል።

ይህንኑ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው የዓለም የሳምባ ካንሰር ቀን በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ግዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ13ኛ ግዜ ‹‹ግንዛቤ ከመፍጠር ወደ ተግባር!›› በሚል መሪ ቃል በኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲ አስተባባሪነት ከጤና ሚኒስቴርና ከማቲዎስ ወንዱ ኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ጋር በመተባበር ባሳለፍነው ሐምሌ ወር መጨረሻ የተከበረው።

የኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ራሔል አርጋው እንደሚናገሩት፣ በብሪስቶል ማየርስ ስኩዊብ ፋውንዴሽን /BMSF/ ድጋፍ የሳምባ ካንሰር ተጋላጭነትን በመፈተሽ የቅድመ ልየታና ክትትል ሥራ ከአራት ዓመት በፊት አዲስ አበባን ጨምሮ በኦሮሚያ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች በተመረጡ የጤና ተቋማት ተጀምሯል። በነዚህ ተቋማት ላይ ግንዛቤ የመፍጠር፣ የጤና ባለሙያዎችን አቅም የማሳደግና ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር የተጣጣሙ ሳይንሳዊ ጥናቶችን የማመንጨት ሥራዎች ተከናውነዋል።

በኢትዮጵያ የሳምባ ካንሰር ላይ የምርምርና ጥናት ውጤቶች ውስንነት በመኖሩ የኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲ በዘርፉ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መሥራት ይፈልጋል። የዓለም የሳምባ ካንሰር ቀን በኢትዮጵያ ሲከበር በሳምባ ካንሰር ላይ እየተጠኑ ያሉ የጥናት ግኝቶች ቀርበዋል። በጥናቶቹ ላይም ውይይት ተደርጓል። ዓውደ ጥናት ተዘጋጅቷል። በዓውደ ጥናቱም ተመራማሪዎች፣ የጤና ባለሙያዎችና ፖሊሲ አውጪዎች በኢትዮጵያ ባለው አሁናዊ የሳምባ ካንሰር ገፅታ ላይ ምክክር አድርገዋል። የዚሁ መርሐ ግብር ዋነኛ ዓላማም የዓለም የሳምባ ካንሰር ቀንን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ስላለው የሳምባ ካንሰር ገፅታ፣ የሕክምና ሁኔታና ተግዳሮቶች ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው።

የኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲ ግንዛቤው ያለው ሁሉም ሰው ለሳምባ ካንሰር የሚያጋልጡ የግል ባሕሪና የአኗኗር ዘይቤ መረጃን በመለዋወጥ ረገድ ንቁ ሚና እንዲጫወቱ ያበረታታል። ሲጋራና ሺሻ ማጨስ፣ ለከባድ ጭስና ጥቀርሻ ያለ ተጋላጭነት፣ በሥራ ቦታ ለመርዛማ ብናኞች/ንጥረ ነገሮች መጋለጥና ስር የሰደደ የመተንፈሻ አካላት በሽታ ታማሚ መሆን በጥናት የተለዩ የሳምባ ካንሰር አጋላጭ መንስኤ በመሆናቸው ቅድመ ምርመራና የሕክምና ክትትል ማድረግ፣ የባሕሪ ለውጥ ማድረግ በሽታውን በመከላከልና በመግታት ሂደት ውስጥ ጉልህ ሚና አለው።

ፕሬዚዳንቷ እንደሚያብራሩት፣ በኢትዮጵያ ከ6 እስከ 10 በመቶ የሚሆነው ሞት የሚከሰተው በካንሰር ምክንያት ነው። የካንሰር ሕክምና ተደራሽነት አናሳ መሆን ደግሞ ለዚህ አንዱና ቁልፍ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል። በዚህ ምክንያት 15 ከመቶ ወይም 80 ሺ የሚሆኑት ብቻ የካንሰር ሕሙማን የሕክምና አገልግሎት ያገኛሉ። ይህን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የጤና ሚኒስቴር ስትራቴጂክ እቅድ በመንደፍ እንዲሁም ለሳምባ ካንሰርና ሌሎች ካንሰሮች የሚሆን ሕክምና መመርመሪያ መምሪያዎችን በመቅረፅ በሽታውን ቅድመ ልየታና ሕክምና አገልግሎት ለማዳረስ እየሠራ ይገኛል።

ከነዚህ ውስጥ አንዱ የኬሞቴራፒ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ቁጥር በመጨመር ወደ 30 በሚሆኑ ሆስፒታሎች ሕክምናውን መሰጠት መቻሉ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ከካንሰር ሕክምና ውስጥ አንዱ የሆነውን የጨረር ሕክምና አገልግሎት ለማስፋት ባለፉት ዓመታት የሬዲዮቴራፒ አገልግሎትን ከ1 ወደ 7 ማሳደግ ተችሏል። ይህም ሚዛናዊ በሆነ ስርጭት በአዲስ አበባ 2 ተቋማት ላይ እንዲሁም በሌሎች ክልል ከተሞች 5 ማዕከላት ላይ ተስፋፍቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

የጤና ሚኒስቴርም በካንሰር ሕክምና ላይ ያለውን የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ የኪሊኒካል ኦንኮሎጂስቶችን ቁጥር ከነበሩበት 4 ወደ 50 ማሳደግ ችሏል። ከነዚህ ውስጥ 40 ያህሉ የስፔሺያሊቲ ትምህርታቸው እየተከታተሉ ይገኛሉ። የካንሰር መድኃኒት አቅርቦትንም ከግዜ ወደ ግዜ እያሻሻለ የመጣ ሲሆን አሁን ላይ የመድኃኒቶች ዋጋ ከ 60 በመቶ በላይ የሚሆነውን ወጪ በመሸፈን በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት በኩል ሕክምናውን ለሚሰጡ ሆስፒታሎች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

ከካንሰር ሕመም ጋር በተያያዘ ያሉ የመረጃ አቅርቦቶችን ለማሳደግ ጥራትና ተደራሽነት ያለው ሕክምና ለመስጠት እንዲረዳ ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ ብቻ የነበረው የካንሰር ሬጅስትሪ አሁን ላይ ወደ አምስት ሌሎች ተቋማት ለማዳረስ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

የማቲዎስ ወንዱ ኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ወንዱ በቀለ እንደሚሉት ተቋሙ ከጤና ሚኒስቴርና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ እየጨመረ የመጣውን የሳምባ ካንሰርን ለመቆጣጠር ሦስት ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ እየሠራ ይገኛል። ከሚተገብራቸው የተለያዩ ፕሮጀክቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ የሚያሳድጉ፣ ዘመናዊ ምርመራና ሕክምናን የሚያበረታቱና በኢትዮጵያ የሳምባ ካንሰርን የተመለከቱ ምርምሮችን የሚደግፉ ናቸው።

እነዚህ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ክልሎችና ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የሳምባ ካንሰር ሕክምናን ውጤታማ በማድረግ በማድረግ በኩል ሚናቸው ከፍ ያለ ነው። ተቋሙ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አጋላጭ የሆኑ መንስኤዎች ላይ የሚሠራ እንደመሆኑ ትምባሆ በዋናነት ለሳምባ ካንሰር እንዲሁም ለአብዛኛዎቹ ተላላፊ ላልሆኑ ሕመሞች አጋላጭ በመሆኑ ከጤና ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ሕግ እንዲወጣና ቁጥጥር እንዲደረግ በጋራ ሠርቷል።

በሌላ በኩል ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሳምባ ካንሰር ሕክምና ክፍልን በልዩ ልዩ መልኩ እንዲጠናከር አድርጓል። በቱሉ ቦሎ የኬሞቴራፒ ሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ አመቻችቷል። በአፋር ክልልም ለሳምባ ካንሰር ብቻ ሳይሆን በሌሎች ካንሰሮች ላይ ሕክምና እንዲጀመር ጥረት አድርጓል። ከጤና ሚኒስቴርና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ባለሙያዎች ተሰባስበው ሕሙማኖችን አይተው በየደረጃው ሕክምና የሚሰጡበት የመልቲ ዲስፕሊነሪ ቡድን በማቋቋም እየሠራ ይገኛል። ይህም ሕሙማን ሆስፒታል ከደረሱ በኋላ እንዳይጉላሉና ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ ትልቅ እገዛ አድርጓል። የሚሰጡ ሕክምናዎችና ልየታዎች በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መንገድ የሚሄድበትን ሁኔታ ለመፍጠርም እየሠራ ይገኛል።

በጤና ሚኒስቴር የካንሰር መቆጣጠርና መከላከል አማካሪ ዶክተር ኩኑዝ አብደላ በበኩላቸው እንደሚሉት የሳምባ ካንሰር ችግር ዋነኛ የጤና ችግር ነው። የካንሰር መርሐ ግብር ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ተቀርፆ ወደ ሥራ ሲገባ የተለዩ ዋና ዋና የካንሰር አይነቶች ነበሩ። ነገር ግን ከሰባት ዓመት በኋላ ያለው መረጃ ሲታይ የሳምባ ካንሰር ዋና ዋና ከሚባሉ አስር የካንሰር አይነቶች ውስጥ አንዱ ሆኗል። ይህ ማለት በሚፈለገው ልክ ሥራዎች ካልተሠሩ፣ አስፈላጊ የሆነ እርምጃ ካልተወሰደ በሽታው ደረጃውን እያሻሻለ ወደ ዋና የካንሰር አይነት ሊመጣ እንደሚችል ሁኔታዎች ያሳያሉ።

የመጀመሪያው የዓለም ሳምባ ካንሰር ቀን ከኢትዮጵያ ቶራሲክ ሶሳይቲና ከማቲዎስ ወንዱ ኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ጋር በመተባበር ሲከበር በጤና ሚኒስቴር በኩል የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ከነዚህ ውስጥ አንዱ በሳምባ ካንሰር ዙሪያ መረጃዎችን በሚገባ በማጠናቀር በሳይንሳዊ መንገድ የሳምባ ካንሰር መከላከያና ማከሚያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ችግሮችን ፍንትው አድርጎ እንዲያሳይ ማድረግ ነው። ከዚህ የሚገኘው መረጃ ወደፊት ሀገሪቱ በሳምባ ካንሰር ላይ የምትቀርፀውን የመከላከል፣ የማከም፣ የሕሙማን ማስተላለፍ፣ የክብካቤ ሥራ በመረጃ የተደገፈ ግብዓት እንዲገኝ ያግዛል። ይህ ግብዓት በፖሊሲ፣ አካሄድና ስትራቴጂ ላይ ለውጥና ውጤት እንዲመጣ ያስችላል።

በሌላ በኩል ትልቁ በሳምባ ካንሰር ላይ ያለው ችግር ያለው የግንዛቤ ክፍተት ከፍተኛ መሆኑን ነው። ከታች ካለው ማኅበረሰብ ጀምሮ እስከ ጤና ባለሙያዎች ድረስ ብሎም በጤና ሥርዓት ውስጥ የሳምባ ካንሰርን አክሞ ለማዳን ያለው የግንዛቤ ክፍተት ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ከፍ ያለውን ግንዛቤ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መለወጥ ያስፈልጋል። ኅብረተሰቡ ጋር እየደረሱ ያሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተግባራዊና የባሕሪ ለውጥ ማምጣት አለባቸው። በአጋላጭ ሁኔታዎች ላይ፣ አስቀድሞ በሽታውን በመለየት ላይ፣ ኅብረተሰቡ ወደ ሕክምና ተቋማት ቀርቦ የሳምባ ካንሰር ቅድመ ልየታና ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ሥርዓት የሚበጅበት ከመሆኑ አንፃር በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባ ጉዳይ ነው።

አማካሪው እንደሚገልፁት በሳምባ ካንሰር ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል። በተለይ ስለበሽታው ምንነት፣ ኅብረተሰቡ ራሱን ከዚህ በሽታ ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለበት፣ የእያንዳንዱ ኅብረተሰብና የጤና ባለሙያው ሚና ምን እንደሆነ፣ የፖሊሲ አውጪዎች ሚና ምን እንደሆነ በግልፅ ማስገንዘብ ይገባል። በዚህ ረገድ ደግሞ በተለይ የሚዲያ አካላት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። መረጃ ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ከሳምባ ካንሰር ጋር በተያያዘ ትክክለኛ መረጃ ማስተላለፍም ከሚዲያዎች ይጠበቃል።

የሳምባ ካንሰር ላይ ያለው ሌላኛው ዋና ችግር አብዛኛው የዚህ ካንሰር ተጠቂ የሆነ ሰው ወደ ሕክምና ቦታ በቶሎ አለመምጣቱ ነው። ይህም ታክሞ የማዳን ዕድሉን ያጠባል። በዚህም ምክንያት የሳምባ ካንሰር ሕክምና ውጤታማ አይደለም። ስለዚህ ይህን እንዴት አድርጎ መቀየር ይቻላል ነው ዋናው ጥያቄ። አብዛኛዎቹ በቶሎ እንዲመጡና በጣም ጥቂት የሚባሉት ደግሞ ወደኋላ ሕክምና ቦታ እንዲመጡ ከተቻለ አጠቃላይ የሳምባ ካንሰር የሕክምና ውጤትና ሁኔታ መቀየር ይቻላል።

ለዚህ ደግሞ በጣም ከፍተኛ የሆነ የመረጃ አሰጣጥና የመረጃ ፍሰት በደምብ ማስተካከል ይገባል። የሳምባ ካንሰርን በግዜ በመለየት ማከምና የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻላል። ከዚህ አንፃር ማኅበረሰቡ ካንሰርን እንደመጨረሻ የሞት ፍርድ አድርጎ መቁጠር አይገባም። ስህተቱ ማንም ጋር ይሁን አንድ ሕመምተኛ በግዜ ወደ ጤና ተቋም እስካልመጣ ድረስ ውጤቱ ምትሓታዊ ሊሆን አይችልምና ይህን ማስተካከል ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሳምባ ካንሰር የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንደሚፈልግ አውቆ መንቀሳቀስ የግድ ይላል። በዚህ ረገድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተገቢውን ሚና የመጫወት ኃላፊነትም አለባቸው። ይህን ማድረግ ከተቻለ በሳምባ ካንሰር መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ ውጤት ማምጣት ይቻላል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የሕክምና አገልግሎት ግብዓት ምርት- በሀገር ውስጥ በሀገር ልጅ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

መንግሥት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሰጠው ትልቅ ትኩረት በርካታ አምራቾች ዘርፉን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ። በዚህም የተለያዩ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት አበረታች ውጤት መመዝገብ እንደቻለም መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለይም ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት በመቻሉ ከውጭ የሚገባውን ምርት መጠን መቀነስ እንዲሁም ምርቱን ለማስገባት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት እየተቻለም ነው።

መንግሥት የዘርፉን ችግር እየገመገመ የአሰራር ማሻሻያዎች ሲያደርግ ፣ የዘርፉን የመሰረተ ልማትና የመሬት አቅርቦት ችግርም ለመፍታት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጭምር ገንብቶ በማቅረብ ለዘርፉ የበለጠ መስፋፋት ሰርቷል። ይህን ተከትሎም በርካታ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ገብተዋል፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የአምራች ዘርፉ ተሳትፎ ለማሳደግም ባከናወናቸው ዘርፈ ብዙ ተግባሮች የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የዘርፉ ተሳትፎ እየጨመረ መጥቷል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ተኪ ምርቶችን ለማምረቱ ስራ ትኩረት ተሰጥቷል። በተለይ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታወጣባቸውን መድኃኒቶች ጨምሮ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን ለሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች የቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክን በመገንባት ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ተከትሎ ኢንዱስትሪዎቹ መድኃኒትና የህክምና ቁሳቁስ ለማምረት ዘርፉን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ።

በዘርፉ የተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችም የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የህክምና ግብዓቶችን በማምረት ከውጭ ይገቡ የነበሩ የህክምና ቁሳቁስን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት በዘርፉ ለራሳቸውም ለሀገርም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ናቸው። የኢትዮጵያን የሕክምና አገልግሎት ግብዓት ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥም ሰፊ ሥራ መሰራቱም ይገለጻል፡፡

ይህን ሁሉ ስራ ተከትሎ ኢትዮጵያ አሁን ላይ 36 በመቶ ያህል የመድኃኒትና የሕክምና ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መሸፈን እንደቻለች መረጃዎች ያመላክታሉ። መንግሥት ለተኪ ምርት ልማት በሰጠው ትልቅ ትኩረት በመድኃኒትና የህክምና ቁሳቁስ ምርት ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ወጪን ማዳን እንደተቻለ መረጃዎች ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ በሕክምናው ዘርፍ ኢንቨስትመንት ያሏትን ዕድሎች መጠቀም በመቻሏ በአሁኑ ወቅት የህክምናው ዘርፍ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ጀምራለች። በመሆኑም በርካታ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም አነስተኛና መካከለኛ አምራቾች በሕክምና ግብዓት ማምረት ስራ በስፋት እየገቡ ነው። የህክምና ግብዓቶችን ወደማምረት ከተቀላቀሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል «ኤኬቢዲ ፋርማቲዩካል ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር» አንዱ ነው።

ድርጅቱ ከሚያመርታቸው የህክምናው ዘርፍ ምርቶች መካከል ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድኃኒት፣ ቅባትና ቅባት ነክ የሆኑ ምርቶች ይጠቀሳሉ። አብዛኞቹ ምርቶች ከውጭ ሀገር ይገቡ የነበረ ሲሆን፤ አሁን ግን ጥሬ ዕቃውን ብቻ ከውጭ በማስገባት በሀገር ውስጥ ማምረት ተችሏል። ድርጅቱ አልኮልም በግብአትነት በስፋት ይጠቀማል። ድርጅቱ በህክምና አገልግሎት ትልቅ ድርሻ ያለውን አልኮል በመጠቀም ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድኃኒት፣ ቅባትና ቅባት ነክ ምርቶችን እያመረተ ለገበያ ያቀርባል።

የኤኬቢዲ ፋርማሲቲዩካል ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መስራችና ባለቤት አቶ ብሩክ ዳምጠው በዘርፉ ከተሰማሩ ባለሙያዎች አንዱ ነው። አቶ ብሩክ ሲኒየር ኤክስፐርት ፋርማሲስት እና የድርጅቱ ቴክኒካል ማናጀር ነው። አቶ ብሩክ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት የተነሳው ሙያውን መሰረት በማድረግ እንዲሁም በዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመሙላት በማሰብ መሆኑን ይናገራል።

አዲስ አበባ ከተማ ሳሪስ አካባቢ ተወልዶ ያደገው አቶ ብሩክ፤ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንም በአዲስ አበባ ከተማ ተከታትሏል። የከፍተኛ ትምህርቱንም በሜድኮ ባዮ ሜዲካል ኮሌጅ ተከታትሎ




በፋርማሲስትነት ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። ከትምህርት በኋላ በአንድ ድርጅት ውስጥ የመድኃኒት አቅርቦት ባለሙያ በመሆን ተቀጥሮ ሰርቷል። በቅጥር ቆይታው ሙያውን ማዳበር የቻለው አቶ ብሩክ፤ በዘርፉ የበለጠ እየተሳበና ፍላጎት እያሳደረ በመምጣቱ አምራች የሚሆንበት ቀዳዳ ያማትር ጀመር።

በዚህ ጊዜ ለሙያው ከፍተኛ ተነሳሽነትና ውስጣዊ ፍላጎት እያሳደረ የመጣው አቶ ብሩክ፤ መንግሥት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እያደረገ ያለውን ድጋፍ ተረዳ። ፍላጎቱን ዕውን ለማድረግም ተቀጥሮ ከመሥራት ይልቅ ወደ አምራች ኢንዱስትሪው መቀላቀልን መርጦ ተቀላቀለ።

መንግሥት የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ከረጅም ጊዜ ጥናት በኋላ በ200 ሺ /ሁለት መቶ ሺ/ ብር መነሻ ካፒታል የማምረት ሥራውን ይጀምራል። ወደ ምርት በገባበት ወቅትም ሥራውን በሚገባ መሥራት በመቻሉ በብዙ እንደተማረበት እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገት በማስመዝገብ ውጤታማ መሆን ቻለ።

ይሁንና ካለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ወዲህ ሀገሪቷን ካጋጠሟት ግጭቶች ጋር በተያያዘ ሥራው ቀዝቀዝ ብሎ መቆየቱን አስታውሶ፣ በሀገሪቱ የተረጋጋ ሁኔታ መፈጠሩን ተከትሎ ጥሩ የሚባል የሥራ እንቅስቃሴ እያረገ መሆኑን አመላክቷል።

አቶ ብሩክ መድኃኒትን ጨምሮ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ምርቶችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች በቂ እንዳልሆኑ ጠቅሶ፣ በዘርፉ ብዙ መሥራት እንደሚያስፈልግም ጠቁሟል። ምክንያቱም በሀገሪቱ ያለው ፍላጎትና አምራች ኢንዱስትሪዎች እያመረቱ ያሉት የምርት አይነት መጠን ተመጣጣኝ አይደለም ባይ ነው።

«የኤኬቢዲ ፋርሽማሲቲዩካል ማኑፋክቸሪንግ በዋናነት ከሚያመርታቸው ምርቶች መካከል የወባ ትንኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መድኃኒቶች ይጠቀሳሉ። ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያትም በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የወባ ትንኝ ስርጭት በመኖሩ ነው» የሚለው አቶ ብሩክ፤ ለአፍ መጉመጥመጫ፣ ለጉንፋን፣ ለአዋቂና ለልጆች የሚሆን ለመገጣጠሚያና ለጡንቻ አካባቢ ህመም፣ ለድርቀት በተለይም ውሃ ላይ ለረጅም ጊዜ ለሚቆዩና በተፈጥሮ ድርቀት ላለባቸው ሰዎች የሚያገለግሉ ቅባቶች፣ የልጆች ቅባትና ፣ ቁስል ለማጽዳት የሚያገለግል ፈሳሽና ኮስሞቲክስ ጭምር እያመረተ መሆኑን አብራርቷል፡፡

እነዚህ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት አልኮል ወሳኝ ነው የሚለው አቶ ብሩክ፤ አልኮል እጅግ በጣም ብዙ ቦታዎች ላይ እንደሚገባ አስረድቷል።

እሱ እንደሚለው፤ አልኮል በጣም ወሳኝ የሆነ መቀላቀያ ነው፤ ምርቶቹ እንዳይበላሹ ማድረግ የሚያስችል ንጥረ ነገር ነው። ስለዚህ አልኮል ከሌለ አብዛኞቹ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት የሚቻል አይደለም። በሀገሪቱ የአልኮል ምርት እጥረት ተከስቶ እንደነበር አስታውሶ፣ በዚያን ወቅት እንደልብ ማምረት አልተቻለም ነበር ይላል። አሁን ላይ የአልኮል እጥረት መቀረፉን ጠቅሶ፣ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ምርቶች በጥሩ ሁኔታ እየተመረቱ መሆናቸውን አስታውቋል።

እሱ እንዳለው፤ ከዚህ ቀደም በርካታ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ምርቶች ከውጭ ይገቡ ነበር። አሁን ላይ አብዛኛውን ንጥረ ነገር ከውጭ በማስገባት ምርቶቹ በሀገር ውስጥ ይመረታሉ። ይህም ለዘርፉ ይወጣ የነበረውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ መቀነስ አስችሏል። አሁን ላይ ጥሬ ዕቃውን ብቻ ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ በርካታ ምርቶች አስፈላጊውን ሂደት ተከትለው በሀገር ውስጥ እየተመረቱ እንደሆነ አስረድቷል።

ያለቀለት ምርት የሚገባበት መጠንና ወጪ እንዲሁም ጥሬ ዕቃው የሚገባበት መጠንና ወጪ ከፍተኛ ልዩነት እንዳለው ነው አቶ ብሩክ የሚናገረው። ይህንንም ለአብነት ጠቅሶ ሲያብራራ፤ አንድ ኮንቴነር ያለቀለት ምርት ከማምጣት ይልቅ አንድ ኮንቴነር ወይም አንድ በርሜል ጥሬ ዕቃ ማስገባት በእጅጉ ተመራጭ ነው ይላል። ይህ ሲሆን ኢንዱስትሪው ጥሬ ዕቃውን ለረጅም ጊዜ ይጠቀምበታል፤ ብዙ ማምረትም ያስችለዋል ሲል ገልጾ፤ ይህም ለመጓጓዣና ለሌሎች በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚወጡ ወጪዎችን በእጥፍ መቀነስ ያስችላል ብሏል፡፡

ድርጅቱ ሥራውን ከጀመረ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል። ሥራው የተጀመረው ኮቪድ 19 ወረርሽኝ ከመከሰቱ አስቀድሞ ነበር። በወቅቱ ድርጅቱ ሳኒታይዘር በስፋት እያመረተ ለገበያ ያቀርብ ነበር። የኮቪድ 19 ወረርሽኝ እየቀነሰ ሲመጣ ከኮቪድ ውጭ ያሉና ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ምርቶችን በስፋት ማምረት ወደ ማምረቱ ገባ። በአሁኑ ወቅትም ምርቶቹን በተለያዩ ቦታዎች ተደራሽ በማድረግ ገበያ ውስጥ መግባት ችሏል።

ድርጅቱ ምርቶቹን በአከፋፋዮች አማካኝነት ወደተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ተደራሽ ያደረጋል። እነዚህ አከፋፋዮች መድኃኒቶችንና ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ምርቶችን ከአምራቹ በመረከብ አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ ለክልል ከተሞች ጭምር ያሰራጫሉ። በመሆኑም ድርጅቱ በገበያ ያለውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ያመርታል። ምርቶቹንም አከፋፋዮቹ በሚፈልጉት የምርት አይነትና መጠን እያቀረበ ይገኛል።

ምርቶቹ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉና እንደ ህክምና የሚታዩ በመሆናቸው በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚመረቱ ናቸው። የተወሰኑ ለኮስሞቲክስ የሚውሉ ቅባቶችና ቅባት ነክ ምርቶችም እንዲሁ ይመረታሉ። እነዚህ ምርቶችም በተለይም የቅባት ምርቶቹ በተለያዩ ፋርማሲዎች የሚገኙ ሲሆን፤ በዋናው የገበያ ማዕከል መርካቶ ውስጥ በሚገኙ ተረካቢዎችና በወኪል አከፋፋዮች አማካኝነት ማህበረሰቡ ጋር እንደሚቀርቡ ተናግሯል፡፡

ድርጅቱ አሁን ባለው የማምረት አቅም በዓመት ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ጠርሙስ የሚደርስ ምርት ማምረት የሚችል ቢሆንም፤ ከዚህ የበለጠ የገበያ ፍላጎት ቢመጣ ለማምረት የሚያስችል በቂ አቅም እንዳለው አቶ ብሩክ አስታውቀዋል። ገበያው በሚፈልገው መጠን ለማምረትም በቂ የማምረቻ ማሽን፣ የሰው ኃይልና ጥሬ ዕቃ እንዳለም ገልጿል።

በአሁኑ ወቅት 20 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለ ሲሆን፤ ካፒታሉም ወደ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ደርሷል። በቀጣይ ሥራውንና የመሥሪያ ቦታውን በማስፋት ተጨማሪ የሥራ ዕድል የመፍጠር እና ካፒታሉን የማሳደግ ዕቅድ እንዳለው አስረድቷል፡፡

ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር ድርጅቱ የአቅሙን እያረገ መሆኑን አቶ ብሩክ ይገልፃል። ድርጅቱ ሥራ በጀመረ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ኮቪድ 19 ወረርሽን መከሰቱን አስታውሶ፣ በወቅቱ በጣም ተፈላጊ የነበረውን ሳኒታይዘር በስፋት እያመረተ ለገበያ ያቀርብም እንደነበርም ተናግሯል። ድጋፍ ለሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች በአይነትም በገንዘብም ድጋፍ ማድረጉንም ጠቅሷል። በተጨማሪም መንግሥታዊ ለሆኑ ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት የድርሻውን እንደሚወጣም ነው ያስታወቀው፡፡

«በአሁኑ ወቅት አብዛኛው ሕዝብ ዘመናዊ ህክምናን እየመረጠ አይደለም» የሚለው አቶ ብሩክ፤ ወደፊት ስልጣኔ እየጨመረ ሲመጣ ማህበረሰቡ ወደ ዘመናዊ ህክምና መምጣቱ እንደማይቀር ይገልጻል። ለዚህም ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት በህክምናው ዘርፍ ብዙ መስራት እንደሚጠበቅ አስታውቋል። መንግሥት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እየሰጠ ያለውን ድጋፍ አሟጦ በመጠቀም አምራቾች መድኃኒቶችን ጨምሮ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ፍላጎቱን መሙላትና ማህበረሰቡ ጋ ለመድረስ መስራት እንደሚገባቸው አመልክቷል።

ኤኬቢዲ ፋርማሲቲዩካል ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት በቀጣይ የምርት አይነቶቹን በአይነትና በመጠን ከፍ የማድረግ ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ነው። በተለይም የምርት መጠኑን ከጥራት ጋር ከፍ አድርጎ ለማቅረብ ዝግጁ መሆኑን አቶ ብሩክ ተናግሯል። ተጨማሪ ምርቶችን እንዲሁም ተጨማሪ የሥራ ዕድል በመፍጠር በተሻለ ጥራት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት አልሞ እየሰራ መሆኑን ጠቅሶ፤ ይህን ዕቅድ ለማሳካትም ማህበረሰቡ የሀገር ውስጥ ምርትን ገዝቶ በመጠቀም የድርሻውን መወጣት እንዳለበትም አስገንዝቧል።

# ተናጋሪው ዶሴ

## የተሠበረው ጋሪ እና መዘዙ

**ምሕረት ሞገስ**

ወርቅነህ የትውልድ ቦታው ደቡብ ክልል ልዩ ስሙ ሃዲያ አካባቢ ነው። ትምህርት የተማረው እስከ 5ኛ ክፍል ብቻ ነው። አዲስ አበባ ጎጃም በረንዳ አካባቢ የግል ሥራ የሚሠራ ሲሆን፤ በ20 ዓመቱ ለመማር ፍላጎት ባይኖረውም፤ ከጓደኞቹ በተለየ መልኩ ታታሪ ነው። ሠርቶ አይጠግብም። ኑሮን ለማሸነፍ ቀን ከሌት ይባዝናል። ሰዎችን የሚተባበር ቀና ወጣት ስለመሆኑም አብረውት የሚኖሩ እና አብረውት የሚሠሩ ጓደኞቹ ይመሰክሩለታል።

ቀደም ሲል ይሸከም ነበር። በኋላ ወደ የመንገድ ላይ ንግድ ገባ። አንዱ አልሸጥ ሲለው፤ ሌላ ንግድ ይቀይራል። አንድ ጊዜ በጋሪ ሙዝ ይዞ እየዞረ ይሸጣል። ሌላ ጊዜ ደግሞ አቮካዶ እያዞረ ይሸጣል። አልሆን ሲለው ሽንኩርት እና ቲማቲም ለመሸጥ ይሞክራል። በአንድ ጋሪ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ በሁለት ጋሪ እስከ መነገድ ይደርሳል። ይህንን ሲያደርግ አንዳንዶች ከመደገፍ ይልቅ እርሱን የሚያናድድ ተግባር ይፈፅሙበታል። ዕቃውን ተውሰው በአግባቡ አይመልሱለትም፤ ታግሶ ያልፋቸዋል። ትዕግስቱን አይተው ፈሪ ነው እያሉ ያሙታል። በተለይ ጋሪ እንዋስህ ሲሉት ጨክኖ አይከለክላቸውም። መልሶ ሠርተው እንዲመልሱለት ያውሳቸዋል። ጋሪውን ሲያበላሹበት እና ሲሰብሩበት ደግሞ በጣም ይበሳጫል። ነገር ግን ብስጭቱ ብዙ አይቆይም። መልሶ ይተወዋል፡፡

ወርቅነህ ከሰዎች ጋር የሚጣላ ሰው አይደለም። ከኤርሚያስ ጋር ደግሞ በልዩ ሁኔታ ይግባባሉ። ኤርሚያስ ለወርቅነህ ጓደኛው ነው። አንዳንዴ ተከራይተው አብረው ያድራሉ። ኤርሚያስ ‹‹ጋሪህን አውሰኝ ልነግድበት›› ብሎ ለወርቅነህ ጠየቀው። ወርቅነህ እንደተለመደው አልጨከነም፤ ‹‹ወስደህ ሥራህን ስትጨርስ መልስልኝ፡፡›› ብሎ ጋሪውን አዋሰው። ኤርሚያስ በጋሪው ሲሠራ ቆየ፤ ነሐሴ 12 ቀን ስምንት ሰዓት አካባቢ ኤርሚያስ ጋሪው የሚቀመጥበት ቦታ ላይ መለሰ።

### የጋሪው መሰበር

ወርቅነህ በበኩሉ በጋሪው ሊሠራበት አስቧል። በዛውም ኤርሚያስ ጋሪውን በተገቢው መልኩ መመለሱን ለማረጋገጥ ጋሪው የሚቀመጥበት ቦታ ሄዶ ሲያየው ጋሪው ተሠብሯል። ወርቅነህ በጣም ተበሳጨ። ወደ ኤርሚያስ ሲሔድ ኤርሚያስ ከጓደኛው ዓለሙ እና ከቸርነት ጋር ነበር። ወርቅነህ ለኤርሚያስ ‹‹እንዴት ያዋስኩህን ጋሪ ትሰብራለህ?›› ብሎ ሲጠይቀው፤ ዓለሙ ጣልቃ ገባ። ለጓደኛው ለኤርሚያስ አግዞ፤ ‹‹ራስህ በሰበርከው እርሱ ላይ አታፍጥበት፡፡›› ብሎ ወርቅነህ ላይ መደንፋት ጀመረ፡፡

ወርቅነህ ‹‹አንተን አላነጋገርኩም ያነጋገርኩት ኤርሚያስን ነው፤ ስለዚህ ኤርሚያስ መልስ ይስጠኝ።›› አለው። ዓለሙ ግን ለያዥ ለገናዥ አስቸገረ፤ ‹‹ከእኔ ጋር እንነጋገር ና ይዋጣልን፡፡›› ማለት ጀመረ። ዓለሙ ደረቱን እየገፋ ግንባሩን እያሾለ ለመደባደብ ራሱን ሲያዘጋጅ፤ አብሯቸው የነበረው ቸርነት ለወርቅነህ፤ ‹‹አንተ መጀመሪያም ለምን ጋሪህን ትሰጣለህ?›› ብሎ መሐል ላይ ገብቶ ለመገላገል ሞከረ። በዛ ጊዜ ለጓደኛው ተቆርቋሪው ዓለሙ ለወርቅነህ ‹‹ዕቃህን አድርሰህ ና ወይም ልብ ካለህ ማታ እንገናኝ፡፡›› ሲለው ወርቅነህ ዝም ብሏቸው ከአካባቢው ራቀ።

ወርቅነህ ከነገር ለመሸሽ ከአካባቢው ራቅ ብሎ ቢሔድም፤ ወደ ማታ ሻይ የሚሸጥበት አካባቢ ጎዳና ላይ ሻይ እየጠጣ ብስኩት ሲበላ ስልኩ ጠራ። ስልኩን ሲመለከት የደወለው ዓለሙ ነው። ወርቅነህ ተናድዶ፤ ጥሪውን ለመመለስ ስልኩን አንስቶ ‹‹ምን ፈልገህ ነው?›› ብሎ አነጋገረው። ደዋዩ ‹‹የት ነህ?›› የሚል ጥያቄ አቀረበለት። ‹‹የትስ ብሆን ምን አገባህ? ለምን ፈለግከኝ?›› ብሎ ምላሽ ሳይጠብቅ ወርቅነህ ስልኩን ዘጋው፡፡

ዓለሙ መደወሉን አላቆመም። በድጋሚ ሲደውል፤ ወርቅነህ ‹‹በድጋሚ ስልኩ ጠራ፤ ›› እንደገና መልስ ለመስጠት ወርቅነህ ‹‹ሃሎ›› አለ። ዓለሙ ባሻገር ሆኖ ለወርቅነህ፤ ‹‹ወንድ ከሆንክ ናና ይዋጣልን፡፡›› አለው። ቀን የተጣላው ዓለሙ ማታም ሊተወው ፍቃደኛ አልሆነም። ወርቅነህ በዓለሙ ሁኔታ በጣም ተበሳጨ። ‹‹እሺ የቀኑ ቦታ ላይ ጠብቀኝ›› ብሎ ምላሽ ሰጠ። ነገር ግን ወርቅነህ ላለመጣላት በመፈለጉ መልሶ ተወው። ቀን የተጣሉበት ቦታ ላይ አልሔደም።

### የምሽት ቀጠሮ

ወርቅነህ ለጠብ የቀጠረውን ዓለሙን ትቶ እራቱን ለመብላት ወደ ጎጃም በረንዳ መሔድ ጀመረ። ወርቅነህ ወደ ጎዳናው ሲመለከት ኤርሚያስ፣ ቸርነት እና ዓለሙ ከሩቅ ሦስት ሆነው አንድ ሕንፃ ሥር ቆመው ተመለከታቸው። እነኤርሚያስ ግን ወርቅነህን አላዩትም። ካዩት ሊያጠቁት እንደሚችሉ ገመተ። ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያስብ፤ በጋሪ ቢላዋ የሚሸጥ ሰው አየ። ቢላዋ ገዝቶ ወደ ኪሱ ከተተ። ምንም እንዳልተፈጠረ እየተራመደ ሊያልፋቸው ሲል፤ ዓለሙ ወርቅነህን ሲያየው ተንደርድሮ ያዘው። እነቸርነት ለመገላገል መሐል ገቡ። ዓለሙ ከገላጋይ አልፎ ሁለት ጊዜ የወርቅነህ ፊት ላይ በቦክስ ሰንዝሮ መታው።

ወርቅነህ ቦክሱ ሲደጋገምበት በኪሱ የያዘውን ቢላዋ አውጥቶ የዓለሙን የግራ እግር ላይ ጭኑ አካባቢ አንድ ጊዜ ወጋው። የወጋበትን ስለት ቢላዋ በድጋሚ ሰንዝሮ ጎኑ አካባቢ ጎድኑን ወጋው። ዓለሙ ወርቅነህ ስለት መያዙን ሲያውቅ ጭንቅላቱን ግራ እና ቀኝ እያወዛወዘ አጎንብሶ ድንጋይ መፈለግ ጀመረ። ወርቅነህ በበኩሉ ድብድቡ እንዲያበቃ ፈልጓል። ነገር ግን ዓለሙ ካልገደለ የሚመለስ አይመስልም። ስለዚህ ወርቅነህ ፊቱን ሲያዞር የፖሊስ ጥበቃ ሴንተር ተመለከተ። ወደ ፖሊስ ማዕከሉ ጊቢ መሮጥ ሲጀምር፤ ዓለሙ ወርቅነህ ላይ ትልቅ ድንጋይ ከጀርባው ወርውሮ ጭንቅላቱን መታው። ወርቅነህ እየተንገዳገደ ቢላዋውን ግቢው በር ላይ ጥሎ ውስጥ ገብቶ ወደቀ።

ዓለሙም ከዛ በላይ መደባደብ አልቻለም። ሰውነቱ ዛለ፤ ጉልበቱ ተፍረከረከ። እርሱም ተዝለፍልፎ ግቢው ውስጥ በጀርባው ወደቀ። ወርቅነህ ከዚህ በላይ መቀጠል አይችልም ነበር። ቢላዋውን ግቢው በር ላይ ጥሎት ነበር። ዓለሙም ከወደቀበት ተነስቶ ለመደባደብ አልሞከረም። የዓለሙ ደም በከፍተኛ መጠን መፍሰስ ቀጠለ። ሁለቱም እንደወደቁ ሰዎች ተሰብስበው ወደ ማዕከሉ ገቡ። ወርቅነህን ሲያዩት ደህና ነው። ዓለሙ ግን የሚፈሰው ደም ብዙ ስለሆነ እንደተጎዳ ገምተው ወርቅነህን እዛው በፖሊስ ማዕከሉ ትተው ወደ ሆስፒታል ወሰዱት። ወርቅነህም እጁን ለፖሊስ ሰጠ። ዓለሙ ሆስፒታል እስከሚደርስ በሕይወት ነበር። ዓለሙን ሰዎች ተረባርበው ሊያድኑት ቢሞክሩም ሊሳካ አልቻለም። ደሙ በከፍተኛ መጠን ሲፈስ ስለነበር ሐኪሞቹ ብዙ ተጣጣሩ ነገር ግን በዛችው ቀን ሌሊት ሕይወቱ አለፈ።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ጉዳዩን መመርመር ጀመረ። ከወርቅነህ የእምነት ክህደት ቃል ተቀበለ። ወርቅነህ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ላይ እንደሰፈረው፤ ወርቅነህ ‹‹ጥፋተኛ ነኝ›› ብሎ አምኗል። ድርጊቱን የፈፀመበትን ሁኔታ ሲያስረዳ ሐምሌ 12 ቀን 2015 ዓ.ም የሟች ዓለሙ ዳዊት ጓደኛ የሆነው ኤርሚያስ አበራ በጋሪው ለመሥራት ወስዶ ነበር። ሥራውን ጨርሶ ጋሪውን ያስቀመጠበት ቦታ ሔዶ ሲያይ ጋሪው ተሰብሯል። ወርቅነህ ለምን ጋሪው ተሰበረ በሚል ብስጭት ኤርሚያስን ሔዶ ሲጠይቀው፤ አብሮት የነበረው ዓለሙ ለጓደኛው ለኤርሚያስ በማገዝ ራስህ የሰበርከውን እርሱን አትጨቅጭቀው ብሏል። አንድ ሁለት እያሉ ወደ ጠብ ገብተው ነበር።

በእምነት ክህደት ቃሉ ላይ እንደሠፈረው፤ ወርቅነህ ዓለሙ ይሞታል ብሎ አልገመተም ነበር። ከጠብ ለመራቅም ብዙ ሞክሯል፤ ነገር ግን በተቃራኒው ዓለሙ ወርቅነህ ተበሳጭቶ ወንጀል ውስጥ እንዲገባ ገፋፍቷል። ስልክ እየደወለ ‹‹ና ይዋጣልን›› ብሎታል። ወርቅነህ ሊሸሸው ቢሞክርም ሟች ዓለሙ ግን በተቃራኒው ወርቅነህን መንገድ ከልክሏል። በዚህ ምክንያት ወርቅነህ በስለት ራሱን ለመከላከል በወሰደው እርምጃ ሟች ዓለሙ ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል። በመጨረሻም በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ቢሮ እንዳለ የመምሪያው ኃላፊ የዓለሙ ሕይወት እንዳለፈ ሲነገረው እጅግ ደንግጧል። በድርጊቱ በጣም መፀፀቱን በመግለፅ ለምክትል ኢንስፔክተር በዕለቱ ድርጊቱን በመፈፀሙ መፀፀቱን እና በእርሱ ምክንያት የዓለሙ ሕይወት ማለፉን እንደሚያምን አረጋግጧል።



የፖሊስ ምርመራ ቡድኑ የእምነት ክህደት ቃል ከመውሰድ ባሻገር አስከሬን እንዲመረመር አደረገ። የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የፎረንሲክ ሜዲስንና ቶክሲኮሎጂ ትምህርት ክፍል የአስከሬን ምርመራ ውጤቱን በደብዳቤ አሳወቀ። በደብዳቤው ላይ እንደተመላከተው በሟቹ ጭን ላይ 17 ሴንቲ ሜትር ስፋት ያለው ቁስለት በስለት በመወጋት የተከሰተ ሲሆን፤ የ5ኛ የጎድን አጥንቱም ተጎድቷል። የሞቱ ምክንያት በግራ ጭኑ ላይ በተፈጠረ ቁስለት በነበረው ከፍተኛ ደም መፍሰስ ሕይወቱ ማለፉን ተመላክቷል።

በመጨረሻም የፖሊስ ምርመራ ቡድኑ ድርጊቱ የተፈፀመው በነሐሴ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡30 መሆኑን ጠቅሶ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ልዩ ቦታው ጎጎት ሆቴል ቡና ባንክ አጠገብ ቀን በነበረ ፀብ ምክንያት ቂም በመያዝ ስለት ይዞ በመጠበቅ ሟች ዓለሙ ዳዊት የተባለውን ሰው ወርቅነህ ጫኔ የግራ ጭኑን ከፊት በኩል አንድ ቦታ ላይ ወግቶ ከፍተኛ የደም መፍሰስ በማጋጠሙ የዓለሙ ሕይወት እንዲያልፍ አድርጓል በማለት ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሠርት መረጃውን እና ማስረጃውን አደራጅቶ ዝርዝሩን አቀረበ።

### የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በፖሊስ የምርመራ ቡድን የቀረበውን ክስ አደራጅቶ ወንጀሉ የተፈፀመው በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕግ በመተላለፍ መሆኑን ጠቅሶ፤ የአስከሬን የምርመራ ውጤትን፣ የተከሳሽ ወርቅነህን የእምነት ክህደት ቃል እንዲሁም የሰው ምስክር አቀረበ። የግድያ ወንጀል መፈፀሙን ማስረጃዎች ተሰምተው እና ታይተው በበቂ የቀረቡ በመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሰጠ።

### ውሳኔ

ተከሳሽ ወርቅነህ ጫኔ በተከሰሰበት ሰው የመግደል ወንጀል ክርክሩ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት ሲካሔድ ቆይቷል። ፍርድ ቤቱ በሐምሌ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ክስና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ ወንጀል ፈፃሚውን ያርማል ሌሎችንም ያስተምራል ብሎ ባመነበት የስድስት ዓመት ፅኑ እስራት ፈርዶበታል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የክረምቱ ነገር ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

መቼም የክረምት መልኮች ብዙ ናቸው። ቆም ብለን ሁኔታዎችን እንታዘብ ካልን ደግሞ አጋጣሚዎች በየአቅጣጫው ያሣዩናል። ክረምቱ ሲቃረብ፣ ዝናቡ ‹‹መጣሁ›› ሲል ዓእምሯችን አስቀድሞ የሚያስበው አይጠፋም። ክረምት በባህርይው እንደበጋው ደረቅ አይደለምና ቀድመው ቢፈሩት፣ ቢጠነቀቁት አይገርምም።

ክረምት በመጣ ጊዜ የወንዝ ዳር ቤቶች ዕንቅልፍ ይሉት ብርቃቸው ነው። ደሳሳ ጎጆዎች ፣ የሚያፈሱ ጣራዎች፣ ጎድጓዳ መንደሮች ሁሉ ምቾት አልባ ይሆናሉ። የክረምት ዝናብ ቆላ ደጋ ጥሎ ምድርን አረስርሶ ብቻ አይበቃውም። ደርቆ ከከረመው መሬት ያለ አቧራ ጭቃ ሆኖ እስኪላቆጥ የየዕለት ግብሩ ከበረከት ይሻገራል፡፡

ዝናቡ ጠንከር ብሎ በመጣ ጊዜ እንደዋዘ ደርሶ፣ ያሻውን አርጥቦ ብቻ አይመለስም። ከመሬት ያገኘውን እየጠረገ፣ ስር ይዞ የኖረውን እየገነደሰ መሬትን አጥቧት፣ ሞልጯት ያልፋል። ገና የረጠበው ጠፈፍ ሳይል፣ ‹‹እግዚኦ! ማረን! አውጣን ›› ተብሎ ሳያበቃ ደግሞ አጋጣሚው መልሶ ራሱን ሊደግም ይችላል። ይህ እንግዲህ ክረምትን ከፍስሐው አሻግረን ‹‹ቁጣውን ጣለብን፣ መአቱን አመጣብን ›› በምንል ጊዜ የሚጋጥም ሀቅ ነው፡፡

ተፈጥሮ ምንጊዜም ውሉን አይስትም። ፀሀይ ብርዱን፣ ዶፍ በረዶውን ሲያዘንብ በምክንያት ነው። ለእንዲህ አይነቱ እውነት ደግሞ በይሁንታ የሚለወጥ፣ በማስጠንቀቂያ የሚቀየር ምርጫ የለም። ተፈጥሮ ፣ ተፈጥሮ ነውና አምነን እንቀበለዋን፣ ፈቅደን እንኖረዋለን።

አንዳንዴ ተፈጥሮ ፊቱን ሲያዞርብን ጥፋቱ ይከፋል። በጋው ላይ ያልነበረ አንዳች ምልክት በክረምቱ ደርሶ ባህርይው ይለወጣል። ጥቂት ያልነው ሁሉ ገዝፎ፣ ሁኔታው ተቀይሮ ለሰው ልጆች መኖር ጠንቅ ይሆናል። ይህን ጉዳይ ስናነሳ በርካታ ሀቆች ወደ ራሳችን መምጣታቸው አይቀሬ ነው፡፡

ዛሬ ዓለማችን በተፈጥሮ አደጋዎች ስትናጥ ፣ ስትፈተን ፣ ውላ ታድራች። በግግር በረዶ መቅለጥ፣ በመሬት መራድና መንሸራተት፣ በአውሎንፋስና ውሃ መጥለቅለቅ በሰደድ እሳትና በሌሎችም። ለዚህ ሁሉ ጥፋት ግን በአንድም ይሁን በሌላ የሰው ልጅ እጆች አስተዋጽኦው የላቀ ነው። ሰው ተፈጥሮን አክብሮ ከመያዝ ይልቅ ለተቸረው ድንቅ ስጦታ ግዴለሽ መሆኑ ዛሬም ድረስ ዋጋ እያስከፈለው ይገኛል።

ወደእኛ ሀገር እንመለስ። አሁን የምንገኝበት ጊዜ የክረምት ወቅት ነው። ክረምታችን ምንጊዜም ቀኑን ቆጥሮ፣ ወራትን አስልቶ የሚደርስ ነውና ገብቶ እስከሚወጣ በራሱ ባህርይ ይገዛል። ወራቱ ላይ የጎበዙ ብርቱዎች ጊዜውን በወጉ ተጠቅመው አዝምረውና አርሰው የሚጎርሱበት ነው፡፡

በክረምት የሚታሰበው ዝናብና ጭቃ ብቻ አይደለም። በጊዜው በረከቶች ልሥራ ፣ልጠቀም የሚል ከተገኘ ወቅቱ ለእርሱ ከወርቅ በላይ ይመዝናል። ከዚህ እውነታ ወጣ ብለን ስናየው ደግሞ ክረምት በተለይ ለከተማ ነዋሪዎች ከችግሮች ጋር የሚታሰብ ከባድ አጋጣሚ ሊሆን ይችላል።

ዛሬ ላይ በመኖሪያ አካባቢዎቻችን ጥቂት በማይባሉ ሥፍራዎች ቆሻሻ አብሮን ውሎ ያድራል። ለዓይን የሚከብድ ለአፍንጫ፣ የሚሰነፍጥ፣ ለእይታ በእጅጉ የሚያስጠላ ቆሻሻ ለእኛ ብርቃችን አይደለም። ከተማችን ሁሌም ከቆሻሻነት መልኳ ተላቀቀች፣ ጸዳች ሲባል አይሰማም። ቀኑን ሙሉ ሲጠርጉ ቆሻሻን ሲያስወግዱ የሚውሉ ሠራተኞች ማግስቱንም መኪና ሞልተው ሲሄዱ ይታያል። ይህ ደግሞ ክረምቱ ላይ ሲሆን ጉዳቱ የከፋ ነው። ቱቦ ውስጥ የከረመ ቆሻሻ፣ በዝናብ የራሰ ቆሻሻ፣ ሆን ብሎ የሚጣል ቆሻሻ በአንድ ያብሩና ሽታቸውን ሊናገሩት ይከብዳል፡፡

በጋ በሆነ ጊዜ ደረቅ ቆሻሻው ራሱን ችሎ የሚወገድ ነው። ክረምት ላይ ግን ለሚጣለው ቆሻሻ ሌላ ሃይል ይጨመርለታል። በተለይ እንደነገሩ ዝናብ አግኝቶት የከረመ ካለ ችግሩ ከህመም በላይ ነው። ማንም ይህን እንደ ግድ ሊቀበለው የኑሮ ሁኔታዎች ያለምዱታል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ አካባቢዎች ቆሻሻን በቀን ከቤት አውጥቶ መጣል በሕግ ተከልክሏል። እንደቀድሞው በቀንና ባሻው ሰአት ቆሻሻ የሚጥል ሰው ከተገኘ ቅጣቱ ከፍ ያለ ይሆናል። አስገራሚው ጉዳይ ግን ቀን የተከለከው ሕግ ተገልብጦ ምሽት ላይ መተግበሩ ነው። ደንቡ ሲወጣ ግን ለተጠቃሚዎች ቀንና ሰአት ተለይቶ ነበር፡፡

ለአንዳንድ ሰዎች ይህ አይነቱ መመሪያ ያመቻቸው ይመስላል። የቤት፣ የግቢያቸውን ያለ የሌለ ቆሻሻ አውጥተው የሚጥሉት ሁሌም ምሽት ላይ ሆኗል። አብዛኞቹ ‹‹አዩኝ አላዩኝ›› በሚል ጨለማን ይተገናሉ። የእነሱን በምሽት መድረስ የሚናፍቁ ቋጠሮ በርባሪዎች ደግሞ ከስፍራው እስኪርቁላቸው አይጠብቁም። በየላስቲኩ ያለውን ምናምን ለመበርበር ይፈጥናሉ። የሚፈልጉት ነገር ፣ ከማይፈልጉት ቆሻሻ እስኪለይ አካባቢው ለመዝረክረክ አፍታ አይቆይም፡፡

የተጣለው ውዳቂ በየቦታው ሲበተን ደግሞ ሊያነሳው ዞር የሚል አይገኝም። መዝረክረኩ ለውሻና ድመት ሲሳይ ሆኖ ስፍራው በሚያስነውር እይታ ይሞላል። እንደተለመደው ቆሻሻን የሚያስወግዱ ሠራተኞች ያለሰአታቸው ብቅ አይሉም።

ቀኑ በክፉ ሽታና ለዓይን በሚያስቀይም እይታ ታጅቦ ይውላል። ምሽት ደግሞ ሁሉም እንደልምዱ ሆኖ ይቀጥላል። ቆሻሻውን የሚያነሱት ስራቸውን ጨርሰው ሲሄዱ የሚጥሉት ደግሞ በእግራቸው ይተካሉ። ‹‹ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ›› ሂደቱ አይቋረጥም፡፡

በአብዛኞቹ የከተማችን አካባቢዎች ያሉ የውሃ መውረጃ ቱቦዎች ክረምት ላይ በቆሻሻ ይደፈናሉ። ዝናብ ጠብ ካለ አልያም ከባድ ሆኖ ከጣለ ዓይናችን ተአምር ያያል። ጎርፉ መሄጃ መስመር የለውም። ወደ አስፓልት ገንፍሎ ይወጣል። በአፍታ ቆይታ መውጫ መግቢያ መንገዶች ይዘጋሉ። ይህኔ መኪኖች እግረኞች፣ ከአንድ ቦታ ለሰአታት ሊታገቱ ግድ ነው። እንዲህ በሆነ ጊዜ ቀድሞ ባልተለመደ ሁኔታ አስፓልቱ በጎርፍ ተሞልቶ ይዘጋል። የውሃ ሙላቱ ሄዶ እስኪያበቃም ተጎልቶ መቆየት የውዴታ ግዴታ ነው፡፡

የዝናቡ አጋጣሚ በተለይ ምሽት ላይ ችግሩን ያብሰዋል። በመዘጋጋቱ ምክንያት በሚኖር የረዘመ ቆይታ ብዙዎች በሰአቱ ለቤታቸው እንዳይገቡ ምክንያት ነው። ከጨለማው መግፋት ጋርም በርካቶቹ ለዝርፊያና እንግልት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

ብዙ ጊዜ የመንገድ ላይ ጎርፍ ጥፋቱ ከፍ ያለ ነው። በሱቆች ዳርቻ ያሉ የሽያጭ ዕቃዎችን አግበስብሶ ይወስዳል። እግረኞችን አብዝቶ ይፈትናል። የመንገድ ላይ አካፋዮችን፣ ጠቃሚ የሀገር ሀብቶችን ያወድማል። ይህን የዚህን ሁሉ ችግር የመነሻ ምንጭ እንመርምር ከተባለ መልሱ አንድና ግልጽ ነው። ከየቤታችን ፣ ከየመንደራችን እያወጣን እንደዋዛ የምንጥለው ቆሻሻ፡፡

በያዝነው ክረምት በዚሁ የመነሻ ችግር ሳቢያ ብዙዎቻችን ከመንገድ ላይ እናመሻለን። ለመራመድ፣ ለመሻገር ተቸግረንም ድንገቴውን የጎርፍ ሙላት ስንለምን እንቆያለን። ጥቂት የማይባሉ ወገኖች ደግሞ ሥራ ውለው ሲገቡ ቤታቸው እንዳይሆን ሆኖ ያገኙታል፡፡

የቆሻሻ አጠቃቀማችን ችግር ከራሳችን አልፎ በዓለም ጭምር ስማችን በክፉ እንዲነሳ አድርጓል። ዛሬም ግን ለዚህ እንከናችን ዘላቂ መፍትሄ እየፈለግን አይደለም። አሁንም ከእኛ የምናስወግደውን ቆሻሻ በየመንገዱ እንጥላለን። ዛሬም ከበሽታና ፣ ከከፋ ጉንፋን አልወጣንም። ዝናብ በጎበኘን ቁጥር አስፓልቶቻችን ጀልባ የሚሹ ይመስላል። አሁንም ከችግርና ከጎዳና ላይ ጎርፍ አልተላቀቅንም፡፡

አንዳንዴ የከተማዋ የጽዳት ሠራተኞች ድካም በእጅጉ ያሳዝናል። በ‹‹ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ሂደት ሲመላለሱ መኖራቸው እንዳለ ሆኖ ሥራቸው ያለመፍትሄ መቀጠሉ አስገራሚ ያስብላል። ሁሌም በጋሪ ሞልተው የሚወስዱት የቆሻሻ ክምር በአብዛኛው የሚዛቀው ከየቱቦዎቹ ነው፡፡

ለከተማችን መንገድ ማሳለጫ ተብለው በሚሠሩ መንገዶች ላይ የሚዘጋጁ ቱቦዎች ከፍተኛ ወጪ የተከፈለባቸው ነው። እነዚህ የሀገር ሀብቶች ግን በወጉ ተሰርተው እንኳን ሳይጠናቀቁ ሆዳቸው በቆሻሻ ይታጨቃል። ልማደኛው ጎርፍ ደርሶ ዳርቻውን ሲያጥለቀልቅ ችግሩን የመታደግ አቅም የላቸውም። ማዳን ሲገባቸው እነሱም ሰለባዎች ይሆናሉ፡፡

ከዚህ አጋጣሚ በኋላም ሆነ በፊት በየዕለቱ የጎረሷቸውን ውዳቂዎች ጠርጎ የማውጣት ግዴታ የተጣለው በእነዚሁ መከረኛ የጽዳት ሠራተኞች ትከሻ ነው። በየቀኑ ቆሻሻው ይታጨቃል። በየቀኑ ጠርገው ያወጣሉ። እንደ እኔ ግን ንብረትን ለጉዳት ዳርጎ ከማበላሸትና ጉልበት በከንቱ ከማባከን መፍትሄው ቢበጅ ይሻላል ባይ ነኝ፡፡

አሁን ላይ በየአካባቢው ተሠርተው የተጠናቀቁ የውስጥ ለውስጥ አስፓልት መንገዶች ጥቂቶች አይደሉም። ከግንባታው ጋር የተቀበሩና ክፍት የተተው ትላልቅ ቱቦዎች ደግሞ ያለአንዳች አገልግሎት ይታያሉ። እነዚህ ቱቦዎች የቆሻሻ ምሽግ ናቸው። አሳቢ ቢገኝ ኖሮ በወቅቱ ሽራ ማስጀመር ፣ አልያም በጠንካራ ሽፋን መጋረድ ያስፈልግ ነበር።

እንዲህ ከተሞከረ አገልግሎት የሚሰጡት ቱቦዎች ጠቀሜታ ለተሠሩለት ዓላማ ብቻ ይሆናል። ቆሻሻ ማጨቃቸው ይቀርና ለውሃ መውረጃ ብቻ ይሆናሉ። ይህ የኔ አስተያየት፣ የቢሆን ምክርና ግሳፄ ነው። ያው የሚሰማ ከተገኘ።

# ዓስም አቀፍ

## በኢራንና በሩሲያ መካከል ያለው ግንኙነት እየተጠናከረ እንደሚገኝ አሜሪካ ገለጸች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኢራን እና ሩሲያ መካከል ያለው ግንኙነት እየተጠናከረ እንደሚገኝ አሜሪካ ገለጸች።

የዩክሬኑ ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ በወታደራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የሀገራቱ ግንኙነት መጨመሩ ተሰምቷል በሩሲያ እና ኢራን መካከል ያለው ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እንደሚገኝ አሜሪካ አስታወቀች።

የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስትር መሥርያ ቤት ፔንታጎን ምክትል ቃል አቀባይ ሰብሪና ሲንግ በሳምንታዊ መግለጫቸው ላይ እንደተናገሩት የሀገራቱን ግንኙነት አሜሪካ በቅርበት እየተከታተለች ትገኛለች።

ከዋሽንግተን በተጻራሪ የቆሙት ሞስኮ እና ቴሄራን ከሶቭየት ህብረት መፍረስ ጀምሮ እያሳደጉት የሚገኘው ግንኙነት በተለያዩ ዘርፎች ላይ ተጠናክሮ ይገኛል። ሞስኮ እና ቴሄራን በመካከለኛው ምስራቅ በኢራቅ፣ ሶርያ ፣ አፍጋኒስታን የሚያንጸባርቁት ሃሳብ ተመሳሳይ ከመሆኑ ባለፈ በአንዳንድ ሀገራት ላይ ለተመሳሳይ ቡድን ወታደራዊ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደቆዩ ይታወቃል።

ሀገራቱ በጋዛው ጦርነት ለሀማስ እንደሚወግኑም የፔንታጎን ምክትል ቃል አቀባይ ተናግረዋል። ከዚህ በተጨማሪም ሩሲያ በዩክሬን ላይ በምታደርገው ውግያ የኢራን ከፍተኛ የጦር መሣርያዎች እና ድሮኖች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ነው ያነሱት።

ባሳለፍነው መጋቢት ሮይተርስ ባወጣው መረጃ ኢራን ለሩሲያ 400 ባላስቲክ ሚሳኤሎችን መላኳን ከውስጥ ምንጮቼ አገኘሁት ባለው መረጃ መዘገቡ ይታወሳል።

ይህን ተከትሎም ሞስኮ እና ቴሄራን ጉዳዩን ቢያስተባብሉም መሰል የጦር መሳርያ ድጋፍ እና ልውውጦች በሀገራቱ መካከል እንደሚደረግ ተደጋጋሚ መረጃዎች እየወጡ ይገኛሉ።

ሶስተኛ አመቱን ባስቆጠረው የዩክሬን ጦርነት ሩሲያ የመድፍ ተተኳሾችን ፣ ድሮኖችን እና የመካከለኛ ርቀት ሚሳኤሎችን ከኢራን እንደምታስገባ ሲገለጽ በተመሳሳይ የረጅም ርቀት ሚሳኤሎችን ለኢራን በመሸጥ ላይ እንደምትገኝ ተነግሯል።

ባለፈው ዓመት ህዳር ወር ላይ ኢራን ከሩሲያ ጋር ከቀረጥ ነጻ የንግድ ስምምነት ላይ ደርሳለች፤ ከዚህ በተጨማሪም በ2010 ሀገራቱ የተፈራረሙትን የሁለትዮሽ የትብብር ስምምነት በአዲስ ስምምነት ተክተዋል።

በ2023 የታደሰው ስምምነት ኢኮኖሚ ፣ ወታደራዊ እና ፖለቲካዊ ትብብርን የሚያካትት ሲሆን ለ20 ዓመታት የሚቆይ መሆኑም ታውቋል።

በተመሳሳይ ዓመት በሀገራቱ መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ 5 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ ነበር።



በዓለም አቀፍ መድረክ የሀገራቱን ወዳጅነት እና ትብብር በስጋትነት የምታየው አሜሪካ በቅርብ ዓመታት እያደገ የመጣውን ግንኙነታቸውን በቅርበት እየተከታተልኩ ነው ብላለች።

## የዓለም ጤና ድርጅት የዝንጀሮ ፈንጣጣ የህብረተሰብ ጤና ስጋት ሆኗል ሲል ለሁለተኛ ጊዜ አወጀ


**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዓለም ጤና ድርጅት የዝንጀሮ ፈንጣጣ የህብረሰብ ጤና ስጋት ሆኗል ሲል ለሁለተኛ ጊዜ አወጀ።

የዓለም ጤና ድርጅት የዝንጀሮ ፈንጣጣ በዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኮንጎ መከሰቱን እና ወደ ጎረቤት ሀገራት መስፋፋቱን ተከትሎ በሁለት ዓመት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ በሽታው ዓለምአቀፋዊ የህብረተሰብ ጤና ስጋት መሆኑን አውጇል።

የአስቸኳይ ጊዜ ኮሚቴ በሽታው የህብረተሰብ ጤና ስጋት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም ለማማከር ባለፈው ረቡዕ እለት ስብሰባ አድርገው ነበር።

የህብረተሰብ ጤና ስጋት ደረጃ፣ ድርጅቱ የሚሰጠው



ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ሲሆን ይህም በበሽታው ዙሪያ ጥናት እና ርዳታ እንዲፋጠን እንዲሁም በሽታውን ለመቆጣጠር ዓለምአቀፋዊ የህብረተሰብ ጤና ርምጃዎችን ለመውሰድ ያለመ ነው።

"እነዚህን ወረረሽኞች ለማስቆም እና ሕይወት ለማዳን የተቀናጀ ዓለምአቀፋዊ ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኗል" ብለዋል ዶክተር ቴድሮስ።

የዝንጀሮ ፈንጣጣ በንክኪ የሚተላለፍ በሽታ ነው። ብዙ ጊዜ ቀላል የሚባል ቢሆንም አልፎ አልፎ እስከሞት የሚያደርስ ነው። በሽታው የጉንፋን አይነት ምልክቶችን እና በሰውነት መግል የያዙ ትናንሽ እብጠቶችን ያስከትላል።

በኮንጎ የተሰራጨው ወረርሽኝ ልዩ መጠሪያው ወይም ዝርያ ክላድ አይቢ ተብሎ ይጠራል። ነገር ግን ክላድ አይቢ የተባለው አዲሱ ዝርያ በወሲባዊ ግንኙነት ጭምር በቀላሉ የሚተላለፍ ነው ተብሏል።

በሽታው ከኮንጎ ወደ ቡሩንዲ፣ ኬንያ፣ ሩዋንዳ እና ኡጋንዳ እና ወደ ሌሎች ጎረቤት ሀገራት መሰራጨቱ የዓለምጤና ድርጅት ርምጃ እንዲወስድ አስገድዶታል።

ዶክተር ቴድሮስ የአዲሱ የበሽታው ዝርያ በፍጥነት መስፋፋት እና ከዚህ ቀደም ባልታየባቸው ጎረቤት ሀገራት መከሰት እንዲሁም በአፍሪካ ውስጥ የመስፋፋት አቅሙ እንደሚያስጨንቃቸው ገልጸዋል።

ድርጅቱ ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ለመስጠት 1.5 ሚሊዮን መመደቡን እና በመጪዎቹ ቀናት ተጨማሪ እንደሚለቅ ተናግረዋል ዳይሬክተሩ። የድርጅቱ የመጀመሪያ ምላሽ እቅድ 15 ሚሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልገው ተገልጿል።

በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ የአፍሪካ ከፍተኛ የህብረተሰብ ጤና አካል የዝንጀሮ ፈንጣጣ የአህጉራቱ አደጋ ሲል አውጇል። በሽታው በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ሲሆን ቢዚህ አመት ህጻናትን ጨምሮ 500 ሰዎች ሲሞቱ፣ 17ሺ የሚሆኑ ደግሞ በሽታው ሳይዛቸው አይቀርም ተብሎ ተጠርጥረዋል።

## መጋቢ አዕምሮ

# ሕልምህን ካላከበርከው፤ ትገፈተራለህ!

**አንስይ ጥላሁን ምትኩ**

በዚች ምጥን ጽሑፍ የአንድ ሰው የሕይወት ዘመን ሕልም ወይም ግብ ለመቅረፅም ሆነ መዳረሻው ላይ ለመገኘት ማለፍ ወይም ማድረግ ስላለበት ጉዳይ ምክረ ሀሳብ ለመስጠት የግል ልምድንና አረዳድን ማዕከል በማድረግ ለአንባቢ ለማድረስ በማሰብ እሞክራለሁ። ስለሆነም በወፍ በረር ተዳዳኝ ጉዳዮችን እንመለከታለን። ጤናማ ስኬት ምን መልክ አለው! የሚለውን በተለየ አፅንዖት ሰጥተን እንመለከታለን፡፡

**እነሆ፡-**

ለውጥን ገና ማህፀን ውስጥ ሆነን ተለማምደነዋል። እናም እድገት ሁሉ ለውጥ ሲሆን ለውጥ ሁሉ ግን እድገት አይደለም። ስለሆነም ብርቱ ሕይወት የመስዋዕትነት ተምሳሌት ልትሆን የምትችልበት አጋጣሚ በርካታ ነው። ለውጥ በራሱ ከአዲስ ነገር ጋር መፋጠጥ ስለሆነ አዕምሮንና ስሜትን ይፈትናል፡፡

አጥብቀን የምንሻው የትኛውም አይነት ውጤት ሂደት ነው። ሂደት ደግሞ መንገዱ ነው። ነገር ግን የመንገዱ መዳረሻ ስኬት የሚመስለው የትየለሌ ነው። ግን እኮ... ስኬት ሁሌም የምንኖረው እንጂ ነገ የምንደርስበት ወይም ያጣነው ነገር አይደለም። ምክንያቱም ስኬት ሁሌም ከውስጣችን ያለ እንጂ ከውጭ የምንፈልገው ወይም የሚሰጠን አይደለም። ጉዞህን ከለየህበት ቅፅበት ጀምሮ የምትኖረው ነው። የምትኖርለትን ውስጣዊ ገፊ ኃይል መለየት ነው፤ ስኬት። የማያቋርጥ ውጤታማነትና የገደብ የለሽ ደስታ ምንጩም ይህ ይመስለኛል፡፡

ለእያንዳንዱ ሰው ከውጭ የሚሰጠው ነገር በረከት ወይም ስጦታ እንጂ ስኬት አይደለም። ስጦታ፤ እያደረገው ላለው ሥራ ከሆነ፣ ምክንያቱ የውስጥ ማንነት ሽልማት ሆኖ በጉዞ ውስጥ እንደ አንድ ፌርማታ ሊታይ የሚችል ነገር ነው። ከዓላማ ወይም ከሕልም ጋር በመዝለቅ የሚገኝ ሽልማት ነው። ይህም ጉልበት ወይም አነሳሽ ምክንያት ሆኖ ብርታት ያጎናፅፋል። ተጓዳኝ እውቅና ይዞ ይመጣል።

ሆኖም ግን ስኬት የማይረግብ እሾት (መሻት) ዘላቂ ሽልማት ነው። ውስጥን ፈንቅሎ የሚወጣ የሚንቀለቀል ጥሬ ጉልበት ነው። ‹‹እመነኝ፣ እሾትህ ከችሎታህ በላይ ከሆነ ተዓምር ትሠራለህ››። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ሰዋዊ ችሎታዎች በትምህርት ወይም በልምምድ የሚገኙ ናቸው። ለዚህም ነው ፤ ‹‹እሹ ታገኙማላችሁ፤ አንኳኩ ይከፈትላችኋል›› የሚባለው። ስለዚህም መሻትህን ጠብቀው። ጉጉትህን አክመው። አስቸጋሪና አሻሚ ቢሆንም በምናብህ የጠራ ምስል ተመልከት። መንገድህን ተረዳው። የተገደቡና ያልተገደቡ ተፈጥሯዊ ማንነቶችህን አጥናቸው። ስለሆነም የኃይልህ ብርታት የሚወሰነው በነኚህ ማንነቶችህ ላይ ነው። ማስተዋልና ትዕግስት ተላብሰህ በመንገድህ ከፀናህ ሕልምህ ሁሉ እውን ይሆናል። ብቻ መንገድህን በአዕምሮህ ተመልከተው። መንገድህን ካለየህ የትኛውም መንገድ ወደ የትም ይወስድሀል። የአዕምሮህን ጓዳ ጎድጓዳ ፈትሸው፤ መርምረው። የነፃነትህም ሆነ የሕይወት ግብህ ሚዛን መፍለቂያ፤ የደህንነትህ ምሰሶ፤ አንድም ሁለትም የሆነ ኃይልህ ነውና ለየው፡፡

የጠራ ሕልም ሲባል በግልፅ ቋንቋ ሚዛን ጠብቆ ወረቀት ላይ የሰፈረ፣ የእለት ከእለት እንቅስቃሴዎቻችንን የሚገራ ግብ ያለው ተግባር ነው። የሕይወት ፍሬም ልንለው እንችላለን። ስታስበው! የምትሄድበትን ሳትገነዘብ ስኬት መናፈቅ ሰማይን በጣቶችህ ለመዳሰስ እንደመሞከር አይሆንብህም?... ሐቁ ይሄው ነው፡፡

ለዚህ የሚያበቁ በርካታ ጥቃቅን ተግባራት ቀድመው መከናወን አለባቸው። ‹‹ማለትም›› ሰው በክህሎት እየዳበረ፣ በዕውቀት እየጎለመሰ የሚሄድ ፍጡር ነው። ምክንያቱም ማኅበራዊ ሰንሰለቶች ለተለያዩ ሥርዓቶች መፈጠር ምክንያት ናቸው። ፈትሻቸው። እርምጃህ ወቅቱን የዋጀ ይሁን። ስኬት ከወቅት ጋር የተሳለጠ መስተጋብር ውጤት ነው። ጊዜው የፈጠራቸውን ዓውዶች ተረድቶ ተመጣጣኝ ምላሽ መስጠት ያሸልማል። የራስን አቅም መመዘኛም ይሆናል። ለዚህም መሰለኝ ኤርሚያስ አመልጋ፤ ‹‹ካላታገለኝና ካልፈተነኝ፣ ልኬ አይደለም!...›› የሚለው (የማይሰበረው ኤርሚያስ አመልጋ ፤ ገፅ 178፣ ‹‹አንተነህ ይግዛው›› እንደፃፈው)፡፡

**‹‹መንገድህን ካለየህ የትኛውም መንገድ ወደ የትም ይወስድሃል። የአዕምሮህን ጓዳ ጎድጓዳ ፈትሸው ፤ መርምረው ። የነፃነትህም ሆነ የሕይወት ግብህ ሚዛን መፍለቂያ፤ የደህንነትህ ምሰሶ፤ አንድም ሁለትም የሆነ ኃይልህ ነውና ለየው፡፡››**

ስለሆነም ስኬት ማለት ምኞት ብቻ አይደለም፤ ለሚሻውና ልቦናውን በጌትነት ላጠመቀው፣ ዓውዱን ላወደው፣ የማግኛውን ዘዴ ለቀየሰው እና በመጨረሻም ያቀደውን ለተከታተለውና ላስፈፀመው ነው ‹‹እምነት ክብረት ዓለም›› ሚሊዮኑን የምታስታቅፈው። ይህም የምትሠራውን ለይተህ ከማወቅ ይጀምራል። ‹‹ያለሥራ የለም እንጀራ›› እንዲሉ አበው። አንድ ሰው ሊያሳካ የሚፈልገውን ጉዳይ ለይቶ ሲከውን ስኬት እንለዋለን። ሂደቱም ውስጥህ ላይ የሚንቀለቀለውን ያልተገራ



ፍላጎት በተጠና እርምጃ መግራት ነው። ስለሆነም ሕይወት እንደ ምግብ ቤት ነው። መክፈል እስከቻልን ድረስ የፈለግነውን እናገኛለን። ዋናው ጉዳይ ‹‹ግባችንን ከተረዳን በኋላ የምንከፍለው ዋጋ ምን ድረስ መሆን አለበት›› የሚለው ላይ የሚኖረን አቋምና ፅናት የሚወስነው ነው፡፡

ስኬት ውስጣዊ ነው። ከውስጣችን አድጎ ሕይወታችንን ወደ ምንፈልገው አቅጣጫ የሚመራ ሂደታዊ ወይም የማይቋረጥ እሾት ነው። መለወጥ እችላለሁ! ማድረግ እችላለሁ! የሚል እልህ የተላበሰ ከራስ ጋር የሚደረግ ትንቅንቅ ነው። ወደ ምድር ስንመጣ (ከእናታችን ማህፀን ስንወጣ) አልቅሰን። ተወራጭተን። ተፈራግጠን ቀስ በቀስ ወደ ልምምድ ውስጥ እንገባለን። ኖረን በከፈልነው ልክ አንዳንዴም በላይ ወይም በታች ዋጋ ተቀብለን ከምድር እንሰናበታለን። ሆኖም ግን መቋጫው በፀፀትና በቁጭት መሆን የለበትም። ይህ ሁኔታ የሚስተካከለውና መልክ የሚይዘው በሚኖረን ስኬት ልክ ነው። ስለሆነም በምድር ስንኖር የሚገባንን ወስደን፣ በሚገባን ልክ መጥነን ኖረን፣ የተገለገልናትን ምድርና ዓለም በስፋት አገልግለን፤ ከተጠቀምነው በላይ በማትረፍ ትውልድን አገልግለን፣ ሰጥተንና ተቀብለን፣ በመዳፋችንና በላባችን ዋጋ ፀፀትን አስወግደን በሠላም መሰናበት ያስፈልጋል። ለዚህ ሳይሆን ይቀራል ገጣሚው ከበደ ሚካኤል ፤

**“ፅድቅና ኩነኔ ቢኖሩም ባይኖሩም፤**
**ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም፡፡”**

በማለት የተቀኙት፡፡

በቀጥተኛ አገላለፅ ስንተረጉመው ‹‹The major key to your better future is you!›› የሚለው የእንግሊዘኛ አባባል ይበልጥ ገላጭ ነው፡፡

ስለሆነም ስኬት ማለት ሕይወትን በቁም ነገር በመቀበል ትርጉም የሚሰጠንን የልቦናችንን መሻት በዙሪያችን ካለ ሕግና ሥርዓት ጋር አስማምቶ መዝለቅ ነው። የራስን ዕድል በራስ መወሠንም ጭምር ነው። ስኬታማነታችንን በራሳችን መወሰን እንችላለን ስንል ሰዋዊ ፀጋዎችን ተጠቅመን ነው። ከነዚህ ፀጋዎች መካከል ትልቁን ድርሻ የሚጫወቱት የምናብ (imagination) እና የአመክኒዎ (Reason) ስጦታዎች ናቸው። እንግዲህ የነፃነት ምንጩ እነዚህ ፀጋዎች ይመስሉኛል። ነፃነት ምንድን ነው? ከተባለ ደግሞ ‹‹የበለጠ ተወዳዳሪ መሆን›› ማለት ነው።

እያንዳንዱ ሰው ውስጡ ያለውን ጥበብ ለራሱና ለሌሎች ሊተርፍ በሚችል መልኩ ለማድረስ መጣር ማለት ነው። ውድቀትንና ስኬትን በውሳኔዎቻችን ልክ መቀበልም ነው። የኃላፊነት ምንጩ ነፃነታችንን ተጠቅመን በምናደርገው ውሳኔና ተግባር አማካኝነት የሚመጣን ማንኛውም ምላሽ ወይም ውጤት ተጠያቂው ‹‹እኔ ነኝ!›› ብሎ ጠንካራ አቋም መያዝ ነው። ‹‹ታላላቅ ሰዎች እራሳቸውን ይፈጥራሉ›› የሚለው ብሂል የሚሠራው ለእያንዳንዱ እርምጃቸው ውጤት ሙሉ ኃላፊነት በመውሰድ አዲስ በር ለሚከፍቱ ብርቱ እጆች የተሰነዘረ ነው። በተለይ ያለንበት ዘመን ባሕሪ ይህ ነው።

ታዲያ! መሻትህ ለውስጥህ እውነት ነፀብራቅ ነው። የጌትነትህ ምንጩ ማንነትህን በተገቢው ዓውድ መሾምህ ላይ ነው። ይህ ጌትነትህ ደግሞ የቀረፅከው ግብህ ወይም ወረቀት ላይ ያሰፈርኸው ሕልምህ ረዳት ነው። ብልጫ የምታሳይባቸው ነገሮች ምንጭ ይህ ተግባራዊ ኃይል ነው። ስለሆነም ለአንተ ብቻ የሚታይህ የጠራ መንገድ፤ ለኑሮህ መቃናት ቁልፍ ነው። ጨብጠው። ‹‹ሰው ለማይታየው ሕልሙ አሽከር ነው›› የሚባለው ብሂል አዕምሮህ ላይ በግልፅ የተቀረፀን እና የፀናን መዳረሻ እንጂ ብቅ ጥልቅ የሚልን ተርመስማሽ ሃሳብ አይደለም። በሃሳብ ደረጃ ብዙ ሰው የትም፣ ወደ የትም ደርሶ ይመለሳል። ይህንን የሰው ልጅ የአዕምሮ ባሕሪ ተረድቶ በልምምድና በንቃት ገርቶ በተወሰነና በተለየ (በታወቀ) ጉዳይ ላይ በማሰላሰል፣ በመመርመር ጥልቅ አረዳድ በመጎናፀፍ መንገድን ማጥራት ይጠበቃል። ይህ ተግባር ትኩረት የሚጠይቅ በመሆኑ በሂደት የምንፈልገውን እንድንጎናፀፍ ይረዳል፡፡

ስለሆነም በሕይወት ስትኖር አዕምሯዊ ረቂቅ የምስል ረዳት ይኑርህ። ሕሊናህ በጉልህ ይሳለው። የስኬት የመጀመሪያው ነገር የሚታይ አዕምሯዊ ረዳት ማግኘት ነው። የሚታየው ነገር ሁሉ የመጣው ከማይታየው ነገር ነው። ከተገራ ሃሳብ። ስለሆነም ሕልምህን ቅረፅ። እወቀው። እመነው። ተግብረው። ለመሰናክሎች እጅ መስጠት የያዙትን ለመጣል መፍቀድ ነው። ባልተረዳኸውና በማታምንበት ነገር ፅናትና ትጋት ሊኖርህ አይችልም። ስለሆነም በእጅህ ላይ ላለውን ፀጋ በቀላሉ አትልቀቅ። መርምረው። እወቀው። የግብህ ሾፌር አንተ ስለሆንክ በመንገዱ ያለማቅማማት ዝለቅበት። ፌርማታዎችህ ፤ ምርጫዎችህ ናቸውና በጥንቃቄ ምረጣቸው። መዳረሻህ የፃፍከው አንተነትህ ነው። አጥብቀህ ያዘው። መሸነፍን መፍራት ከስኬት ያርቃል። ትግልህ የመውደቅና የመነሳት፣ አቀበትና ቁልቁለት ያለበት ሸካራ ሜዳ ነው። በሂደት የምትጎናፀፋቸው የሰሉ እይታዎችህ እና የተሞረዱ ልምዶችህ ወደ ውጤት ይቀይሩታል። አባጣ ጎርባጣውን የመጫወቻና የድል ሜዳ ያደርጉታል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ለሶማሊያውያን ደኅንነት የከፈለችው አኩሪ መስዋዕትነት በትክክለኛው ጊዜ ለታላቅ ዓላማ የተከፈለ ድንቅ መስዋዕትነት ነው!

የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ካለው ስትራቴጂክ ጠቀሜታ አኳያ የብዙዎችን ቀልብ የሚስብ ነው። ይህንን ተከትሎም በየወቅቱ በሚፈጠሩ ዓለም አቀፍ የፍላጎት ተቃርኖዎች አካባቢው ለግጭት እና ለአለመረጋጋት ፤ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦችም ለድህነት እና ለኋላ ቀርነት የተጋለጡ እና በዚህም ብዙ ዋጋ እንዲከፍሉ ያስገደደ ነው።

በተለይም የቀዝቃዛውን ጦርነት ተከትሎ በአካባቢው የተፈጠረው የኃያላኑ ሽኩቻ ፣በአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች መካከል ለዘመናት የቆየውን ወንድማማችነት ፣ ተቻችሎ እና ተስማምቶ በጋራ የመኖር እሴቶችን በመሸርሸር ፣አካባቢው ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በግጭት እና በአለመረጋጋት እንዲታመስ አድርጎታል።

ይህ በአብዛኛው ከአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች እውነተኛ ፍላጎት የማይነሳ ፤ በአብዛኛው ቅኝ ገዥዎች ቀደም ባለው የአገዛዝ ዘመናቸው ፈጥረውት ከሄዱት የልዩነት ትርክት የሚቀዳው የአንድ ሃይማኖት ፣ባህል እና ማህበራዊ እሴት ባለቤት የሆኑ ሕዝቦችን ሳይቀር ተቃርኖ ውስጥ በመክተት ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ ያደረገ ነው።

ለዚህ ደግሞ ከነጻነት ማግስት ጀምሮ በአካባቢው የተከሰቱ እና ዛሬም ድረስ ለአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ሰላም እና አለመረጋጋት ምንጭ የሆኑ ችግሮች ፣ ከትናንት የልዩነት ትርክቶች የመነጩ፤ ትርክቶቹ ተጠቃሚ ያደርገናል ብለው በሚያስቡ ኃይሎች አቅም ገዝተው ፣ጉልበት አግኝተው የዘለቁ ናቸው።

ዛሬም የአካባቢው ሀገራት በቀጣናው የተሻለ ሰላም እና መረጋጋት ለመፍጠር የሚያደርጓቸው ጥረቶች ፣አካባቢው ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ፍላጎት ባላቸው ኃይሎች ትርጉም ያለው ውጤት እንዳያመጣ ፤ከዚያም አልፎ አካባቢው የአሸባሪዎች መፈልፈያ እንዲሆን አድርጎታል።

ለዚህ በሶማሊያ መሠረት ያደረገውን እና በዓለም አቀፍ አሸባሪነት የተፈረጀውን አልሸባብን ውልደት እና እድገት ማየት ይቻላል። ይህ ጽንፈኛ ቡድን በሶማሊያ እንደሀገር የልዩነት ትርክት የፈጠረውን የሀገረ መንግሥት ክፍተት በመጠቀም ፣የሀገሪቱን ሕዝቦች በጽንፈኛ አመለካከቱ ብዙ ዋጋ አስከፍሏል። ድንበር ተሻግሮም በአካባቢው ሀገራት ሰላም እና ደህንነት ላይ ስጋት ሆኗል።

የአካባቢው ሀገራት በአፍሪካ ኅብረት በኩል ሆነ በተናጠል ፣ቡድኑ በሶማሊያ ሕዝብ ላይ ሆነ በአካባቢው ሀገራት ላይ የፈጠረውን የሽብር ስጋት ለመቀልበስ ተንቀሳቅሰዋል። በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ወንድም ለሆነው የሶማሊያ ሕዝብ ሰላም እና ደህንነት ከማንም በላይ ዋጋ በመክፈል ለሕዝቡ ያላቸውን አጋርነት በሕይወት መስዋዕትነት በተጨባጭ አሳይተዋል።

ለበለጠ ድጋፍና ከንፈር ከመምጠጥ ባለፈ፤ ከአልሸባብ ጋር ፊት ለፊት በመግጠም ዛሬ ላይ የሶማሊያ ሕዝብ ላገኘው አንጻራዊ ሰላም እና መረጋጋት በታሪክ ውስጥ ገዝፎ የሚታይ የመስዋእትነት ታሪክ ጽፈዋል። በዚህም ለሶማሊያ ሕዝብ ያላቸውን ክብር እና ወንድማዊ ፍቅር በደም አረጋግጠዋል።

በርግጥ ከኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያውያን በላይ ለሶማሊያ ሕዝብ ሊቀርብ እና ሊቆረቆር የሚችል የለም ፤ይኖራል ብሎ ማሰብ የዋህነት ብቻ ሳይሆን ለትዝብት የሚጥልም ነው። የነዚህ ሀገራት ሕዝቦች ከባህል እና ከሃይማኖት ባለፈ እጣ ፈንታቸውን ብሩህ የሚያደርግ የጋራ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፍላጎቶች አሏቸው።

እነዚህ ፍላጎቶች፤ ከሁሉም በላይ አንዳቸው የአንዳቸውን ሰላም እና መረጋጋት አብዝተው እንዲያስቡ እና ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት እንዲፈጥሩ አስችሏቸዋል፤ አንዳቸው የሌላኛውን ችግር የራሳቸው አድርገው በመውሰድ ራሳቸውን ዋነኛ የመፍትሔ አካል አድርገው እንዲያስቡና በተጨባጭም የመፍትሔ አካል ሆነው እንዲቀርቡ አድርጓቸዋል።

ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ከማንም በላይ ለሶማሊያ ሰላም እና መረጋጋት ብዙ ዋጋ የከፈለው ፤በከፈለው ዋጋም ለሕዝቡ አሁናዊ እፎይታ መፍጠር የቻለው። ይህንን እውነታ በየትኛውም መልኩ አለመቀበል ፤ ወይም አሳንሶ ለማየት መሞከር የሶማሊያ ሕዝብ በአሸባሪዎች የደረሰበትን እና እየደረሰበት ያለውን መከራና ስቃይ የመደገፍና የማስቀጠል ያህል የሚቆጠር ነው።

ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ከሀገራት ጋር አለመጣጣሞች የገጠማት ሲመስላቸው በቀቢጸ ተስፋ የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ሀገራት ለሶማሊያውያን ተቆርቋሪ በመምሰል ኢትዮጵያ ላይ ችግር ለመፍጠር ድብቅ አጀንዳ ቢያራምዱም ሃሳባቸውና እቅዳቸው ቀቢጸ ተስፋ እና ከንቱ ምኞት ከመሆን አያልፍም!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከሕግ ውጪ የሚደረገው እንቅስቃሴ በራስ ላይ አደጋ መጋበዝ ነው

ዳንኤል ዘነበ

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ የሕግ የበላይነት ቅድሚያ ከተሰጣቸው ግንባር ቀደም ጉዳዮች መካከል እንደሆነ ይታወቃል። ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ለሕግ የበላይነት ቅድሚያ ከመስጠት አልፎ በህገ መንግስቱ አንቀፅ ዘጠኝ ላይ እንዲደነገግ አድርጓል ። በዚህ አንቀፅ ስር የሕግ የበላይነት በሀገራችን የሚኖረው ሁኔታ በሚገባ ተብራርቷል።

ኢትዮጵያ ያፀደቀችው ሕገ መንግስት የሕግ የበላይነትን ለማስጠበቅ ሲል ከህግ አግባብ ውጪ ስልጣን መያዝ የተከለከለ መሆኑን ያስረዳል ። የትኛውም አካል ሕገ መንግስቱ ላይ ከተደነገገው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ውጪ ነፍጥ አንግቦ ሥርዓቱን በኃይል ለመጣል የሚያደርጋቸውን ማናቸውም አይነት ተግባራት ይከለክላል።

በማናቸውም ቦታ የሕግ የበላይነት ልዕልና ካልተጠበቀ በሀገሪቱ የሚረቀቁ ማናቸውም ሕጎች በሚፈለገው መጠን ገቢራዊ ሊሆኑ አይችሉም። በሚፈለገው መጠን ገቢራዊ ካልሆኑና በቸልታ የሚታለፉ ከሆኑ የዜጎች መብቶች አይከበሩም። በሕገ መንግሥቱ ላይ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲሁ ለይስሙላ የተደነገጉ አይደሉም።

ሕግና ሥርዓት ከማንኛውም ሰው፣ ተቋም፣ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ፣ ቡድንና ስብስብ በላይ ነው። እነዚህ ሁሉ ከሕግ እና ሥርዓት በታች ናቸው። ሕግና ሥርዓትን አክብሮ የማይንቀሳቀስ የትኛውም አይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመጨረሻ ግቡ ጥፋት ነው። የሕወሓት ያለፉት ዓመታት የግትርነት ባህሪም የዚሁ ምሳሌ ነው።

በቅርቡ እንኳን የትግራይ ሕዝብ ብቸኛ ተወካይ ነኝ የሚለው ሕወሓት ከለውጡ ማግስት ፤ በዲሞክራሲያዊ ምርጭ ወደ ስልጣን ከመጣው መንግሥት ጋር የነበረውን ልዩነት በኃይል ለመፍታት የሄደበት ያልተገባ መንገድ ሀገርን ፤ በተለይም የትግራይን ሕዝብ ያስከፈለው ዋጋ ምንያህል የከፋ እንደሆነ ለማስታወስ አይከብድም።

የትግራይ ሕዝብ ብቸኛ ተጠሪ አድርጎ እራሱን የሚቆጥረው ሕወሓት ፤ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በትግራይ ሕዝብ ስም በሀገር ሆነ በትግራይ ሕዝብ ላይ የፈጠራቸው ምስቅልቅሎች ያስከፈለው ዋጋ ሊዘነጋ የሚችል አይደለም። በወቅቱ መንግሥት ችግሩን ለዘለቄታው በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በወሰደው እርምጃ ችግሩ በድርድር በሰላም ስምምነት ባይፈታ ኖሮ ሊያስከትል ይችል የነበረውን ተጨማሪ ጥፋት መገመት ቀላል ነው።

ሕግ እና ሕገ- መንግሥታዊ ሥርዓትን በማክበር ላይ የተመሰረተው የሰላም ስምምነቱ ከሁሉም በላይ ለትግራይ ሕዝብ ሰላም ማስፈን አስችሏል። ሕዝቡ ግጭት ከሚፈጥረው ሞት ፣ የአካል ጉዳት ፣ ስደት እና የስነልቦና ቀውስ ወጥቶ ፊቱን ወደ ሰላም ማዞሩ ይታወቃል።

ይሁንና “ቀበሮ መልኩሳ አመሏን አትረሳ ”እንደሚባለው ከሰሞኑ ቡድኑ በተፈጠረው ሰላም እፎይታን ያገኘው የትግራይ ሕዝብን ዳግም አንገት ለማስደፋት እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምሯል። ሕወሓት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቀው አዋጅ ተራምዶ ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ትዕዛዝ ንቆ ከሕግ ውጪ ጠቅላላ ጉባኤውን አድርጓል።

የሰሜኑ ጦርነት ከተቀሰቀሰ ሦስት ወራት ገደማ በኋላ የሕወሓት ሕጋዊ ሰውነት በምርጫ ቦርድ መሰረዙ ይታወቃል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነባሩን የፓርቲዎች ምዝገባ እና ሥነ ምግባር አዋጅን በማሻሻል በኃይል እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሳተፉ ለነበሩ የፖለቲካ ቡድኖች ሕጋዊ ዕውቅና የሚሰጠው አዋጅ ግንቦት 27 ቀን 2016 ዓ.ም ጸድቋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቀው ይህ አዋጅ፤ ኃይልን መሠረት ባደረገ የአመጽ ተግባር ተሳትፎ የነበረ የፖለቲካ ቡድን በልዩ ሁኔታ በፓርቲነት የሚመዘገብበትን ሂደት በዝርዝር ያስቀምጣል። ፓርቲው ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በልዩ ሁኔታ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ለመመዝገብ እንዲችል በደብዳቤ ጥያቄ አቅርቧል።

ምርጫ ቦርድ ሕወሓት ያቀረበውን ማመልከቻ እና ሰነዶች መሠረት በማድረግም ፓርቲው በልዩ ሁኔታ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ እንዲመዘገብ ወስኗል። በዚህም ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤውን ከማካሄዱ ከ21 ቀናት በፊት የጉባዔውን ቀን ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት። ቦርዱ በቀሪዎቹ ጊዜያት የፖለቲካ ፓርቲው “ሰላማዊ እንቅስቃሴ እያደረገ ስለመሆኑ” ክትትል የማድረግ እና ግብረ መልስ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

ምርጫ ቦርድ ይህንን ቢልም ሕወሓት ከሕግ ውጪ ጠቅላላ ጉባኤውን ማድረጉ ሕገወጥ ያደርገዋል። ቡድኑ ሕግና ሥርዓትን ባላከበረ መልኩ የሚያደርገው ፖለቲካ እንቅስቃሴ ከራሱ ከፓርቲው ጭምር ነቀፌታ ደርሶበታል። የሕወሓት ምክትል ሊቀመንበርና የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ረዳ ጭምር ጉባዔው የትግራይን ሕዝብ ደኅንነት አደጋ ላይ ከመጣል የዘለለ እርባና እንደሌለው ተናግረዋል።

አቶ ጌታቸው የፓርቲውን ሕጋዊ ሰውነት የመመለስን ጉዳይ በሚመለከትም “የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባ አዋጅ ሕወሓት እንደ አዲስ እንዲመዘገብ የሚያደርግ፣ የትግራይ ሕዝብ የከፈለውን መስዋዕትነት የሚያጎድፍ፣ በቀጣይም ቅርቃር ውስጥ የሚከት መሆኑን በመገንዘብ፣ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንዲፈቱ በማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት ከመግባባት ተደርሶ ነበር” ሲሉ የቡድኑ አካሄድ ከሕግ አግባብ ውጪ የሚደረገው ጉዞ ለሕዝብ ጥቅም ሳይሆን የግል ፍላጎትን ግብ እንዳደረገ አጋልጧል።

ትናንት ኃይልን መሠረት ያደረገ የአመፅ ተግባሩን በማቆም ሕገ-መንግሥታዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተስማማው ሕወሓት ከሕግ ውጪ ሊሆን የሚችልበት አሠራር እንደሌለ ጠፍቶት አይደለም። የቡድኑ ድርጊት ትናንት በፈጠረው ስህተት የቆሰለው የትግራይ ሕዝብ ቁስል ሳይሽር አዲስ ቀውስ ለመፍጠር ሽርጉድ እንደማድረግ ይቆጠራል።

ቡድኑ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት በትግራይ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግፍ አልበቃ ብሎት ሕዝቡን ለዳግም መከራ ለመዳረግ እያሟሟቀ መሆኑን በሕገ ወጡ ጉባኤ ላይ በድፍረት እየተናገረ ይገኛል። ሕገ ወጡን ጉባዔ የመሩት ደብረጽዮን (ዶ/ር) ጉባዔውን ማካሄድ ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያት የትግራይን ሕዝብ ከተጋረጠበት አደጋ ለማዳን እንደሆነ ተናግረዋል። “እኛ ከሌለን ሀገር መምራት አይቻልም፤ የትግራይ ሕዝብ ያለኛ አይኖርም” የሚል ቆሞ ቀር አስተሳሰብ በሕገ ወጡ ጉባኤ ላይ ተንጸባርቋል። ይህ እሳቤ የትግራይ ሕዝብን መናቅ፤ ከእውነት መራቅም ነው።

የትግራይ ሕዝብ ከፓርቲው ያተረፈው ምንድነው? ተብሎ ቢጠየቅ ፤ ጦርነት ፣ሞትና ድህነትን ነው ። ሕዝቡ ለራሱ፣ ለቤተሰቡ እና ለሀገሩ ተስፋ የነበረን ትውልድ ለሞት እና ለአካል መጉደል፣ በትሪሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት ለውድመት አትርፏል። ከዚህ ሁሉ ጥፋት በኋላ “እኔ አድንሃለው” የሚልፈሊጥ የሚያሳፍር ነው።እዚህ ላይ ትልቁ ጥያቄ መሆን ያለበት የትግራይን ሕዝብ ከማን ነው የሚያድነው? የትግራይ ሕዝብ አሁን ላይ የሚፈልገው ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት የሚታደገውን ነው። ለዚህ ደግሞ ሕወሓት የታደለ አይደለም፤ ደግሞ ያለፉትን ሁለት አስርት የስልጣን ጉዞውን ማጤን በቂ ነው ።

የክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር አቶ ጌታቸው እንዳሉት፤ ከሕዝብ ፍላጎት እየተቃረኑ በትግራይ ሕዝብ ስም የሚፈጸም ሕገ ወጥ ተግባር የግል ፍላጎትን ለማሟላት የሕዝብን መከራና ሰቆቃ ለማራዘም የሚደረግ እኩይ አካሄድ ነው፤ ሊቆም ይገባል። በጥቂት ቡድኖች የስልጣን ፍላጎት ።ዳግም የትግራይ ሕዝብም ሆነ ሀገር ዋጋ መክፈል የለባቸውም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆነ የትግራይ ሕዝብ የዘመናት መሻቱ ሰላም እና ልማት እንደሆነ ይታወቃል። ሕዝቡ በተለያዩ ጊዜያት የከፈላቸው መስዋእትነቶች ይህንን እውነታ ተጨባጭ ለማድረግ እንደሆነ መረዳት ይገባል። ስለሆነም የትኛውም ለሕዝብ ፍላጎት እታገላለሁ የሚል ኃይል ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በሕግ አግባብ መሆን አለበት።

ከዚህ አኳያ ማንኛውም የሕዝብ ፍላጎት ፍላጎቴ ነው የሚል አካል ሕግ እና ሕጋዊ ሥርዓትን ማክበር ፣ ልዩነቶችን በውይይት እና በድርድር መፍታት ፣ ከሁሉም በላይ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን ተቋማት ውሳኔ ማክበር ፣ ለውሳኔያቸው ተፈጻሚነት ራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል። ከዚህ ውጪ በሕዝብ ስም የሚደረግ የትኛውም እንቅስቃሴ ከሕዝብ ፍላጎት ጋር ተቃርኖ መቆም ነው። በራስ ላይ አደጋ መጋበዝም ነው።

መንግሥትም ይህ አይነቱን የሕዝብ ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ከሕዝብ ፍላጎት ጋር የተቃረነ ሕገ ወጥ እንቅስቃሴና አካሄድን አደብ ማስያዝ አለበት። ፓርቲው ሕግና ሥርዓት ባላከበረ መልኩ የሚያደርገውን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ማስተካከል ይኖርበታል። የትግራይ ሕዝብም፤ የሕግ ሥርዓት ከማንኛውም ሰው፣ ተቋም፣ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ፣ ቡድን፣ ስብስብ በላይ መሆኑን ማሳየት ይኖርበታል።

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሴሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስለስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ‹‹ልጆቻችሁ ልጆቻችን ናቸው ››

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ትውልድና ዕድገቷ ባህርዳር ከተማ ነው። አዲስ አበባ ስትመጣ የእሷንና የቤተሰቦቿን ኑሮ በተሻለ ለመቀየር አስባ ነበር። አገሬነሽ ለከተማ ህይወት አዲስ አይደለችም። የቦታ ለውጥ ካልሆነ በቀር ከተማ ለእሷ ግርታን አይፈጥርባትም። ሾፌሩ ባለቤቷ ለቤት ለትዳሩ መልካም ገቢ ለማግኘት ርቆ መሄድን ፈልጓል። ለዚህ ደግሞ ምርጫው ባህርዳር ሳይሆን አዲስ አበባ ነው።

ባልና ሚስት ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ካሰቡት ስፍራ ከተሙ። እንደታሰበው ለጥቂት ጊዜያት ህይወት መልካም ሆነላቸው። ትንሹ ልጅ የግል ትምህርት ቤት ተመዝግቦ መማር ጀመረ። ኑሮ ቢከብድም ለእነሱ የሚያቅት አልሆነም። አባወራው ወጣ ብሎ እየሰራ ወይዘሮዋ ቤቷን በወጉ እየመራች ነው።

ውሎ አድሮ የጥንዶቹን ትዳር የሚፈትን አጋጣሚ ተፈጠረ። በድንገት ግዳጅ እንዲሄድ የተወሰነበት ሾፌሩ አባት ለወራት ቤተሰቡን ትቶ ሊለያቸው ሆነ። ይህ ጊዜ ብዙ ለሚያስቡት ባልና ሚስት አስቸጋሪ ነበር። ከፍ ባለ ክፍያ የሚማረው ህጻን በጀመረው አልቀጠለም። ለቤት ኪራይና ለሌሎች ወጪዎች በቂ ገንዘብ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ አባወራው በቅርብ የለም። ወይዘሮዋ ክፉኛ ተጨነቀች። ዛሬን እንደ ትናንቱ እየኖረች አይደለም። የህጻኑ ትምህርት ቤት ለወራት ሳይከፈል ቀጠለ። አገሬ ግራ ገባት። ከየት አምጥታ ግዴታዋን እንደምትወጣው አታውቅም።

ትንሹ ልጅ ጎበዝ የሚባል ተማሪ ነው። በዚሁ ከቀጠለ ለሀገር ተስፋ ለወገን አለኝታ ይሆናል። አሁን ግን በመንገዱ የሚቀጥል አይመስልም። የትምህርት ቤቱ ክፍያ በዕዳ መመዝገብ ይዟል። ብቸኝነትን ከችግሮች የተጋፈጠችው እናት ስለልጇ ትምህርት ብዙ ሞከረች። አንድ ሁለት ማለት የጀመረው ጊዜ እንደቀልድ ወራት አስቆጠረ። ሰኔ ደርሶ ትምህርት ቤት ሲዘጋ ጎበዙ ልጅ በጥሩ ውጤት ክፍሉን ተሻገረ።

አገሬ አሁን እንደትናንቱ እየከፈለች ልጇን ማስተማር አትችልም። ከአንደኛ ክፍል ወደቀጣዩ በጥሩ ውጤት ላለፈው ልጇ ሌላ ትምህርት ቤት መፈለግ አለባት። ለዚህ ደግሞ አቅሟ የሚችለውን ፈልጋ ማስተማር ግድ ይላታል። የልጇን ማስረጃ ከእጇ ለማድረግ እስካሁን በዕዳ የተማረበትን ክፍያ ማጠናቀቅ አለባት። እናት አፏን ሞልታ የትምህርት ማስረጃውን መጠየቁ ከበዳት። ዙሪያው ገደል ሆኖባት በትካዜ ከረመች።

ክረምቱ ሳብ ሲል የልጇ እኩዮች ትምህርት ቤት መመዝገብ ጀመሩ። አገሬ ይህን ማድረግ ባለመቻሏ የ‹‹በይ ተመልካች›› የሆነች ያህል ተሰማት። ዝም ማለት አልፈለገችም። መልሱን ብታውቀውም ለሚመለከታቸው አካላት ጥያቄዋን አቀረበች። የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች ለወራት መከፈሏን አሳምረው ያውቃሉ። ቀጣዩን ዓመት ልጇ በትምህርት ቤቱ እንደማይማር ሲገባቸው ደግሞ ሃሳቧን ተቃወሙ።

ትንሹ ልጅ በትምህርት ልቆ የተሸለመበት የምስክር ወረቀት በእጁ ይገኛል። ይህ ብቻውን ግን አዲስ ትምህርት ቤት አያስገባውም። ተገቢው ማስረጃ ሊኖርና ማለፉ ሊረጋገጥ ግድ ነው። ጊዜው እየገፋ መፍትሄ እየራቀ ሲሄድ አገሬ መፍትሄ ላለችው ሃሳብ ፈጥና ሮጠች። ችግር ክፉ ነው፤ ያሸማቅቃል፣ የሰው ፊት ያሳያል። እናት ስለልጇ በየትምህርት ቤቱ፣ በየዘመድ ቤቱ፣ ደጅ ጠናች። ተማጸነች።

ጊዜው ሲደርስ ጸሎቷ ተሰማ። ብዙ ችግሮችን እያለፈች፣ በርካታ ፈተናዎች እየገጠሟት የቆየችው ሴት አንድ ቀን ከአንድ ትምህርት ቤት ደጃፍ ደርሳ በሩን አንኳኳች። የከፈቱላት እጆች አልገፏትም። ብሶቷን አደመጡ ፣ ችግሮቿን ተረዱ። በእሷ ጥያቄና በልጇ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ምን እንደሚባል አታውቅም። ቀጠሮ ተቀብላ ስትወጣ የቀጣዮቹን ቀናት ፈተናዎች እያሰበች ነበር።

ትምህርት ቤት ሊከፈት ጊዜው ተቃርቧል። ለልጆቻቸው ደብተር የሚገዙ ‹‹ዩኒፎርም›› የሚያሰፉ ወላጆች ስራ በዝቶባቸዋል። አገሬ አሁንም ስለልጇ ትምህርት ቁርጡን አላወቀችም። ትናንትናን ከዛሬ እያስታወሰች በሃሳብ ናወዘች።

ሁለት ልጆችን ከቤት አስቀምጦ ያለአንዳች መፍትሄ መኖር ይከብዳል። ልጁን እኩዮቹ ሲማሩ በር ዘግቶ ማዋል፣ ‹‹አትሄድም›› ብሎ ማገድ አይቻልም። ይህ አይነቱ ሀቅ ለአገሬ ሸክሙ የከበደ ውሉ የተቋጠረ ነው። ሁሌም በለቅሶ የምትውለው ወይዘሮ አሁንም በጭንቀት ተይዛለች።

ከቀናት በአንዱ በቀጠሮ ከተለየችው ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ በድንገት ተገኘች። በእንዲህ አይነቶች ቦታ መገኘት ለእሷ አዲስ አይደለም። እነዚህኞቹ ደግሞ ምን እንደሚሏት አታውቅም። ቀድሞ ባገኛቻቸው ጊዜ በመልካም እንደተቀበሏት ታውቃለች። ከቆይታ በኋላ ያሏትን አድምጣ፣ የምትላቸውን ሰምተው ተለያዩ። ውስጧ ልትገልጸው በማትችለው ድንገቴ ስሜት ተናወጠ።

ከጊዚያት በኋላ ወደ ግዳጅ የተላከው አባወራ በሰላም ወደቤቱ ተመልሶ ቤተሠቦቹን ተቀላቀለ። ወይዘሮዋ ስለሆነላት መልካም ነገር ፈጣሪዋን አመሰገነች። ባል ከቤቱ ሲገባ በኑሮው እንደገና ማንሰራራት እንዳለበት ገባው። በእሱ አለመኖር ከቤተሰቡ የጎደለውን ሁሉ አላጣውም። አሁን ተመልሶ የቤቱ ራስ ሊሆን ግድ ይለዋል።

በሰላም መመለሱ ለጎጆው፣ለባለቤቱና ለመላው ቤተሰብ ታላቅ ተስፋ ነው። ነገን በተሻለ ለመኖር ደግሞ ሥራ ወደተገኘበት ሁሉ ፣ መሄድ ይኖርበታል። ጥቂት ቆይቶ አባወራው መኪና ይዞ ወደ አንድ ስፍራ ተጓዘ። የሄደበት አካባቢ ሰርቶ ገንዘብ የሚያስገኝለት ነው።

እንዲህ በሆነ ጥቂት ጊዚያት በኋላ ለወይዘሮዋ ጆሮ ክፉ ዜና ደረሰ። ባለቤቷ መኪና ይዞ በተጓዘበት አካባቢ ባልታወቁ ሰዎች በጥይት መመታቱን ሰማች። ይህ እውነት ሞላ ጎደለ ለምትለው የቤት እመቤት ከመርዶ በላይ ቁጣ ሆነባት። አንዱ ችግር ሳይፋቅ ሌላኛው ተደረበ።

የዕድል ጉዳይ ሆኖ ባለቤቷ በህይወት ተርፏል። ተመልሶ አዲስ አበባ ሲመጣ ግን ሁለት እግሮቹ ተመተው ክፉኛ ተጎድቶ ነበር። ሁኔታው ‹‹በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ›› ይሉት አይነት ቢሆንም አገሬ አላማረረችም።

**‹‹ልጆቻችሁ ልጆቻችን... ወደ ገጽ 17 ዞሯል**

# እንዲህም ይኖራል

## ‹‹ልጆቻችሁ ልጆቻችን...

**ከገፅ 16 የዞረ**

በህይወት ተርፎ ለቤቱ፣ በመብቃቱ ፈጣሪዋን ‹‹ተመስገን ›› አለች ።

ውሎ አድሮ ባለቤቷ ድኖ መራመድ ጀመረ። ዛሬ ላይ ደግሞ በቀድሞው ስራ መመለስ ይፈልጋል። የመንገዱ አለመረጋጋት፣ የሰላም ዕጦት ሁኔታ እንዲህ ሊያደርግ አላስደፈረውም። ወይዘሮዋ በችግርና ከፉ አጋጣሚዎች ተከባለች። ተስፋ ግን አልቆረጠችም። ልጇ ከቤት እንዳይውልና ትምህርቱን እንዲቀጥል ጥረቷ ሩጫዋ አልተገታም። ብሩህ ስሜት በውስጧ መመላለስ ጀምሯል።

**ሆደባሻዋ ወይዘሮ**

ወይዘሮ መሰረት ለታ ከአዲስ አበባ ወጣ ከምትል የገጠር ቀበሌ ተወልዳ አድጋለች። ገና በልጅነቷ ወላጆቿ ለባል ቢሰጧት ትምህርት ይሉትን ላታይ ተፈረደባት። ‹‹ጅዳ›› የምትባለው የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎች መተዳደሪያቸው ግብርና ነው። የእሷም ህይወት በዚህ ተቃኝቷል። ባለቤቷ አራሽ ገበሬ ነው። በሬውን ጠምዶ መሬቱን ሲያርስ ሲገምስ ይውላል።

ያለ ይሁንታዋ በገባችበት ትዳር ባትደሰትም። ቤቷንና ባሏን አክባሪ ናት። ሁሌም ጎጆዋን ልትሞላ ትተጋለች። ይህ ድካሟ ግን ከአባወራዋ አልተዛመደም። ከስራ መልስ እየጠጣ ፣እየሰከረ ይረብሻት ያዘ። መሀላቸው ፅኑ ቅያሜ ገባ ችግራቸው እንደሌሎች በሽምግልና አልተፈታም።

ከቀናት በአንዱ መሰረት ባለቤቷ የእርሻ በሬዎቹንና ከብቶቹን እንደሸጣቸው ሰማች። ሁሉም የሆነው እሷ ሳታውቅ ነውና ውስጧ ጎሸ። አዘነች፣አለቀሰች። መለስ ብላ ሁለቴ አላሰበችም። ፈጥና ወሰነች ። ትዳርና ጎጆ ይሉት አስጠላት። ማንም ሳያውቅ ተደብቃ ወጣችና ጠፍታ አዲስ አበባ ገባች። የበደል ኑሮዋን ተወልዳ ባደገችበት ገጠር ምሳ፣ቆፍራ ቀበረችው ። የአዲስ አበባን ህይወት በሰው ቤት ተቀጥራ ስምንት ዓመታትን ሰራች።

የትናንቱን ከፉ ህይወት ካስረሳት ሰው ጋር ስትተዋወቅ ቀጣይ ኑሮዋ በትዳር ታሰረ። እሱ መልካም ሰው ነውና ሀሳቧን ያከብራል። በፍቅር የጸናው ጎጆ በመጀመሪያ ልጃቸው ተባርኮ በመከባበር ፀና። መሰረት ልጅዋን እያሳደገች የባሏን ሰላም ውሎ መግባት ተመኘች። ህይወቷ በፍቅር በደስታ ተሟሸ። አባወራዋን አክባሪ ትዳሯን ወዳድ ሆነች።

ከቀናት በአንዱ በድንገት የታመመው የመሰረት ባል በቀላሉ አልተሻለውም። ህመሙ ባይቆይበትም በስቃይ ሲንገላታ ከረመ። ሁለተኛ ልጇን ነፍሰጡር የሆነችው ወይዘሮ እሱን በማስታመም ተንገላታች። አልሆነላትም። በድንገት ሞት ደርሶ ቢነጥቀው ህይወቷ ተቃወሰ።

ነፍሰጡሯ ወይዘሮ ኑሮዋ እንደቋጥኝ ከበዳት። ከወለደች በኋላ ሁለት ህጻናት ያለረዳትና ወዳጅ ዘመድ ይዞ መኖር ለእሷ ቀላል አልሆነም። የቤት ኪራይ፣ የዕለት ወጪና የልጆች ቀለብ ተቸገረች። ልበ መልካሞች የቻሉትን እያገዟት ጥቂት ቀናትን አለፈች።

መሰረት ቤት ኪራዩን አልቻለችም ልጆቿን ይዛ ወጣ ለማለት ሞከረች። ቤት እየጠበቀች የምትኖርበት መጠጊያ አላጣችም። ልጆች ለማሳደግ እንግልቷ ቀጠለ። እንጀራ እየጋገረች፣ ጉልበቷን እየከፈለች ለልጆቿ ሮጠች። ዘመዶቿ ባይጠይቋትም የባዕድ ዘመድ አላጣችም። ያጣቸውን እየሰጡ፣ የጎደለውን እየሞሉ ክፉ ቀናትን አሻገሯት።

አሁን ህይወት ብላ የሰየመቻት ልጇ ትምህርት ቤት መግቢያዋ ነው። መሰረት ተጨነቀች። እኩዮቿ ከትምህርት ውለው መምጣታቸውን ስታይ አብዝታ አዘነች። እሷ ቢቸግራትም። ልጆቿ ዕውቀት እንዲነፈጉ አትሻም። ሆደባሻዋ እናት ቀን ከሌት አለቀሰች። አንድ ቀን ግን ዕንባዋን የሚያብስ፣ ችግሯን የሚካፈል አጋጣሚ አገኘች።

ወደአንድ ትምህርትቤት ቅጥር ስትደርስ የእሷን ብሶት የሚያደምጡ ፣ ጆሮዎች ትኩረት ሰጧት። ትኩስ ዕንባዋን የሚያብሱ እጆች አቅፈው ተቀበሏት። መሰረት የሆነውን አላመነችም። ያሳለፈችውን ህይወት፣ያለችበትን ኑሮ ሳትደብቅ ዘርዝራ ተናገረች።

**በኦርቶተ አጸድ**

አቶ ሀፍቶም ነጋ የኦርቶተ ትሬዲንግ አክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ ናቸው። በ2014 ዓ.ም ስራውን የጀመረው ኦርቶተ ትሬዲንግ በበርካታ አባላት የተዋቀረ ስለመሆኑ ይናገራሉ። ትሬዲንጉ ከተቋቋመባቸው ዓላማዎች አንደኛው ደግሞ በትምህርት ዘርፉ የሚያካሄድ ሰፊ እንቅስቃሴ ነው።

ምስረታውን ለገጣፎ ‹‹ሆጬ›› ከተባለ ቦታ ያደረገው የኦርቶተ አካዳሚ ከአጸደ ሕፃናት ጀምሮ ተማሪዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል። ወደፊት ደግሞ አቅሙን እስከ ዩኒቨርሲቲ የማሳደግ ዕቅድ አለው። በቅርቡ ያስመረቃቸው የመጀመሪያዎቹ የአጸደ ሕፃናት ተማሪዎችም በታሪኩ ቀዳሚዎቹ ሆነው ተመዝግበዋል።

ትምህርትቤቱ ተማሪዎችን የሚቀበለው በክፍያ ነው። እንዲያም ሆኖ ችግር ያለባቸውንና ከፍለው መማር የማይችሉ እኩዮቻቸውን መዘንጋት አይሻም። የትምህርትቤቱ መከፈት ዋና ዓላማ ለትርፍና ክፍያ መሽቀዳደም አይደለም። በትምህርት የላቁ ተማሪዎችን ማፍራት ተቀዳሚ ዕቅዱ ነው።

አቶ ሀፍቶም እንደሚሉት ትምህርት ቤቱ በአካባቢው መከፈቱ የበርካታ ተማሪዎችንና ወላጆቻቸውን ጥያቄ ለመመለስ አስችሏል። በአሁኑ ጊዜ ልጆች ከአካባቢያቸው ርቀው እንዳይሄዱ ሆኗል። በተለያዩ ምክንያቶች የመማርን ዕድል ያላገኙ ተማሪዎችም የበረከቱ ተካፋይ መሆን ጀምረዋል። አገሬና መሰረትን የመሰሉ ወላጆች ደግሞ በጊቢው ደርሰው ዕንባቸው ታብሷል። ዛሬ ልጆቻቸው ነፃ የትምህርት ዕድል አግኝተዋል።

ትምህርት ቤቱ የተለየ ድጋፍ ለሚያሻቸው ተማሪዎችም በጀት አለው። ዮስያስን የመሰሉ በዊልቸር የሚጓዙ ልጆች ሲመጡም የትምህርት ዕድልን አልነፈገም። በሩን ከፍቶ ‹‹እነሆ ! ›› ከበረከቱ እያላቸው ነው። ኦርቶተ አካዳሚ በቅርቡ በነበረው ዝግጅት ደስታን ያቀበለው ለተመራቂ ተማሪዎቹ ብቻ አይደለም። ሕፃን ዮስያስን ለመሰሉ ብርቱ ተማሪዎቹ ጭምር እንጂ። ሕፃን እዮስያስ ከወሊድ ጋር በተያያዘ ባጋጠመው የጤና ችግር የአካል ጉዳት አጋጥሞታል። ከወገቡ በታች ካለመንቀሳቀሱ ባሻገር የዳይፐር ተጠቃሚ ነው።

ወላጅ እናቱ ወይዘሮ ልኬለሽ ተፈሪ እሱን አሳድጋ ከዕውቀት ለማገናኘት በቀላሉ የማይገለጽ ዋጋን ከፍላለች። ትምህር ቤት ለማስገባት፣ ‹‹አስተምሩልኝ ››፣ ለማለት ልጇን አዝላ የበርካቶችን ደጃፍ ረግጣለች፤ የብዙዎችን ፊት አይታለች። በአካልና በአዕምሮ የተቀበለችው ስቃይም የዋዛ አልነበረም።

ልኬለሽ ወደአካባቢው ደርሳ የኦርቶተ አካዳሚን በጠየቀች ጊዜ ፊት የነሳት፣ በር የዘጋባት አልነበረም። ዮሲን ተቀብሎ ለማስተማር ይሁንታቸውን በፈገግታ የመለሱላት ብዙዎች ሆኑ። ዮስያስ በዊልቸር እየተገፋ ከጓደኞቹ ጋር ለትምህርት ተሰለፈ። ለእሱ ፍቅርና አክብሮት የሚሰጡት፣ አቅፈው የሚስሙት፣ ሲገባ ተቀብለው፣ ሲሄድ የሚሸኙት ተሽቀዳደሙ።

በቅርቡ ትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ያላቸውን ተማሪዎቹን ባስመረቀ ጊዜ ዮሲ ባልንጀሮቹና መምህራኖቹ መሀል ተገኘ። መመረቅን ያለፈው ቢሆንም ደስታውን ለመቀላቀል ግን የቀደመው አልነበረም።

ዮስያስ በዝግጅቱ መሀል ከመድረክ ላይ ወጥቶ ሀሳቡን በግጥም ገለጸ። ስለተሰጠው የመማር ዕድልም ትምህርትቤቱንና መምህራኖቹን አመሰገነ። ከዚህ በኋላ የነበረው አጋጣሚ ግን ለየት ያለ መልክ ነበረው። የአካዳሚው ቦርድ አባላት ተማሪ ዮስያስን ባዩት ጊዜ ሰብሰብ ብለው መከሩ። ምክራቸው በቀና ልቦች የተዋቀረ፣ በክርክር ጭቅጭቅ ያልቆየ ነበር። ቃላቸው አንድ ሆኖ ውሳኔያቸውን አስታወቁ።

ሕፃን እዮስያስ ጎበዝና ጠንካራ ተማሪ ነው። ለመማር ያለው ፍላጎትና ፍቅር ደግሞ አክብሮት ሊሰጠው ይገባል። እናም የዕለቱ የሚከፍላቸውን ዋጋዎች‹‹የሚያልፋቸውን ፈተናዎች የሚያቀል፣መፍትሄ ያሻዋል።

ዮስያስ ከዚህ በኋላ ስለ ትምህርት ቤቱ ክፍያ አያስብም። የመማሪያ ቁሳቁሶችም በትምህርትቤቱ አቅም ይሸፈናል። በእጅጉ ለሚያስፈልገው የዳይፐር አቅርቦትም ከዚህ በኋላ ወጪውን የሚችልለት የገዛ ትምህርትቤቱ ሆኗል። ዕንባ ሳቅ የቀላቀለው ደስታ በብዙኃን ፊት ሲነበብ በግልጽ ተስተዋለ። ዮስያስና እናቱ የኦርቶተ አካዳሚን ከልባቸው አመሰገኑ።

አቶ ሀፍቱ እንደሚሉትም ትምህርትቤቱ ለጥቅም ብቻ የተመሰረተ ባለመሆኑ በየጊዜው ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የሚፈጥን ነው።በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እሳቤ ተማሪዎች ሁለት መምህራን አሏቸው። የመጀመሪያዎቹ በስጋ የወለዷቸው ወላጆች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በሙያ የተቀጠሩት መምህራን ናቸው።

ትምህር ቤቱ ለወላጆች በቂ የሚባል ስልጠና ይሰጣል። በየጊዜው ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት መስራትም አዲስ አይደለም። በትምህርት ቤቱ ግቢ የፊት ለፊት ግድግዳ ላይ በጉልህ የተጻፈው አንድ ቃል ደግሞ በትክክል ገዢ ሆኖ ሲተገበር ይውላል።

‹‹ልጆቻችሁ ልጆቻችን ናቸው›› የሚለው ታላቅ መልዕክት።

